አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የፅህፈት ክሂል የማስተማር ስነ-ዘዴዎች አተገባበር ፍተሻ

በ
አንለይ አዳነ

ሰኔ 2000 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የፅህፈት ክሂል የማስተማር ስነ-ዘዴዎች አተገባበር ፍተሻ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ለድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አንለይ አዳነ
ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርህ ትምህርት ውስጥ የፅህፈት ክሂል የማስተማር ስነ-ዘዴዎች አተገባበር ፍተሻ

በ


አንለይ አዳነ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል


የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ — ፊርማ

ፈታኝ — ፊርማ

ፈታኝ — ፊርማ

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ............ i

የስንጠረዥ ማውጫ ............ ii

አጠቃሎ ............ iii

ምዕራፍ አንድ ............ 1

መግቢያ ............ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ ............ 3

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ............ 3

1.4. የጥናቱ ወሰን ............ 4

ክፍል ሁለት ............ 5

ክለሳ ድርሳን ............ 5

2.1. የመርሀ ትምህርት ምንነት ............ 5

2.1.1. የመርሀ ትምህርት አስፈላጊነት ............ 6

2.1.2. የመርሃ ትምህርት አተገባበር ፍተሻ ............ 7

2.2. የስነ-ዘዴ ምንነት ............ 8

2.3. የዕህፈት ምንነት ............ 8

2.3.1. የዕህፈት ትምህርት ዓላማ ............ 10

2.3.2. የዕህፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ............ 10

2.3.2.1. ሥነ-ልቦናዊ ባህርይ ............ 11

2.3.2.2. ሥነ- ልሳናዊ ባህርይ ............ 11

2.3.2.3. አእምሮታዊ ባህርይ ............ 11

2.4. የዕህፈት ክሂልን የማቀድና የማስተማር መርሆዎች ............ 12

2.5. የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች ............ 13

2.5.1. በውጤት ላይ ያተከረ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ (Product Focused Approach) ............ 13

2.5.1.1. ውስን ፅህፈት (Controlled Writing) ..... 14
2.5.1.2. መር ፅህፈት (Guided Writing) ..... 15
2.5.1.3 ነፃ ፅህፈት (Free Writing) ..... 16
2.5.1.4. በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ አስተያየቶች ..... 17
2.5.2. ሂደታዊ አቀራረብ (Process Approach) ..... 18
2.5.2.1. ቅድመ ፅህፈት (Pre-Writing) ..... 18
2.5.2.2. የፅህፈት ጊዜ (While Writing) ..... 19
2.5.2.3. ድህረ ፅህፈት (Post Writing) ..... 20
2.5.2.4. በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ አስተያየቶች 20
2.5.3. ውጤት - ወሂደት አቀራረብ (Process- Product Approach) ..... 21
2.6. በዚህ የጥናት ርዕስ ዙሪያ ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ጥናቶች ..... 22
ምዕራፍ ሶስት ..... 24
የአጠናን ዘዴ ..... 24
3.1. የናሙና አመራረጥ ..... 24
3.1.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ..... 24
3.1.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ..... 24
3.1.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..... 25
3.2. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 25
3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ ..... 25
3.2.2. የሰነድ ምርመራ ..... 26
3.2.3. የፅሁፍ መጠይቅ ..... 26
3.3. የመረጃ አተናተን ..... 27
ምዕራፍ አራት ..... 28
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ..... 28
4.1. የመረጃ ትንተና ..... 28
4.1.1. ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 28
4.1.2. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 32
4.1.3. ከመምህራን በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 42

4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........................................................................ 54
ምዕራፍ አምስት ........................................................................ 62
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ........................................................................ 62
5.1. ማጠቃለያ ........................................................................ 62
5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ........................................................................ 64
ዋቢ መፃህፍት ........................................................................ 66
አባሪ አንድ ........................................................................ 70
አባሪ ሁለት ........................................................................ 72
አባሪ ሶስት ........................................................................ 79

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት ከግብ እንዲደርስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ሙሉ ስራውን በመመርመር ገንቢ የማሻሻያ አስተያየታቸውን ለለገሱኝ መምህሬና አማካሪዬ ለረዳት ፕሮፌሰር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ጥናቱን ለማካሄድ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ተገኝቼ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እችል ዘንድ ፈቃዳቸውን ላልነፈጉኝና ለተባበሩኝ ለደምበጫ፣ ለአዲስ አምባ፣ ለዋድና ለአርበኞች ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራንና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ መጻህፍትን በማዋስ፣ በቪዲዮ ቀረጻ ወቅት ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝና ለተባበሩኝ፣ የሐሳብና የሞራል ድጋፋቸው ላልተለየኝ ጓደኞቼ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ለሆነው ለሙሉሰው አስራቴ፣ ለተስፋ አከለ፣ ለየሽጥላ ምንይልሸዋ፣ ለዑመር ዳውድ፣ ለይግረም ሹቴ እና ለጋረድ ተካ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

የትምህርት ዕድል በመስጠትና ለሁለት ዓመት ሙሉ ደመወዝ በመክፈል ያስተማረኝን የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ሳመሰግነው እወዳለሁ። ይህን ጥናት ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ የአደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ትልቅ ባለውለታዬ ነው።

በመጨረሻም የጥናቱን ረቂቅ በኮምፒዩተር በመፃፍ፣ ስህተቶችን ለቅማ በማረምና በማስተካከል የረዳችኝን ንብረት ኃይሉን ከልብ አመሰግናታለሁ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ

ገጽ

ሰንጠረዥ 1. በእርከኑ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረበውት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶችን ስርጭት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........................................29
ሰንጠረዥ 2. በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የአንቀጽ አፃፃፍን የሚያሳዩ መግለጫዎች .......... 31
ሰንጠረዥ 3. የጽህፈት ትምህርት የማስተማር ዘዴ ትግበራ የሚያሳይ መግለጫ ............ 34
ሰንጠረዥ 4. የመማር ማስተማር ክንውኖች መግለጫ ........................................ 37
ሰንጠረዥ 5. በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህራንንና የተማሪዎችን ሚና የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........................................................................ 41
ሰንጠረዥ 6. የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ መግለጫ.............................................. 43
ሰንጠረዥ 7. የመምህራን የዕውቀትና ክህሎት ሁኔታ መግለጫ.................................. 45
ሰንጠረዥ 8. የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል የመምህራንን የፅህፈት ትምህርት አተገባበር የሚያሳይ መግለጫ.................................................... 46
ሰንጠረዥ 9. የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች በመምህራን ያላቸውን የመማር ማስተማር ክንውን አተገባበር የሚያሳይ መግለጫ..................... 47
ሰንጠረዥ 10. የመምህራን ምግበ ምላሽ ሁኔታ መግለጫ.......................................... 49
ሰንጠረዥ 11. የመምህራንን አተገባበር ስልት የሚያሳይ መግለጫ ......................... 50
ሰንጠረዥ 12. በክፍል ውስጥ የሚቀርበውት የፅህፈት ትምህርት ተግባራት የድግግሞሽ መጠንን የሚያሳይ መግለጫ ........................................ 52

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የዕህፈት ክሂልን ለማስተማር የቀረቡትን ስነዘዴዎች አተገባበር መፈተሽ ሲሆን፣ በመርሀ ትምህርቱ ዕህፈትን ለማስተማር ተግባር ላይ የዋሉት ስነዘዴዎች በደረጃው ከተዘጋጁት የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍቱ ጋር ያላቸውን ተደያኝነት፣ በክፍል ውስጥ ያላቸውን አተገባበር፣ የመምህራንንና የተማሪዎችን ሚና መቃኘትና የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመፈተሽ ከደረሰበት ውጤት ተነስቶ የመፍትሔ ሀሳቦችን መጠቆም ነው:: ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ ምርምርን (qualitative research) ሲሆን፣ አቀራረቡም ገላጭ (Descriptive) ነው:: የአማራ ክልልን በአመቺ ናሙናነት በመምረጥ በክልሉ ከሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል አራቱ የደምበጫ፣ የአዲስ አምባ፣ የዋድና የአርበኞች ትምህርት ቤቶች በነሲብ የዕጣ ናሙና ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪዎች ሆነዋል:: በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ስራ ላይ የዋሉት ምልከታ፣ የሰነድ ምርመራና የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ፣ በመከታተያ ዝርዝር (Checklist)፣ በማስተማሪያ መሳሪያዎችና በመምህራን በተሞላ የፅሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው በመርሀ ትምህርቱ ወስጥ ዕህፈትን ለማስተማር የቀረቡት ተግባራት በአብዛኛው የውስንና መር ዕህፈት (Controlled and Guided Writing) መሆናቸው ታውቋል:: የመምህሩ መምሪያዎችም በአግባቡ አለመዘጋጀታቸውን መረጃዎች ጠቁመዋል:: መምህራኑ የክሂል ትምህርቱን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ እንዲለማመዱ፣ የፃፉትን እንዲከልሱና እንዲገመግሙ አላደረጉም:: የመምህራን ምግበ ምላሽ (Feedback) መጠነኛና ቃላዊ ነው:: በክፍል ውስጥ ያለው የመማር ማስተማር ሂደትም ተማሪዎችን ያሳተፈ አይደለም:: በአጠቃላይ መምህራኑ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ስነዘዴዎች በአግባቡ ሲያከናውኑ አልታዩም:: ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም የመፍትሄ ሐሳቦች ቀርበዋል:: እነሱም የመምህሩ መምሪያዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው በአግባቡ እንዲዘጋጁ ቢደረግ፣ ዕህፈትን የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ያሳተፈ ቢሆን፣ መምህራን ለተማሪዎች የፅሁፍ ስራ ተገቢ እርማትና ማስተካከያ ቢሰጡና ለመምህራን ሙያዊ ስልጠናዎች የሚሰጡበት ሁኔታዎች ቢፈጠሩ የሚሉት ናቸው::

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

አንድን የቋንቋ ትምህርት መርሀ ግብር ከዳር ለማድረስ የመርሀ ትምህርት አስፈላጊነት የሚያከራክር አይደለም። ዓለም (1997፣180) የመርሀ ትምህርትን አስፈላጊነት ሲገልጹ፣ "አንድን የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም በአግባቡ አቅዶ በአግባቡ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ መርሀ ትምህርት መንደፍ የግድ አስፈላጊ ይሆናል።" ይላሉ። Yalden(1987፣86) በበኩላቸው Widdowson(1984)ን በመጥቀስ መርሀ ትምህርት የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት ለመቆጣጠርና በሚገባ መዘጋጀቱን ለማሳየት ይረዳል በማለት ይገልፃሉ።

መርሃ ትምህርት አንድን የቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ከዳር እንዲደርስ የሚያስችሉትን መሰረታዊ ነገሮች የያዘ ነው። የሚያካትታቸው ፍሬ ነገሮችም የትምህርቱ ዓላማዎች፣ ለትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች፣ ማከናወኛ ጊዜያቶች፣ የማስተማሪያ ስልቶች፣ ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችና የማምገማ ስልቶች ናቸው (Dubin እና Olshtain 1986፣27)።

በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከሚካተቱት መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ የቋንቋ ትምህርቱ የማስተማሪያ ዘዴ አንዱ ወሳኝ አካል ነው። የማስተማር ስነ ዘዴ ንድፈ ሀሳብ፣ መምህሩ ለተማሪው የቋንቋውን ትምህርት በማስተማሪያ መሳሪያዎች አማካኝነት በስርዓት ተግባራዊ የሚያደርግበት የክፍል ውስጥ ተግባርም ነው። በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ዋና ክሂሎችንና ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር የቀረቡት ስነዘዴዎች በደረጃው በሚገኙ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ያላቸው አተገባበር ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ስለዚህ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ስነ ዘዴዎች መምህሩ ሊተገብራቸው በሚችል መልኩ ሊቀርቡ ይገባል። በመማር ማስተማር ሂደቱ የተማሪዎች ሚና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ትምህርታዊ ዝግጅቱ ተማሪዎችን መሰረት ባደረገ ሁኔታም መቅረብ ይኖርበታል Richards (2001፣51)፣ Richards እና Rodgers (1985፣10-11፣32)፣ Richards (1990፣11) እና Brown (1994፣159) ።

በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ በይዘት ከሚካተቱት ክሂሎች መካከል የጽሕፈት ክሂል ትምህርት አንዱ ነው። Harmer (1991፣16) ፣ Ur (1996፣26) እና Richards (1990፣101) ገለፃ፣ ይህ

ክሂል ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ የሚዳብር ሳይሆን በመደበኛ አውድ ውስጥ የሚቀርብ በመሆኑ በክሂሉ በተከታታይ መገልገልን በመማሪያ ክፍልም ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጭ ብዙ ጊዜ ወስዶ መለማመድን ይጠይቃል። ለተግባራዊነቱም ተገቢ የሆነ የመማር ማስተማር ክንውንን ይፈልጋል።

የዕህፈት ትምህርት ውስብስብ በመሆኑ አብዛኞቹ የቋንቋ ተማሪዎች የአፍ መፍቻም ይሁን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከትምህርት ቤት ሲወጡ በቂ የሆነ የዕህፈት ችሎታን አያዳብሩም። ይህ ችግር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ጐልቶ የሚታይ በመሆኑ ተማሪዎች በኮሌጅ የቋንቋ ትምህርቶች ውስጥ ተካተው የሚሰጡ የድርሰት ትምህርቶችን በከፍተኛ ፍራቻና ጭንቀት ስለሚመለከቷቸው በእጅጉ አስቸጋሪዎችና ረዘም ያለ ጊዜን የሚጠይቁ ሆነው ይታያሉ (Richards 1990፤100)። ባዬ (1987፤8) እና Nunan (1989፤39)ም በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ።

በሀገር ውስጥ በሚገኙት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለያዩ ጊዜያት ተመርቀው የወጡ ተማሪዎች የመጀመሪያም ይሁን የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በዕህፈት ትምህርት ዙሪያ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል። ከእነዚህ አጥኚዎች መካከልም ማረው ዓለሙ (1987)፣ ሠለሞን ተሰማ (1987)፣ ስዩም ከበደ (1988)፣ ሰሎሞን ዮሐንስ (1991)፣ ጽጌ ታደሰ (1992)፣ ሰይድ ይመር (1993)፣ ወዘተ. ይገኙበታል። በጥናታቸው ከደረሱበት ውጤት በመነሳትም የየበኩላቸውን የመፍትሔ ሀሳቦች ጠቁመዋል።

እነዚህ ጥናቶች የዕህፈት ክሂል ትምህርትን ለማስተማር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች አደረጃጀት ብቁ ሆኖ አለመገኘት፣ የይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ ሆኖ ያለመቅረቡና የመምህራን ዕህፈትን የማስተማር ስነ-ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ስትራቴጅ የሚያሳድግ ሆኖ አለመገኘቱን የገለፁ ቢሆንም፣ በአንፃሩ በቡድን ድርሰት ማፃፍ፣ የቢጤ እርማትና በሂደታዊ ዘዴ ዕህፈትን ማስተማር ለክሂሉ መዳበር ጠቃሚዎች ሆነው መገኘታቸውን የጠቆሙ ናቸው።

እስከአሁን የተካሄዱት ጥናቶች ትኩረት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የዕህፈት ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴዎች የዳሰሱ እንጅ ለቋንቋ ትምህርቱ መነሻ ወይም መሰረት የሆነውን መርሀ ትምህርት መሰረት ያደረጉ አይደሉም። የዚህ ጥናት አቅራቢም ከላይ የተጠቀሱትን የጥናት ግኝቶች መነሻ በማድረግ ተማሪዎች ክሂሉን በአግባቡ አዳብረው

ያለመገኘታቸው ምክንያት ምን አልባት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ባሉ መርሀትምህርቶች የዕህፊት ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎች በአግባቡ ባለመተግበራቸው ይሆን? በማለት ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ የዕህፊትን ክሂል ለማስተማር የቀረቡትን ስነ-ዘዴዎች አተገባበር ለመፈተሽ አሰበ::

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራ ክልል ለሚማሩ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን (ከ5-8ኛ ክፍሎች) ተማሪዎች በ1997 ዓ.ም. በተዘጋጀው (ተግባራዊ እየሆነ በሚገኘው) የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የዕህፊት ክሂልን ለማስተማር የቀረቡትን ስነ ዘዴዎች አተገባበር መፈተሽ ነው:: በመሆኑም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል::

- በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የዕህፊት ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት ስነዘዴዎች ከመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍቱ ጋር ያላቸውን ቁርኝት መመርመር፣
- መምህራን በመርሀ ትምህርቱ ላይ የሰፈሩትን የዕህፊት ክሂል የማስተማር ስነዘዴዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸውን መፈተሽ፣
- በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት ስነ ዘዴዎች አኳያ የዕህፊት ክሂልን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መገምገም እና
- በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የዕህፊት ክሂልን ለማዳበር ከቀረቡት ስነ ዘዴዎች አኳያ የተማሪዎችን ሚና መቃኘት ነው::

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት የዕህፊት ክሂልን ለማስተማር የቀረቡትን ስነ ዘዴዎች አተገባበር መፈተሽ ነው:: ለክሂሉ መዳበር የተመረጡትን የመማር ማስተማር ክንውኖች (ስነ-ዘዴዎች) በመመልከት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመገምገም በክሂል ትምህርቱ አተገባበር ላይ ያሳደሩትን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመግለፅ ይሞክራል:: በመሆኑም የሚከተሉትን ፋይዳዎች ከማስገኘት አኳያ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል::

- በጥናቱ ውጤት በመታገዝ በመርሀ ትምህርት፣ በመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅት፣ እንዲሁም በመምህራን ስልጠና ወቅት የዕህፊትን ክሂል ለማስተማር ስነ ዘዴ መረጣና ትግበራ ሊደረግ የሚገባውን ትኩረት ለመጠቆም ያስችላል ተብሎ ይገመታል::

- በደረጃው ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የዕሁፌት ክሂል የማስተማርን ስነዘዴ ምንነትና አተገባበር በማስተዋወቅ በኩል እገዛ ሊያደርግ ይችላል።
- በደረጃው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያለውን ዕህፌትን የማስተማር ስነዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን በማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ ደካማ ጎኖች ካሉ የማሻሻያ አቅጣጫ ሊጠቁም ይችላል።
- በመስኩ ለሚካሄዱ ሌሎች ጥናቶች መነሻና አቅጣጫ ጠቋሚ ሊሆን ይችላል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት የሚመለከተው በ1997 ዓ.ም. ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን (ከ5ኛ -8ኛ ክፍሎች) በአገር አቀፍ በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ የዕህፌት ክሂልን ለማስተማር የቀረቡትን ስነ ዘዴዎች አተገባበር መሬቱሽ ነው። በመሆኑም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ዕህፌትን የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች ከመማሪያ መፃህፍቱ ጋር ያላቸውን ተያያዥነትና በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህራንና ተማሪዎችን ሚና ይዳስሳል። ይሁን እንጅ ጥናቱ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ዕህፌትን ለማስተማር የቀረቡትን ይዘቶች አደረጃጀት አይመለከትም። በአንፃሩ ክሂሉን ለማስተማር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች ከስነዘዴው አኳያ ያላቸውን አተገባበር በማየት ያሳደሩትን አወንታዊም ይሁን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመመልከት ያለመ ነው።

## ክፍል ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

### 2.1. የመርሀ ትምህርት ምንነት

በመርሀ ትምህርት (Syllabus) እና በስርዓተ ትምህርት (Curriculum) መካከል ያለው ልዩነት አከራካሪ ሁኔታ ይታይበታል (Nunan፣ 1988፣5):: ይሁን እንጅ ሁለቱን ለየብቻ ለያይቶ መግለጹ፣ እያንዳንዳቸው ለሚሰጡት አገልግሎት ትኩረት ለመስጠት ያስችላል (Dubin እና Olshtain፣ 1986፣36)::

"ስርዓተ ትምህርት ምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ Nunan (1988፣6)፣ Allen (1986)ን ጠቅሰው እንደገለጹት፣ ለትምህርት እቅድ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ እንደ ትምህርት ፍልስፍና፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ያሉ ውስብስብ ሁኔታዎችን ያካተተ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው:: እንዲሁም Dubin እና olshtain (1986፣35) ስርዓተ ትምህርት አጠቃላይ የትምህርት ግብ ዝርዝርንና ትምህርታዊ ወባህላዊ ፍልስፍናን የያዘ ሲሆን ከአጠቃላይ የቋንቋ ባህሪና የቋንቋ መማር ትውረት ጋር ተዋህዶ የሚተገበር ሰነድ ነው:: ስርዓተ ትምህርት የሀገራዊና የፖለቲካዊ ፈለግ ነፀብራቅም እንደሆነ እነዚሁ ምሁራን አክለው ይገልፃሉ::

በአጭሩ ስርዓተ ትምህርት አጠቃላይ የትምህርት ግብን፣ ፍልስፍናን፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ከሀገሪቱ ፖለቲካዊና ሀገራዊ ፈለግ ጋር አጣምሮ የሚይዝ ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ነው:: ለበርካታ መርሃ ትምህርቶች ቀረፃ መሰረትም ይሆናል:: ቀጥሎ ደግሞ የመርሃ ትምህርትን ምንነት እንመልከት::

መርሃ ትምህርት ለማስተማር መማር ክንውን የተዘጋጁ ዝርዝር አላባውያንን የያዘ፣ የስርዓተ ትምህርቱን ፍልስፍና ደረጃ በደረጃ ለመተግበር ታልሞ የሚዘጋጅ ዕቅድ ነው (Dubin እና Olshtain፣ 1986፣ 35):: በተመሳሳይ ሁኔታ Breen (1987፣82) መርሀ ትምህርት በመማር ማስተማር ክንውን አማካይነት ከግብ እንዲደርስ የታሰበው ይዘት እቅድ እንደሆነ ይገልፃሉ::

መርሃ ትምህርት፣ በመርሃ ትምህርት ቀራጩና በመምህሩ መካከል ሰጋራ አላማ የሚውል ዝርዝር እቅድ ማስተላለፊያ ሞተር አድርገው የሚያዩትም አሉ:: እንደ Yalden (1987፣10) አገላለጽ፣ መርሃ ትምህርት መምህሩ፣ በመርሃ ትምህርት ቀራጩ እገዛ፣ በተማሪዎች ፍላጎትና አላማ መካከል ያለውን ተገጣጥሞ፣ በክፍል ውስጥ ተማሪዎቹን እያስማመደ፣ ከግብ የሚያደርስበት መሳሪያ ነው::

ይህንን ሃሳብ Dubin እና Olshtain (1986፣ 36) መርሃ ትምህርት፣ ፖሊሲ ቀራጩ ለመምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለመማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆችና ለፈተና አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት፣ የትምህርቱን መርሃ ግብር በተመለከተ መረጃ የሚያስተላልፍበት መሳሪያ ነው በማት ይደግፉታል::

ስለዚህ መርሃ ትምህርት በመማር ማስተማር ትግበራ አማካኝነት ከግብ እንዲደርስ የታቀደውን ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት ዓላማ አካቶ የያዘ የስርዓተ ትምህርት ንኡስ ክፍል ነው::

### 2.1.1. የመርሀ ትምህርት አስፈላጊነት

የመርሀ ትምህርትን አስፈላጊነት አለም (1997፣180) ሲገልጹ፣ "አንድን የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም በአግባቡ አቅዶ በአግባቡ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ መርሀ ትምህርት መንደፍ የግድ አስፈላጊ ይሆናል" ይላሉ:: Yalden (1987፣86) በበኩላቸው Widdowson (1984)ን በመጥቀስ መርሀ ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ሂደቱን ለመቆጣጠርና የአቀራረቡ ዘዴ ብቃት ባለው ሁኔታ መዘጋጀቱን ለማሳየት ይረዳል በማለት ይገልፃሉ::

Hutchinson እና Waters (1987፣83-84)ም የመርሀ ትምህርትን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ይገልፁታል፤

1. ቋንቋ ውስብስብ የሆነ ዘርፍ ነው:: ስለሆነም በአንድ ጊዜ መማር አይቻልም:: ስለዚህ ልንቆጣጠረው በምንችልበት መልኩ መለያየት አለብን:: የተለያዩ የቋንቋውን የእውቀት ክፍሎች ለማቅረብ፣ መማሪያ መፃህፍትን ለማዘጋጀትና የትምህርት ጊዜን ለመወሰን የተግባር መሰረት ነው::
2. መርሀ ትምህርት ከተግባራዊ ጠቀሜታው ባሻገር ለመምህሩና ለተማሪው የሞራል ድጋፍ በመስጠት የቋንቋ ትምህርቱን በቀላሉ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል::

3. መርሀ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች ወዴት እንደሚሄዱ ሀሳብ መስጠት (ግንዛቤ ማስጨበጥ) ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚጠቀሙበትም ያመለክታል::
4. መርሀ ትምህርት፣ እጅግ በጣም ጠቃሚ ተደርጎ የተወሰደው የቋንቋ ትምህርት ክፍል ምን እንደሆነ በሚገባ ይገልፃል::
5. መርሀ ትምህርት የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመምረጥና ለማዘጋጀት ይረዳል::
6. በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ወጥነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት ያግዛል::
7. ማስተማር፣ ተማሪው በአንድ የተወሰነ ነገር ላይ አውቀት እንዲጨብጥ ይመራዋል ተብሎ ይታሰባል:: ስለሆነም መርሃ ትምህርት የተማሪውን ስኬትና ውድቀት መገምገሚያ መስፈርት ያስቀምጣል::

2.1.2. የመርሃ ትምህርት አተገባበር ፍተሻ

የመርሀ ትምህርት አተገባበርን አስመልክተው Lewy (1977፣22)፣ Pratt (1980፣343)፣ Oliva (1988፣115) ፣ Fullan (1992፣37) እና Pasner (1992፣186) ሲገልፁ፣ አንድን የቋንቋ ትምህርት ዝግጅት መሰረት አድርጎ የቀረበ መርሀ ትምህርት በተዘጋጁለት የማስተማሪያ መሳሪያዎች አማካይነት እየታገዘ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ክንውን ተግባራዊ ሲሆን የመርሀ ትምህርት ትግበራ ይባላል ይላሉ::

የመርሀ ትምህርት ትግበራ ፍተሻ፣ በዕቅድ ደረጃ የሰፈረው አላማ ወደ ተግባር እንዴት ይለወጣል? እንዴትስ ውጤታማ ይሆናል? የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚመረመሩበት ነው:: ማለትም በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ምን ታቀደ? የዕቅዱ ተግባራዊነትስ ምን ያህል ነው? በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውኑ ምን ይመስላል? በትግባራው ሂደት የሚታዩ ችግሮች ምንድናቸው? መፍትሄዎቹስ ምን ምን ናቸው? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳትና ምርምር በማካሄድ ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት መሆኑን Oliva (1988፣463) ፣ Doll (1977፣ 367) ፣ Ornstein እና Hunkins (1988፣250-251) ያስረዳሉ::

ከላይ የመርሀ ትምህርትን አተገባበር ፍተሻ በተመለከተ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረበው የመማር ማስተማር ክንውን (ስነ-ዘዴ) ለአንድ የቋንቋ ትምህርት አተገባበር አንዱ ወሳኝ አካል መሆኑን ነው:: ለዚህም ይመስላል Nunan

(1988፡122)፣ Richards (1990፡11) እና Brown (1994፡159) የመርሃ ትምህርት ትግበራ በክፍል ውስጥ በሚደረግ የመማር ማስተማር ክንውን ላይ የሚያተኩር እንቅስቃሴ ነው በማለት የሚገልፁት::

## 2.2. የስነ-ዘዴ ምንነት

የማስተማር ስነ-ዘዴ ትውፊታዊ መሰረት ያለው፣ መምህሩ ለትምህርት የቀረበውን የቋንቋ ይዘት በማስተማሪያ መሳሪያዎች አማካኝነት እየታገዘ ስርዓቱን ጠብቆ ተግባራዊ የሚያደርግበት የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ መሆኑን Richards እና Rodgers (1985፡10-11)፣ Richards (1990፡11) እና Brown (1994፡159) ይገልፃሉ:: በተጨማሪም Richards እና Rodgers (1985፡32) የስነ- ዘዴን ምንነት የሚወስኑ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች (elements) መኖራቸውን ይጠቁማሉ:: እነሱም:- ትውፊታዊ አቀራረብ (approach)፣ ንድፈ ትምህርት (design) እና ስልተ- ትግበራ (procedure) ናቸው:: Richards (1990፡11) በበኩላቸው የስነ ዘዴን ምንነት የሚገልጹ ሌሎች ተጨማሪ ንዑስ ዘርፎች መኖራቸውን በማመልከት ቁጥራቸውን ወደ አምስት ከፍ ያደርጉታል:: እነሱም:- መርሀ ትምህርቱ መሰረት ያደረገው ትውፊታዊ አቀራረብና አመለካከት፣ የመምህሩ ሚና፣ የተማሪው ሚና፣ በክፍል ውስጥ የድርጊቶች፣ የክንውኖችና የመልመጃዎች አቀራረብ ስልትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሚና ናቸው::

ከላይ የስነ ዘዴን ምንነት አስመልክቶ ከቀረቡት የምሁራን ገለፃዎች መረዳት የሚቻለው፣ ስነ ዘዴ የቋንቋ ትምህርቱ መርሀ ግብር ከመነሻው ይዘት የተነሳውን የትምህርት ዓላማ መሰረት በማድረግ መምህሩን በማስተማሪያ መሳሪያዎች ተጠቅመው የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት በክፍል ውስጥ ለተማሪው የሚያቀርቡበት ስልት መሆኑን ነው::

## 2.3. የፅህፈት ምንነት

በመስኩ ልምድ ያላቸው ብዙ ምሁራን ስለ ፅህፈት ትምህርት ካላቸው አተያይ በመነሳት መፃፍ (Writing) የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ በተለያየ መንገድ ይገልፁታል:: እንደ Byrne (1988፡3) አገላለፅ፣ መፃፍ ማለት የቋንቋውን የድምፅ ምልክቶች በወረቀት ላይ ማስፈር ነው ሊባል ይችል ይሆናል:: ይሁን ዕንጅ ፊደላትን አቀናጅቶ ከማስቀመጥ ባሻገር በአእምሮ ያለውን ሀሳብ በፅሁፍ መልክ አቀነባብሮ ለአንባቢ የማግለፅም ሂደት ጭምር ነው:: Pincas (1982፡v)ም መፃፍ

ተግባቦትን ለመፍጠርና ራስን ለመግለፅ የሚያስችል መሳሪያ ነው በማለት ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ያጠናክሩታል።

በሌላ በኩል Nunan (1989፣36) Bell እና Burnaby (1984)ን ጠቅሰው እንደሚገልፁት ፅህፈት እጅግ በጣም ውስብስብ የሆነ የአእምሮ ተግባር ሲሆን ተግባሩም በአንድ ጊዜ በርካታ ነገሮችን እያሰቡ ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ሂደት ነው። ይዘቱን፣ የአፃፃፍ ስልቱን፣ የአረፍተ ነገር መዋቅሩን፣ ቃላቱን፣ ስርዓተ ነጥቡን፣ ወዘተ. ተቆጣጥሮ መጻፍን ይጠይቃል። ከዚህ ባሻገርም ፀሀፊው ሀሳቦችን በማዋቀርና በማዛመድ አንድነትና ግጥምጥምነት ያለው ፅሁፍ ማቅረብ መቻልን የሚጠይቅ ክሂል ነው ይላሉ። Raimes (1983፣14) በበኩላቸው "የፅህፈት ክሂል በቅደም ተከተል የተደራጁና እርስ በርስ በሀሳብ የተሰናሰሉ ተከታታይ ዐረፍተ ነገሮችን በማፍለቅ፣ ሀሳብን በፅሁፍ መግለፅ የሚያስችለን ክሂል ነው" በማለት ከቀደመው ሀሳብ ጋር ይስማማሉ።

ፅህፈት በቀ ዝግጅትንና መማርን የሚጠይቅ (በመደበኛ አውድ ውስጥ የሚቀርብ) ነው። ማንኛውም አካሉና አእምሮው ጤነኛ የሆነ ሰው መደበኛ ባልሆነ መንገድ በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር ይችላል። ነገር ግን ሁሉም ሰው በቋንቋው እንዴት መፃፍ እንዳለበት የግድ መማር አለበት (Nunan 1989፣36)።

ፅህፈት ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት በተከታታይ መለማመድን የሚጠይቅ የክሂል አይነት መሆኑን Harmer (1991፣16) ፣ Ur (1996፣26) እና Richards (1990፣101) በተመሳሳይ ሁኔታ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። ዓለም (1995፣14)ም የምሁራኑን ሀሳብ በመደገፍ የሚከተለውን ሀሳብ ገልፀዋል።

> *... ፅህፈት ሀሳብን በትክክል ለማስተላለፍ ከድምፅ ጀምሮ ያሉት ቃላትና አረፍተ ነገሮች በቋንቋው ስርዓት መሰረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀውና ተቀናብረው የሚቀርቡበት ነው። እንግዲም መልዕክቱን በትክክል የሚረዳው የቋንቋውን ስርዓት የጠበቀ እንደሆነ ብቻ ነው። በዚህ መንገድም ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። ፅሁፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑም በተደጋጋሚ በሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፤ ይዳበራል፤ይበለፅጋል።*

በአጠቃላይ ፅህፈትን አስመልክተው ከቀረቡት የምሁራን ስራዎች መረዳት የሚቻለው የፅህፈት ክሂል የታላሚውን ቋንቋ የድምፅ ወኪሎች በትክክል ለይቶ በማወቅ በአእምሮ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በወረቀት ላይ የመግለፅ ሂደት መሆኑን ነው። ትምህርቱ በመደበኛ አውድ ውስጥ

የሚቀርብ በመሆኑም ክሂሉን ለማዳበር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በተጨማሪ መገንዘብ ይቻላል።

2.3.1. የመፃፍ ክሂል መልመጃዎች ዓላማ

በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ የሚጠበቁትን ክሂሎችና ዕውቀቶች ማስጨበጥ ነው። የዕህፌት ክሂልም ከቋንቋው መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ በመሆኑ የራሱ የሆኑ ዓላማዎች ይኖሩታል። እንደ Raimes (1983፤4) ገለፃ በአረፍተ ነገር ደረጃም ቢሆን በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ክፍሎች ብዙ የዕህፌት ትምህርት መልመጃዎች ይሰጣሉ። እነዚህ መልመጃዎች የተማሪዎችን የአረፍተ ነገር አወቃቀር፤ የአገባብና የቃላት ምርጫ ችሎታ ያጠናክሩላቸዋል። ከዚያም አልፎ ከአንባቢ ጋር ለመግባባት፤ ከፊት ለፊት ከሚካሄድ ተግባቦት ውጭ (በፅሁፍ) ሀሳብን ለመግለፅ፤ አንድን ዕሁፍ አንብቦ እውቀትን ለማግኘት፤ አንድን የህይወት ተሞክሮ ለቀጣይ ትውልድ መዝግቦ ለማቆየትና በቋንቋው ለተፃፉ የፅሁፍ ስራዎች ተማሪዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ለማስቻል እገዛ ያደርጋል።

በሌላ በኩል እነ Attkins (1996፤114) የመፃፍ ክሂል መልመጃ ሁለት ዓላማዎች እንዳሉት ይገልፃሉ። አንደኛው ዓላማ የተማሪዎችን የቋንቋ እውቀት ማለትም የቃላትና የሰዋስው ችሎታ ለማጠናከር ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ ተማሪዎች ተግባቦታዊ የመፃፍ ክሂልን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ነው።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የዕህፌት ትምህርት መልመጃዎች አላማ የተማሪዎችን የቃላትና የሰዋስው ዕውቀትን በማጠናከር በፅሁፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል ነው። ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር መግለፅ እንደሚችሉ ሁሉ በአእምሮአቸው የሚመላለሱትን ሀሳቦች በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው መዳበር አለበት። ይህም ከሚያዳምጡትና ከሚያነቡት ተነስተው ለግንዛቤ የሚረዳቸውን ሀሳብ መዝግቦ ለመያዝ ይጠቅማቸዋል። በሂደቱም የቋንቋውን ምልክቶች ከመለየት ባሻገር ሰዋስዋዊ ስርዓቱን እንዲያውቁት ያግዛቸዋል።

2.3.2. የዕህፌትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

የዕህፌትን ትምህርት ዓላማ በቀላሉ ከግብ ለማድረስ አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖራቸውን ምሁራን ይገልፃሉ። እንደ Barr እና Barbara (1997፤17) ገለፃ ዕህፌት ባሉት ባህርያቱ የተነሳ ውስብስብና በቀላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊዳበር የሚችል ክሂል ባለመሆኑ

ብዙ ጊዜ ወስዶ ልምምድ ማድረግ የሚጠይቅ ነው:: የዕህፈት ክሂል በባህርይው የተለያዩ ክሂሎችን የሚጠይቅ በመሆኑ አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋ ለፈቱትም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑት ተማሪዎች ለሁሉቱም በእኩል ደረጃ አስቸጋሪ እንደሆነ Kroll (1990፣141) በበኩላቸው ያስረዳሉ:: ሌሎች ዕህፈትን አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉት ባህርያቱ ደግሞ ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊና አእምሮአዊ ገፅታዎቹ ናቸው Hedge (1988፣7)፣ Pincas (1982፣18)፣ Raimes (1983፣11) እና Reid (1993፣113):: እነዚህን ባህርያት ከዚህ በታች በአጫጭሩ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል::

### 2.3.2.1. ሥነ-ልቦናዊ ባህርይ

በዕህፈት ክሂል የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚገፈው ዕሁፍ ለማን እንደሆነ ወይም አንባቢውን ማሰብ የማይቀር ጉዳይ ነው:: መልዕክቱ ለአንባቢው በትክክል እንዲደርሰው ለማድረግ ደግሞ ፀሀፊው በሀሳብ መውጣት መውረድ ስላለበት ይጨነቃል:: "የዕህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁና ቁና መተንፈሻ፣ እግራቸውን ማፋተጊያና እርሳሳቸውን ማኘኪያ የስቃይ ጊዜ ነው" በማለት ዕህፈት ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ Hedge (1988፣5) ይገልፃሉ:: ከዚህ ሀሳብ በመነሳትም የዕህፈት ክሂል ውስጣዊ ጭንቀት የሚፈጥር (ስነልቦናዊ ችግር) መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

### 2.3.2.2. ሥነ- ልሳናዊ ባህርይ

ሥነ-ልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድ ቋንቋ ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታው ይጠናበታል:: በዕህፈት ትምህርት ረገድም የሥነ-ልሳን እውቀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው:: ምክንያቱም ሀሳብን በዕህፈት አማካይነት በትክክል ማግለፅ የሚቻለው የቋንቋውን ሥርዓት ጠንቅቆ ማወቅን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው:: ተቀባይነትና ተነባቢነት ያለው መልዕክት ለማስተላለፍ የግድ የቋንቋውን ህግጋት ማወቅ ያስፈልጋል:: ይህ ደግሞ የቋንቋውን ስርዓት ከአጠቃቀሙ ጋር አስማምቶ በማቅረብ በዕሁፍ መግባባት ያስችላል:: ይህን ዕውቀት ለማዳበርም በንግግር ወቅት ትኩረት የማናደርግባቸው ነገር ግን በዕህፈት ጊዜ ሲተኮርባቸው የሚገቡ ነገሮች መኖራቸውንም መፈተሽ ይገባል (Hedge 1988፣19)::

### 2.3.2.3. አእምሮታዊ ባህርይ

ዕህፈት በከፍተኛ ደረጃ የአእምሮን እንቅስቃሴ (በሀሳብ መውጣት መውረድ) የሚጠይቅ ትምህርት ነው ማለት ይቻላል:: የዕሁፍ ሥራ የግንዛቤን መዳበር ይጠይቃል:: Moore

(1995፣13) "መፃፍ ማለት ማሰብ ማለት ነው" በማለት ሳይታሰብበት የሚከናወን የፅህፈት ተግባር አለመኖሩን ይገልፃሉ:: Reid (1993፣116) በበኩላቸው "የፅህፈት ትምህርት እጅን፣ ዓይንንና አእምሮን በማስተባበር በተገቢ ትዕምርታዊ ወኪሎች አማካይነት የራስን ወይም የጋራን ገጠመኝ የማካፈል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው" በማለት አእምሮ ለፅህፈት ትምህርት ክንውን ያለውን አስተዋፅኦ በአፅንኦት ይገልፃሉ::

በአጠቃላይ የፅህፈትን ትምህርት አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች በመነሳት ክሂሉን ለማስተማር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግን የሚጠይቁ ነገሮች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል:: የተማሪዎችን የስነ ልቦና ሁኔታ በቋንቋው ያላቸውን የዕውቀት ደረጃና የአእምሮ ብስለታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክሂሉ መዳበር የሚቀርቡትን ይዘቶች ተገቢ በሆነ ስነ-ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

## 2.4. የፅህፈት ክሂልን የማቀድና የማስተማር መርሆዎች

ተማሪዎች በፅሁፍ አማካይነት ሀሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ የመግለፅ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ፣ መምህሩ የፅህፈትን ክሂል በሚያዳብሩና የሰዋስውና የቃላት ችሎታን በሚያጠናክሩ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ትምህርቱን ማቅረብ እንዳለበትና በትግበራ ሂደቱም የሚከተሉትን መርሆዎች ማስታወስ ተገቢ እንደሚሆን እነ Attkins (1996:11) ይገልፃሉ::

1. የመፃፍ ክሂል በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የሚለማመዱት መሆን አለበት:: በክፍል ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋስውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች መልመጃዎችን በመስራት የመፃፍ ክሂላቸውን ማዳበር አለባቸው::
2. በክፍል ውስጥ የሚተገበሩት መልመጃዎችም አስደሳችና ለመፃፍ የሚያነሳሱ፣ ዓላማ ያላቸው፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃ እና ልምዳቸውን ያገናዘበ፣ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልፁ የሚያስችል፣ ለውይይትና በቡድን ለመፃፍ ተስማሚ የሆነ፣ ግልጽ መመሪያዎች ያሉትና ተማሪዎች እንዲያቅዱ፣ እንዲያረቁና እንዲከልሱ የሚያበረታታ እንዲሆን ያስፈልጋል::
3. ተማሪዎች እንዲፅፉ ከመነገራቸው በፊት ተማሪዎችን ማነሳሳት::
4. ተማሪዎች በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን እንዲሰሩ ከተፈለገ በቅድሚያ በግልፅ ሊነገራቸው ይገባል::
5. መልመጃዎች ሲከናወኑ መቆጣጠር::

6. በቁጥጥር ወቅት ጠቃሚና ገንቢ ምግበ ምላሽ (Feedback) መስጠት:: ለምሳሌ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ያሉትን በመለየት ድጋፍ መስጠት፤ ማድነቅና ማበረታታት፤ ስህተቶቻቸውን ማረም፤ አስተያየት መስጠት:: ተማሪዎች መፃፍ የሚፈልጉባቸውን ሀሳቦች በመቀበል በተቻለ መጠን ግልፅና ትክክል በሆነ መንገድ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት::

7. ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው ከተፈላጊው ደረጃ ላይ ከደረሰ፣ ተማሪዎችን ሊፈትኑ የሚችሉ አዝናኝና ልቅ ያልሆኑ ውስን መልመጃዎችን ማቅረብ እና

8. ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲገመገሙ ማበረታታት:: የፃፉትን ፅሁፍ ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል (እነ Attkins 1996፣11)::

## 2.5. የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች

የፅህፈትን ትምህርት ለማስተማር ቀላል መንገድ ባይኖርም የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል Raimes (1983፣5-10) ያስረዳሉ:: እኒሁ ምሁር አያይዘው ሲገልፁም ከተገደበ የጽህፈት አፃፃፍ አንስቶ በቅርብ ጊዜ እየተለመደ ወዳለው ሂደታዊ አቀራረብ ድረስ የተለያዩ የጽህፈት ማስተማሪያ መንገዶች በስራ ላይ የዋሉ መሆናቸውን ይገልፃሉ:: Richards (1990፣106)፣ Byrne (1988፣21-23) እና Nunan (1989፣36)ም በበኩላቸው የተለያዩ የጽህፈት ትምህርት አቀራረቦች መኖራቸውን በስራዎቻቸው ውስጥ ገልፀዋል:: እነዚህ ዘዴዎች (አቀራረቦች) ቀጥለው ይቀርባሉ::

### 2.5.1. በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ (Product Focused Approach)

ይህ ዘዴ ከመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች የመጀመሪያው እንደሆነ Nunan (1989፣36) ይገልፃሉ:: አያይዘውም በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ የሚያተኩረው ተማሪዎች በጻፉት የመጨረሻ ስራ ላይ ነው:: ዓላማው ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው የጽህፈት ትምህርት ተግባራት ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ ነው:: በመሆኑም የጻፏቸው ነገሮች ከስዋስው፣ ከአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ ከሀሳብ ቅንጅት፣ ከስርዓተ ነጥብ፣ ከግልጸት ወዘተ አኳያ ይገመገማሉ::

በሌላ በኩል Richards (1990፣106) በውጤት ላይ ያተኮረ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ በተለያዩ አንቀፆችና ፅሁፎች የመዋቅር ቅንብር ስልት ላይ ተማሪዎች ልምምድ እንዲያደርጉ ይመራቸዋል ይላሉ:: ምክንያቱንም ሲገልፁ የዘዴው ትኩረት ተማሪዎች ስህተት የሌለበት ፅሁፍ እንዲፅፉ ማስቻል ስለሆነ የተፈለገውን የፅሁፍ ቅርፅ እንዲያጠኑ በማድረግ ወደፊት ቃዘው በሚፅፉት ነገር ላይ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋቸዋል ይላሉ::

እንደ ምሁራኑ ገለፃ ይህ ፅህፈትን የማስተማሪያ ዘዴ የተወሰነ ቅደም ተከተል አለው:: አብዛኛውን ጊዜ ለተማሪዎች ሞዴል አረፍተ ነገርን ደግመው እንዲፅፉ የሚጋብዝ መልመጃ በመስጠት ይጀምራል:: ከዚያም በደረጃ ከፍ ወዳለው አንቀፅን ወደ መፃፍ ያሸጋግራል:: አንዳንድ ጊዜም ከአንድ አረፍተ ነገር ቅርፅ ወደ ሌላ አይነት የአረፍተ ነገር ቅርፅ የመቀየር ተግባራትን ይሰጣል:: ዋና ትኩረቱ በሰዋስው፣ በቅርፅና በስርዓተ ነጥብ ላይ ከመሆኑ ባሻገር ተማሪዎች ስህተት የመፍጠር አጋጣሚ እንዳያገኙ በማድረግ ለጥራት ልዩ ስፍራ ይሰጣል::

በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የሚገኙ ተግባራት በሶስት እንደሚከፈሉ Richards (1990፣107) ይጠቁማሉ:: እነሱም ውስን ፅህፈት (Controlled Writing)፣ መር ፅህፈት (guided Writing) እና ነፃ ፅህፈት (Free Writing) ናቸው:: ስለእነዚህ የፅህፈት ተግባራት ሲገልፁ በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ መልመጃዎች ሁል ጊዜ የሚጀመሩት በውስን ፅህፈት መልመጃ ነው:: ከዚያም ቀስ በቀስ ወደ ነፃ የመፃፍ ክሂል መልመጃ ያመራሉ በማለት ሀሳባቸውን ይገልፃሉ::

### 2.5.1.1. ውስን ፅህፈት (Controlled Writing)

የውስን ፅህፈት መልመጃ በአብዛኛው በጀማሪ ተማሪዎች ለሚካሄድ የፅህፈት ትምህርት የሚቀርብና ተማሪዎች ወደ መር (guided) ፅህፈት ከመሸጋገራቸው በፊት የሚለማመዱበት የመጀመሪያው መልመጃ ነው:: በውስን ፅህፈት ደረጃ ተማሪዎች ስራቸውን የሚሰሩት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በአግባቡ በመከተል ነው:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት ተማሪዎች ስህተት እንዳይሰሩ ለመቆጣጠር ነው:: የክንውኑ ዓላማም ከስህተት የጸዳ አረፍተ ነገርን ወይም አነስተኛ ፅሁፍን እንዲፅፉ ለተማሪዎች ዕድል መስጠት ነው::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በሌላ በኩል Raimes (1983፣95) እንደሚገልፁት ውስን የፅህፈት መልመጃ ተማሪዎች የፅሁፍ ቅርፅና ይዘት ተሰጥቷቸው የሚያከናውኑበት በመሆኑ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የማፍለቅ ዕድል የላቸውም:: ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በመምህሩ ቁጥጥር ስር ናቸው:: እነሱም ማሟላት የሚገባቸው ነገር በጣም የተወሰነ በመሆኑ ስህተት ለመስራትም ሆነ የራሳቸውን ቅርፅና ይዘት ለመከተል ዕድሉ የላቸውም::

በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ውስን የፅህፈት መልመጃ ዓላማው ስህተትን በማስወገድ ላይ መሆኑንና ለመማር ማስተማር የሚቀርቡት መልመጃዎችም ማሰብንና ፈጠራን የማይጠይቁ ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል (McDonough and Shaw 1993፣178 እና Harmer 1991፣ 109)::

በክፍል ውስጥ የሚከናወኑት ተግባራትም:-

- ባዶ ቦታዎችን መሙላት፣
- ሞዴል አረፍተ ነገሮችን አስመስለው እንዲፅፉ ማለማመድ፣
- አረፍተ ነገሮችን ማያያዝ፣
- በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት አረፍተ ነገር መስራት፣
- ቅደም ተከተላቸው የተዛባ ቃላትን በማስተካከል አረፍተ ነገሮችን መገንባት፣
- አረፍተ ነገሮችን ማያያዝ እና ሌሎችም ይገኙባቸዋል Raimes (1983፣17)

### 2.5.1.2. መር ፅህፈት (Guided Writing)

ይህ የፅህፈት ደረጃ ተማሪዎችን ከውስን ወደ ነፃ ፅህፈት መልመጃ የሚያሸጋግር ድልድይ ነው:: በመር የጽህፈት መልመጃ ተማሪዎች የራሳቸውን አንዳንድ ሀሳቦች የመጨመር ዕድል ይኖራቸዋል:: በመሆኑም ከውስን የፅህፈት መልመጃ ይልቅ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተሻለ ነፃነት እንዳላቸው ምሁራኑ ይገልፃሉ:: ለምሳሌ Pincas (1982፣126) መር ፅህፈት ከውስን ፅህፈት በተሻለ ለተማሪዎቸ ነፃነት ይሰጣል፤ ነፃነቱ ግን በነፃ ፅህፈት ጊዜ ከሚያገኙት ያነሰ ነው:: ምክንያቱም በመር የፅህፈት መልመጃ ጊዜ ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ ሞዴል ይሰጣቸዋልና በማለት ያስረዳሉ::

በሌላ በኩል Raimes (1983፣103) መር የጽህፈት መልመጃ ቁጥጥር ከውስን ፅህፈት ያነሰ የሚሆነው የሚሰጣቸው ፅሁፍ ቅርፅና ይዘት ሙሉ በሙሉ ለተማሪዎች ስለማይቀርብላቸው

ነው ይላሉ:: ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለውም በመር ዕህፈት ጊዜ ተማሪዎች እንደ የተጀመረን ውጥን ታሪክ፣ ደብዳቤ፣ እንቀፅ... እንዲያሟሉ የሚታዘዙ መሆኑን ነው:: የሚጨምሩት ሀሳብ ግን በጅምር ከቀረበው እንቀፅ ሀሳብ ጋር የሚስማማ መሆን ይኖርበታል::

ይህ የፅህፈት ተግባራት ለተማሪዎቹ መነሻ የሚሆን ፍንጭ በመስጠት የራሳቸውን ሀሳብ አክለው በፅሁፍ እንዲያቀርቡ የሚያለማምድ ነው (Raimes 1983፣103):: የሚቀርቡት ተግባራትም:-

- በስንጠረዥ የቀረቡ ሀሳቦችን ወደ ፅሁፍ መቀየር፣
- በጅምር የቀሩ ፅሁፎችን (ውጥን ታሪኮችን፣ ደብዳቤዎችን፣ ቅፃችን ወዘተ.) መጨረስ፣
- የተዘጋጀ ቢጋርን ተጠቅሞ እንቀፅ መፃፍ፣
- የቀረቡትን ነገሮች በማወዳደርና በማነፃፀር በፅሁፍ መግለፅና
- ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ለጥያቄዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መነሻ አድርጎ አጭር ታሪክ መፃፍ የሚሉት ይገኙባቸዋል (እነ Athkins 1996፣112)::

2.5.1.3. ነፃ ፅህፈት (Free Writing)

ነፃ የፅህፈት መልመጃ ከመር የፅህፈት መልመጃ ቀጥሎ የሚመጣ በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ዘዴ የመጨረሻ ደረጃ ነው:: ይህ የፅህፈት መልመጃ ከመርም ይሁን ከውስን መልመጃዎች የበለጠ ለተማሪዎች ሰፊ ነፃነትን ይሰጣል:: Pincas (1982፣106) እንደሚገልፁት ነፃ የፅህፈት መልመጃ ተማሪዎች በሚሰጣቸው ርዕስ ወይም በመረጡት ሀሳብ በራሳቸው የሚያከናውኑት መልመጃ ነው:: ተማሪዎች ፅሁፉን የሚፅፉት ከራሳቸው አፍልቀው ሲሆን በሚፅፉት ነገር ላይም የሚደረገው ቁጥጥር የላላ ነው::

Pincas (1982፣110) በተጨማሪ ሲያብራሩ የነፃ ፅህፈት መልመጃ ትኩረት የሚሰጠው ሁሉንም ነገር እንዲፅፉ ሳይሆን የተማሩትን ለመፃፍ ብቻ ነው:: ተማሪዎች በውስንና በመር የፅህፈት መልመጃ ያገኙትን ዕውቀትና ልምድ በማቀናጀት እራሳቸውን ችለው መፃፍ ይኖርባቸዋል:: በነፃ የፅህፈት ትምህርት መልመጃ ምንም እንኳ ተማሪዎች በውስንና በመር የፅህፈት መልመጃዎች የተማሩትን እንዲከተሉ ቢደረግም ሀሳቡን የሚያቀናጁት በራሳቸው ስለሆነ ሰፊ ነፃነት አላቸው:: እንደ Raimes (1983፣7) ገለፃ ደግሞ፣ ነፃ ፅህፈት ለሰዋስዋዊ

አጠቃቀምና ስርዓተ አፃፃፍ፣ እንዲሁም ለትክክለኛነቱ ትኩረት የሚሰጥ ቢሆንም፣ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የመግለፅ ዕድል አላቸው::

**2.5.1.4. በውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች**

Richards (1990፣112) Murray (1980)ን ጠቅሰው ሲያስረዱ ይህ ዘዴ የተማሪዎችን የመጨረሻ የጽሁፍ ስራ (ውጤት) እንጂ የአፃፃፋቸውን ሂደት አያሳይም:: አያይዘው ሲያብራሩም በአሁኑ ጊዜ ስለ ዕህፈት ትምህርት የሚያጠኑ ምሁራን በውጤት ላይ ያተኮረ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ፣ ዕህፈትን ለማስተማር ችግሮች አሉበት ባይ ናቸው:: ምክንያቱንም ሲገልፁ ዘዴው የሚያተኩረው አንድ የዕህፈት ተግባር እንዴት ሆኖ ተጠናቋል የሚለውን እንጅ አንድን ዕሁፍ ለመፃፍ ምን አይነት አካሄድ እንከተል የሚለውን አያመለክትም:: በተጨማሪም ይህ ዘዴ በተፃፈው ነገር ትክክለኛነት ላይ ልዩ ግምት አለው:: በዚህ የአቀራረብ ዘዴ ተማሪው የሚያውቀው አረፍተ ነገርን ከአረፍተ ነገር እንዴት ማዋቀር እንደሚችልና የተለያዩ የዕሁፍ ቅርፃችን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት ነው:: ይሁን እንጅ፣ ይህ ውጤት ላይ ያተኮረ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪው በራሱ መንገድ ሄዶ፣ በራሱ ሀሳብ አፍልቆና አደራጅቶ የራሱን ዕሁፍ እንዴት መፃፍ እንደሚችል አይገልፅም በማለት ይተቻሉ::

በውጤት ላይ ያተኮረ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴን አስመልክተው Pincas (1982፣24) እንደሚገልፁት፣ በዚህ ዘዴ ተማሪው የሚያከናውነው በመምህሩ አድርግ ተብሎ የታዘዘውን ብቻ በመሆኑ የፈጣሪነት ባህርይው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው:: Kroll (1990፣ 15) በበኩላቸው በዚህ በውጤት ላይ ያተኮረ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪው በራሱ ተነሳስቶ ሀሳቡን በትክክል ለመግለፅ የሚያስችል ዕውቀት አያዳብርም:: ምክንያቱም ዘዴው ተማሪው ፈጥሮ እንዲፅፍ የማያበረታታና በትዕዛዝ የተሞላ በመሆኑ ነው ይላሉ::

በሌላ በኩል Raimes (1983፣17) ይህ ዘዴ ተማሪዎች እንዴትና ለምን እንደሚፅፉ ከማሳየት ይልቅ የዕሁፍ ቅርፃችንና የሰዋስው ህጎችን ተከትለው እንዲፅፉ የሚገፋፋ ነው:: በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ለሂደታዊ ክሂሎች ዋጋ አይሰጥም:: የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ትኩረትም ዕሁፉ በሚዘጋጅበት ሂደት ላይ ሳይሆን ተጠናቆ በሚቀርበው ስራ ላይ ሲሆን ውጤቱም የሚለካው ከትክክለኛነት አንፃር ነው (Badger እና Goodith 2000፣157)::

### 2.5.2. ሂደታዊ አቀራረብ (Process Approach)

Raimes (1983፣10) ሂደታዊ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብን አስመልክተው ሀሳባቸውን ሲገልፁ፣በአሁኑ ጊዜ የጽህፈት ትምህርት በውጤት ላይ ካተኮረ አቀራረብ ይልቅ ወደ ሂደት ተኮር የመለወጥ አዝማሚያ እያሳየ መጥቷል:: በሂደት ተኮር ተማሪዎች የሚፅፉበትን ተግባርና ተደራስያንን ከማሰብ አልፈው እንዴት አድርጌ እፅፋለሁ? እንዴትስ አድርጌ እጀምረዋለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች ማሰብ ይኖርባቸዋል:: የዚህ አቀራረብ ትኩረት በመፃፍ በተደረሰበት ውጤት ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ለመፃፍ በሚያልፉባቸው ሂደቶች ላይ ነው::

ሂደታዊ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የሚያተኩረው ተማሪው አንድን የዕህፈት ተግባር እንዴት አድርጎ ጀምሮ ከዚያም እንዴት አድርጎ አቀናጅቶ በራሱ መፃፍ ይችላል የሚለው ላይ ነው:: በመሆኑም ይህ የአቀራረብ ዘዴ ተማሪ መራሽ ነው ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም ትልቁን ሚና የሚጫወተው ተማሪው ነውና:: Richards (1990፣111) የመምህሩን ሚና ሲገልፁ፣ በሂደታዊ አቀራረብ የመምህሩ ሚና በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ማመቻቸት ነው:: መምህሩን ተማሪዎች በሚፅፉበት ጊዜ እየተንቀሳቀሱ በማየት ተማሪዎችን ያበረታታሉ የሀሳብና የምክር እርዳታ ያደርጋሉ፤ የሚያስፈልጉ ነገሮች ካሉም ያሟላሉ::

በሂደታዊ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ ፅሁፍ ለመፃፍ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የተግባር ደረጃዎች እንዳሉ Hedge (1988፣15) ፣ Duke (1983፣4-7) ፣ Murray (1982፣15-19) እና Richards (1990፣118) ይገልፃሉ:: እነዚህ ምሁራን የጠቀሷቸው የተለያዩ ደረጃዎች በሂደታዊ አቀራረብ የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን በሂደት ለማሳየት የቀረቡ ሲሆኑ ይዘውት የተነሱት መሰረታዊ ሀሳብም ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ Richards (1990፣108) በሶስት ደረጃ ከፍለው ያስቀመጧቸው የዘዴው የአቀራረብ ስልቶች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል::

#### 2.5.2.1. ቅድመ ፅህፈት (Pre-Writing)

ይህ ደረጃ በሂደት ተኮር ውስጥ ካሉት የዕህፈት ትምህርት አተገባበር የመጀመሪያው ነው:: ቅድመ ፅህፈት በቅድሚያ ሊያካትታቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል የሚፅፉበትን ርዕስ መምረጥ፣ ስለ ርዕሱ ማሰብ፣ ተደራሲያንን መመልከትና ለምን ዓላማና ተግባር እንደሚፅፉ

ማወቅ ይገኙባቸዋል (Richards 1990፣109):: እንደ Murray (1982፣15) ገለፃ ደግሞ በዚህ ደረጃ መፃፍ ከመጀመር በፊት የሚከናወኑ ዝግጅቶችን በሙሉ ይይዛል:: ተማሪው መረጃ ለመሰብሰብ፣ አንባቢውን ለመገመት፣ አላማውን ለመወሰንና የመጀመሪያ ንድፉን ለማቀድ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ያጠቃልላል በማለት የመጀመሪያውን ምሁር ሀሳብ ያጠናክሩታል::

ቅድመ ፅህፈት አንድ ፅሁፍ ለመፃፍ የሚያስችል ሀሳብ የሚሰበሰብበት ጊዜ ነው:: አንድ ፅሁፍ ከመፃፉ በፊት ስለሚፃፍበት ርዕስ ጉዳይ ይታሰባል፤ ርዕሱ ምን አይነት ስፋትና ጥልቀት አለው? ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦችስ ማግኜት የሚቻለው እንዴት ነው? እና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ የሚፈለግበትና የአእምሮ ጓዳ የሚፈተሽበት ጊዜ ነው:: ይህ ደረጃ ድንገት በአእምሮ የሚመጣ ማንኛውም ሀሳብ የሚሰበሰብበትም ወቅት ነው:: እነዚህን የተለያዩ መረጃዎች ለመሰብሰብ ከሚያስችሉት ነገሮች መካከል አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው::

2.5.2.2. **የፅህፈት ጊዜ** (While Writing)

ይህ ከሂደታዊ የፅህፈት ትምህርት አተገባበር መካከል ሁለተኛው ደረጃ ነው:: የፅህፈት ጊዜ (While Writing) ሀሳብን በወረቀት ላይ በረቂቅ መልክ ማስፈርን ይመለከታል:: ደረጃውም ትክክለኛ የፅህፈት ተግባር የሚጀመርበት ሲሆን፣ ተማሪው በቅድመ ፅህፈት ደረጃ የሰበሰባቸውን ሀሳቦች በረቂቅ መልክ ወረቀት ላይ የሚያሰፍርበት ጊዜ ነው:: ተማሪው በተጨማሪም ሀሳቦቹን አብራርቶ ግልፅ በሆነና አሻሚነት በሌለው ቋንቋ የሚፅፍበት፣ ለፅሁፉ ቅርፅ በራሱ የሚፈጥርበት ደረጃ ነው (Richards 1990፣109)::

እንደ Hedge (1988፣11) ገለፃ ደግሞ በዚህ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት በርካታ ናቸው:: ለአብነት ያህልም ማቀድ-ማርቀቅ-መከለስ- ደግሞ ማቀድ ይጠቀሳሉ:: በመከለስ ደረጃም ከሚካሄዱት ክንውኖች ቅድሚያ የሚሰጠው የይዘት ትክክለኛነት ነው:: ተማሪዎች የተፃፈውን መገምገምና የሚጨመሩ ወይም የሚቀነሱ ሀሳቦች ካሉ ማስተካከል ይኖርባቸዋል:: ስለዚህ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ የመጀመሪያውን ረቂቅ ሲፅፉ መግለፅ በፊልጉት ይዘት ላይ ማተኮር አለባቸው::

2.5.2.3. ድህረ ፅህፈት (Post Writing)

ይህ ደረጃ ከሂደታዊ የፅህፈት ትምህርት አተገባበር መካከል የመጨረሻው ነው:: ድህረ ፅህፈት ወይም ማቃናት/ ክለሳ የተፃፈው ነገር የሚገመገምበትና በፅሁፉ አመካኝነት ለማስተላለፍ የተፈለገው ነገር በትክክል እንዲተላለፍ የመጨረሻ ማስተካከያ የሚደረግበት ነው:: ተማሪው መልዕክቱን፣ ቅርፁንና አንባቢውን የሚያጤንበት፣ ግልፅነቱን የሚገመግምበትና ፅሁፉን ደግሞ በማንበብ ለአንባቢው በሚመች መልኩ መቅረቡን የሚያረጋግጥበት የክንውን ደረጃ ነው (Richards 1990፣109)::

ድህረ ፅህፈትን አስመልክቶ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ድህረ ፅህፈት በቅድመና በፅህፈት ጊዜ የተሰበሰቡትና የተረቀቁት ሀሳቦች ተገቢነት የሚገመገምበት ደረጃ ነው:: በአጠቃላይ ተማሪው ያረቀቃቸውን ሀሳቦች ከዓላማውና ከአንባቢው አኳያ ሊያስተላልፍ የተፈለገው መልዕክት በትክክል መቅረብ ያለመቅረቡን የሚመረምርበት ነው::

2.5.2.4. **በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ አስተያየቶች**

እነ Attkins (1996፣120) ዘዴውን አስመልክተው እንደሚገልፁት "ሂደታዊ የፅህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ድክመት ሙሉ በሙሉ ነፃ ፅህፈትን ተጠቅሞ ተግባራዊ ማድረግ የተማሪዎችን የፅሁፍ ችሎታ ያዳብራል" ብሎ መገመቱ ነው ይላሉ::

ሂደታዊ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ በራሱ ያልተሟላ በመሆኑ ተማሪዎች ፅህፈትን ለመለማመድ የሚያስፈልጋቸውን የቋንቋ መዋቅር፣ የውህድ አሀድ ሞዴል፣ የስርዓተ አፃፃፍ መልመጃ፣ እንዲሁም ስነ ልሳናዊ ክሂሎችን የማከናወኛ በቂ ጊዜ አላካተተም በማለት Dyer (1996፣313) Rodrigues (1985)ን ጠቅሰው ይገልፃሉ::

Horowitz (1986፣445) በበኩላቸው ሂደታዊ የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከተላቸው የማስተማሪያ ስልቶች አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው መሆኑን ያስረዳሉ:: ይህም በአፃፃፍ ሂደቱ ተማሪዎች ብዙ ረቂቆችን እንዲፅፉ የሚሰጠው ትኩረት ሁል ጊዜ ለሚፅፉት ድርሰት ብቁ አያደርጋቸውም:: ስለሆነ እርማት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱም ተማሪዎች ስለራሳቸው ችሎታ ያላቸው ግምት የተሳሳተ እንዲሆን ያደርጋቸዋል በማለት ይተቻሉ::

### 2.5.3. ውጤት ወሂደት አቀራረብ (Process- Product Approach)

ይህ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በስፋት አገልግሎት ላይ የዋሉትን በውጤት ላይ ያተኮረና ሂደታዊ የዕህፈት ትምህርት አቀራረቦችን በማጣመር የቀረበ ዘዴ ነው:: እነዚህ ዘዴዎች በተናጠል ውጤታማ ባለመሆናቸው ክፍተታቸውን ለመሙላት የቀረበ ነው:: የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለውጤትም ሆነ ለሂደት እኩል ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያምናል:: የተማሪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የዕህፈት ትምህርት ይዘቶችን ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል:: በተጨማሪም የተማሪዎች የዕህፈት ልምምድ (ክንውን) የተወሰነ አላማና ገደብ ሊኖረው ይገባል የሚል የአሰራር መርህ ያለው ነው (Dyer 1996፣312)::

Horowitiz (1986፣447) እንደገለፁት ሁለቱን አጣምሮ በስራ ላይ የዋለው ውጤት ወሂደት አቀራረብ፣ በኋላ ተግባር-ተኮር (Task-based) ተብሎ እንደዳበረም ይገልፃሉ:: አያይዘውም ይህ ዘዴ አካባቢን መሰረት አድርጎ በተለይ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ የዕህፈት ትምህርት ማስተማሪያ ሆኖ እንደተገኘ ያስረዳሉ::

እንደ Raimes (1983፣11) ገለፃ በአጠቃላይ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በተናጠል የሚተገበሩ አይደሉም:: በክፍል ውስጥ በአንድ ዘዴ ላይ ብቻ ተመስርቶ (ሌሎች ዘዴዎችን ሳያካትት) ዕህፈትን ማስተማር አስቸጋሪ ነው:: ለምሳሌ በሂደታዊ አቀራረብ ዘዴ ተጠቅሞ ክፍል ውስጥ የሚያስተምር መምህር ከተማሪዎች አቅምና ፍላጎት አንፃር እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች ዘዴዎች የወጡትን የማስተማሪያ ስልቶች (Techniques) መጠቀም አለበት:: ሞዴል አንቀፆች፣ ውስን ዕህፈት፣ ነፃ ዕህፈት፣ የአረፍተ ነገር መልመጃዎች እና የአንቀፅ ትንተና ለሁሉም አቀራረብ ዘዴዎች ጠቃሚዎች ናቸው:: የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ አንድን ዘዴ መሰረት ያደረገ ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም ዘዴዎች የተውጣጣ መሆን ይኖርበታል:: ዕህፈትን ለማስተማር አንድ መንገድ ብቻ ያለ ሳይሆን ብዙ መንገዶች አሉ::

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳ የዕህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች የተለያየ የማስተማሪያ ስልቶች ቢኖሯቸውም፣ በክፍል ውስጥ ያላቸው አተገባበር ስብጥር ባለው መልክ የሚቀርብ ነው እንደ Raimes (1983፣11) ገለፃ:: እኒሁ ምሁር አንድን ዘዴ ብቻ ተጠቅሞ ለማስተማርም የማይቻል መሆኑንም ይጠቁማሉ:: በአጠቃላይ የዕህፈት ትምህርት

አቀራረብ ዘዴዎች በአተገባበራቸው ሂደት የተደጋጋፊነት ባህርይ አላቸው ብሎ መናገር ይቻላል::

## 2.6. በዚህ የጥናት ርዕስ ዙሪያ ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ጥናቶች

በዕህፊት ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ጥናቶች ተካሂደዋል:: እነዚህ ጥናቶች ከመረጃዎቻቸው ተነስተው የደረሱበትን ውጤት ገልፀዋል፤ የየበኩላቸውን የመፍትሄ ሀሳቦችም ጠቁመዋል:: ጥናቶቹን ካካሄዱ ተማሪዎች መካከልም የሚከተሉት ይገኙበታል::

ሠሎሞን (1987) "የቢጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት" በሚል ርዕስ በ11ኛ ክፍል ላይ ጥናት አካሂደዋል:: ውጤቱም በተማሪዎች የግንዛቤ ችግርና በጉዳዩ ያለመለመድ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ላይ ባይሆንም፣ በአግባቡ ከተያዘ ጠቃሚ መሆኑን ገልፀዋል::

ማረው (1987) "በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ በሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል:: የደረሱበት መደምደሚያም በግል ከሚፃፉ ድርሰቶች ይልቅ በቡድን የሚጻፉት የተሻሉ መሆናቸውን፣ በጥሩ ድርሰትና በቡድን ስራ መካከል (በአንፃራዊነት) ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩንና የቡድን ስራ ለድርሰት ትምህርት አወንታዊ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን አመልክተዋል::

ሰዮም (1988) "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት" በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት ሂደታዊ የዕህፊት አቀራረብን (ሥነዘዴን) ተጠቅሞ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕህፊትን ማስተማር ክሂሉን ለማዳበር ውጤታማ ሆኖ መገኘቱን ማረጋገጣቸውን ገልፀዋል::

ሠሎሞን (1991) "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ" በሚል ርዕስ በአዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአንድ መምህር ላይ ጥናት አካሂደዋል:: የደረሱበት ውጤትም በመምህሩ የማስተማር ዘዴና በተማሪዎቹ የመፃፍ ስትራቴጅ መካከል ክፍተት መኖሩንና መምህሩ የሚከተሉት የማስተማር ዘዴ በአብዛኛው ተማሪዎች በተፈጥሮ ያላቸውን የመፃፍ ስትራቴጅ የሚያሳድግላቸው አለመሆኑን አመልክተዋል::

ዕጌ (1992) "ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛው እርከን (5-8) በተዘጋጁት የአማርኛ መፃህፍት ላይ የይዘት ትንተና ግምገማ አካሂደዋል:: በጥናታቸው የደረሱበት ማጠቃለያም በአራቱም ክፍሎች የፅህፈት ክሂል ይዘቶችን አስመልክቶ የቀረበው የተለጣጣቂነት (Sequence) መስፈርት በአግባቡ ስራ ላይ አለመዋሉንና ለዚህም አብይ ምክንያት የሆነው ይዘቶቹ የተማሪዎችን ችሎታ የሚመጥኑ ሆነው ያለመመረጣቸው ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል::

ሰይድ (1993) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መፅሀፍ የቀረቡትን የፅህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ ግምገማ" በሚል ርዕስ በሰባት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጥናታቸውን አካሂደዋል:: የደረሱበት ማጠቃለያም ተማሪዎች ፅህፈትን በተግባር በመለማመድ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴ አለመታየቱን፣ በመማር ማስተማር ሂደቱም የሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች ለደረጃው በመርሀ ትምህርቱ ከቀረቡት ዝቅ ያሉ መሆናቸውና የፅሁፍ ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ አለመሆናቸውን አመልክተዋል:: በተጨማሪም ተማሪውን ለመፃፍ የሚያበረታታ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ተግባራዊ እንዳልሆነ ጠቁመዋል::

ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ለፅህፈት ክሂል ትምህርት በአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች አደረጃጀት፣ የይዘትና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ፣ የመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴና ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅ፣ የቢጤ እርማት፣ በግልና በቡድን የሚጻፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት፣ እንዲሁም ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ባለው ተግባራዊነት ላይ በመመስረት የቀረቡ ናቸው:: ይሁን እንጅ ይህ ጥናት በመርሀ ትምህርቱ ላይ በማተኮር የፅሁፈትን ትምህርት ለማስተማር የቀረቡትን የመማር ማስተማር ክንውኖች (ስነ ዘዴዎች) አተገባበር የሚፈተሽ መሆኑ ከእነዚህ ስራዎች የተለየ ያደርገዋል::

## ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው የአጠናን ዘዴ አይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) ሲሆን አቀራረቡ ደግሞ ገላጭ (Descriptive) ነው:: ጥናቱ ይህን የምርምር ዘዴ በመከተል በአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት የዕህፈትን ትምህርት ለማስተማር የቀረቡትን ስነዘዴዎች አተገባበር ፈትሿል::

### 3.1. የናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የአማራ ክልል መስተዳድር ነው:: ክልሉ የተመረጠው በአመች ናሙና (Convenience Sampling) ሲሆን የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያትም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለአጥኚው አመች ሆኖ በመገኘቱ ነው::

### 3.1.1. የትምህር ቤት ናሙና አመራረጥ

በክልሉ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል የደምበጫ ወረዳን ተተኳሪ በማድረግ በስሩ ከሚገኙት አስራ ሰባት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች መካከል አራቱ የደንበጫ፣ የአዲስ አምባ የዋድና የአርበኞች ትምህርት ቤቶች በነሲብ የእጣ ናሙና ዘዴ (Random Sampling) ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪዎች እንዲሆኑ ተደርገዋል

### 3.1.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪዎች የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ተማሪዎችና መምህራን ናቸው:: የክፍል ደረጃው ከ5ኛ እስከ 8ኛ እንዲሆን የተደረገው የይሁንኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴን (Purposive Sampling) በመጠቀም ነው:: ዘዴው የተመረጠበት ምክንያትም ሁሉም በተመሳሳይ የእርከን ደረጃ ላይ ስለሚገኙ አራቱንም የክፍል ደረጃዎች በተከታታይ ማየቱ በሁለተኛው እርከን የዕህፈት ክሂል እንዴት እየተተገበረ እንዳለ አስተማማኝ መረጃ ይገኛል ተብሎ ስለታመነበት ነው::

### 3.1.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙትን አስራ ሁለት መምህራን የጥቅል ንሞና ዘዴን (Comprehensive Sampling) በመጠቀም ሁሉም በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል:: ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ ቢካተቱ የተሻለ መረጃ ሊገኝ ይችላል ተብሎ ስለታመነ ነው:: እነዚህ መምህራን በሙሉ የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን በምልከታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ግን የይሁንኝ ንሞና ዘዴን (Purposive Sampling) በመጠቀም በአጠቃላይ ከአራቱም ትምህርት ቤቶች ስምንት መምህራንን መምረጥ አስፈላጊ ሆኗል:: ይህ ዘዴ የተመረጠውና ሁሉም መምህራን በምልከታው እንዲካተቱ ያልተደረገበት ምክንያት በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት አንዳንድ መምህራን ከአንድ የክፍል ደረጃ በላይ የሚያስተምሩ በመሆናቸው ነው::

## 3.2. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰነድ ምርምራ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው::

### 3.2.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ምልከታ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከመማር ማስተማሩ ሂደት ለመሰብሰብ በዋናነት የተመረጠ ዘዴ ነው:: ምልከታው በአራቱም ናሙና ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ ስምንት መምህራንን አካቷል::

ምልከታ በማካሄድ በክፍል ውስጥ መረጃዎችን መሰብሰቢያ የመከታተያ ዝርዝር (Checklist) ከHedge (1988፣ 24-26) የፅህፈት ክሂል መርሆችንና ከNunan (1989፣115) የክፍል ምልከታ መከታተያ ዝርዝር (Checklist) ሀሳብ በመውሰድ በአንድ የስነ ትምህርት ምሁርና በጥናቱ አማካሪ ሙያዊ አስተያየት ተሰጥቶበት ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት ስራ ላይ ውሏል::

የናሙና ትምህርት ቤቶቹን አስተዳደር ፈቃደኝነትና የመምህራንን ትብብር በመጠየቅ በጊዜ ሰሌዳቸው መሰረት የምልከታ ዕቅድ በማዘጋጀትና ለረዳት ተመልካቾች በመከታተያ ዝርዝሩ ላይ

ስለተቀመጡት ክንውኖችና መስፈርቶች እንዲሁም ስለአሞላሉ ግንዛቤ በማስጨበጥ የቅድመ ምልከታ ተግባር ተከናውኗል::

አጥኚው ለምልከታ የወጣውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግም ፈቃደኛ የሆኑትን መምህራን በረዳት ተመልካችነት መርጧል:: ምልከታው እያንዳንዱ ተጠኚ መምህር በሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ ሁለት ሁለት ጊዜ የተካሄደ ሲሆን አጥኚውና አንድ ረዳት ተመልካች አንድ ላይ በመግባት ተከናውኗል:: ከየምልከታው በኋላም ወዲያውኑ በዕለቱ ውይይት በማካሄድና በተፈጠሩ ልዩነቶች ላይ በመነጋገር አንድ የጋራ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ጥረት ተደርጓል:: በተጨማሪም የመከታተያ ዝርዝሩን ለመደገፍ የቪዲዮ ቀረጻ ተካሂዷል::

### 3.2.2. የሰነድ ምርመራ

የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ የሰነድ ምርመራ አስፈላጊ በመሆኑ በመርሃ ትምህርቱ፣ በመማሪያ መፃህፍቱና በመምህሩ መምሪያዎች ውስጥ የዕህፈትን ክሂል ለማስተማር የቀረቡት የመማር ማስተማር ክንውኖች (ስነዘዴዎች) ፍተሻ ተደርጎባቸዋል::

### 3.2.3. የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ የተዘጋጀው ለመምህራን ብቻ ሲሆን መጠይቁን አስራ ሁለት መምህራን እንዲሞሉ ተደርጓል:: የመጠይቁ አላማም በምልከታ የተሰበሰበውን መረጃ ለማገዝና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ እና አስተማማኝ ለማድረግ ነው:: መጠይቁ የተጠኚዎችን ዳራዊ ሁኔታ ለማወቅ፣ የጽህፈትን ትምህርት የሚያስተምሩበትን ስነዘዴ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደትም የሚያከናውኗቸውን ተግባራት፣ ለትምህርቱና ለመማር ማስተማሩ የሚሰጡትን ትኩረት ለማወቅ የቀረበ ነው::

ይህ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የመጀመሪያው የመምህራኑን ዳራዊ ሁኔታ፣ የሁለተኛው ክፍል ደግሞ አስራ ሰባት ጥያቄዎች ሲኖሩት በመማር ማስተማሩ የሚከናወኑ ተግባራትን፣ ቴክኒኮችንና ሚናዎችን ይዟል:: በመጨረሻም በመማር ማስተማሩ ሂደት በይበልጥ በተደጋጋሚ የሚቀርቡትን የመማር ማስተማር ክንውኖች ለይተው እንዲያሳዩ የሚጠይቅ ነው::

ጥያቄዎቹ በአብዛኛው የተዘጋጁት በ Likert ስኬል መሰረት ሲሆን፣ ለሚሰጡት አወንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ ምክንያት የሚፈልጉ ጥያቄዎችም ቀርበዋል:: የፅሁፍ መጠይቁ ከRobert Sommer እና Barbara Sommer (1980፣138-139 እና 151) የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና ስልቶች ሀሳብ በመውሰድ የጥናቱን የዓላማ ጥያቄዎች ሊመልስ በሚችል መልኩ ማሻሻያ ተደርጎበት በአንድ የስነልቦና ምሁርና በጥናቱ አማካሪ ተገምግሞ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል::

## 3.3. የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ከምልከታ፣ ከሰነድ ምርመራና ከፅሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎችና ውጤቶች በመነሳት በአላማው ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ትንተና ተካሄዷል:: ትንተናው በሁለት ንዑስ ክፍሎች የቀረበ ሲሆን፣ የመጀመሪያው መረጃዎቹ የተተነተኑበት ክፍል ነው:: መረጃዎቹ በሚያነሱት መሰረታዊ ጉዳይ ተለይተው በሰንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት (%) ቀርበዋል:: ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ደግሞ በመረጃ ትንተና ወቅት የታየው ውጤት የተብራራበት ነው::

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዓላማ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የጽህፈትን ክሂል ለማስተማር የቀረቡትን ስነ ዘዴዎች አተገባበር መፈተሽ ሲሆን፣ ስነ ዘዴዎቹ ከመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ በክፍል ያላቸውን አተገባበር፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህራንንና የተማሪዎችን ሚና በመቃኘት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መግለፅ ነው:: በመሆኑም ከልዩ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከሰነድ ምርመራ፣ ከምልከታና ከመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ተለይተውና ተተንትነው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

## 4.1. የመረጃ ትንተና

### 4.1.1. ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች መርሃ ትምህርት፣ መማሪያ መፃህፍትና የመምህር መምሪያዎች የፅህፈትን ክሂል በመማር ማስተማር ሂደት ተግባራዊ የሚሆኑ አላማዎችን፣ መልመጃዎችን ወይም ክንውኖችንና የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን ያካተቱ መሆናቸውን ከተደረገው የሰነድ ምርመራ መገንዘብ ተችሏል::

የፅህፈት ክሂልን ለማስተማር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ይዘቶች በአራቱም የክፍል ደረጃዎች (ከ5ኛ-8ኛ) በአብዛኛው ተመሳሳይነት ታይቶባቸዋል:: ይዘቶቹም በተከታዩ ሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ናቸው::

ሰንጠረዥ 1. በእርከኑ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶችን ስርጭት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች | የክፍል ደረጃዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 2 | በስርዓተ ነጥቦች መገልገል | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 3 | አንቀፅ መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 4 | ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 5 | አጭር ፅሁፍ መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 6 | የተዘበራረቁ ሀሳቦችን አስተካክሎ መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 7 | የመንስኤና ውጤት ግንኙነትና ልዩነት መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 8 | ነገሮችን እያወዳደሩ መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 9 | ማስታወሻ መያዝ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 10 | የህይወት ታሪክ መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 11 | ፅሁፍን በማረም መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 12 | አስተዋፅኦ ማዘጋጀት | - | - | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 13 | አንድን ሀሳብ በራስ አባባል መፃፍ | 1 | 8.33 | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 14 | ፅሁፍን ማሳጠር | - | - | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 15 | ውጥን ታሪክን መጨረስ | - | - | 1 | 5.88 | - | - | - | - |
| 16 | ዋናና ንዑስ ሀሳቦችን ለይቶ መፃፍ | - | - | - | - | 1 | 5.26 | - | - |
| 17 | ቃለመጠይቅ መያዝ | - | - | - | - | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 18 | ድርሰት መፃፍ | - | - | - | - | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 19 | ፅሁፎችን ማስፋፋት | - | - | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| 20 | በሀቅና የግል አስተያየት መካከል ያለውን ልዩነት መፃፍ | - | - | 1 | 5.88 | 1 | 5.26 | 1 | 5.55 |
| | ድምር | 12 | 100 | 17 | 100 | 19 | 100 | 18 | 100 |

በሰንጠረዥ አንድ ላይ እንደተገለፀው በደረጃው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ያላቸውን አቀራረብ ስንመለከት በአምስተኛ ክፍል አስራ ሁለት ይዘቶች ይገኛሉ:: ከእነዚህ ውስጥም ስድስቱ (በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 6፣ 7፣ 9 እና

13 የተጠቀሱት) ውስን ፅህፈትን (Controlled Writing) በመከተል የሚተገበሩ ናቸው:: አራቱ ደግሞ (በተራ ቁጥር 3፣ 4፣ 5 እና 8 የተመለከቱት) መር ፅህፈትን (Guided Writing) መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ማለትም በተራ ቁጥር አስር እና አስራ አንድ ነፃ ፅህፈትን (Free Writing) እና ሂደታዊ ፅህፈትን (Process Writing) ለማስተማር የቀረቡ የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች መሆናቸውን ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል::

ለስድስተኛ ክፍል የቀረቡትን የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች ስናይ ደግሞ አስራ ሰባት ናቸው:: ስምንቱ (በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 6፣ 7፣ 9፣ 13፣ 14 እና 20 የተጠቀሱት) ውስን ፅህፈትን፣ ሰባቱ (በተራ ቁጥር 3፣ 4፣ 5፣ 8፣ 12፣ 15 እና 19 የተጠቀሱት) መር ፅህፈትን፣ በተራ ቁጥር አስር ነፃ ፅህፈትን እንዲሁም በተራ ቁጥር አስራ አንድ ሂደታዊ ፅህፈትን ለመተግበር የተዘጋጁ የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች እንደሆኑ መረጃው ያመለክታል::

በሰባተኛ ክፍል ደግሞ አስራ ዘጠኝ የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል:: ከእነዚህ ይዘቶች መካከል አስሩ (በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 6፣ 7፣ 9፣ 13፣ 14፣ 16፣17 እና 20 የተጠቀሱት) ውስን ጽህፈትን፣ ስድስቱ (በተራ ቁጥር 3፣4፣5፣8፣12 እና 19 የተጠቀሱት) መር ፅህፈትን፣ በተራ ቁጥር አስርና አስራ ስምንት የቀረቡት ሁለቱ ነፃ ፅህፈትንና በተራ ቁጥር አስራ አንድ ሂደታዊ ፅህፈትን ለማከናወን የቀረቡ መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ::

በስምንተኛ ክፍል አስራ ስምንት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች የቀረቡ ሲሆን ዘጠኙ (በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 6፣ 7፣ 9፣ 13፣ 14፣ 17 እና 20 የተጠቀሱት) ውስን ፅህፈትን፣ ስድስቱ (በተራ ቁጥር 3፣ 4፣ 5፣ 8፣ 12 እና 19 የተጠቀሱት) ደግሞ መር ፅህፈትን፣ ሁለቱ (በተራ ቁጥር 10 እና 18 የተጠቀሱት) ነፃ ፅህፈትን እና በተራ ቁጥር አስራ አንድ የተጠቀሰው ሂደታዊ ፅህፈትን ለማስተማር ያለሙ መሆናቸውን በተደረገው ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል::

በእርከኑ በስራ ላይ በሚገኘው መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች በአጠቃላይ ሃያ ሲሆኑ አስሩ (50%) የውስን ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡ ሆነው ተገኝተዋል:: ሰባቱ (35%) ደግሞ በመር ፅህፈት ላይ ያተኩሩ ናቸው:: ሂደታዊ ጽህፈትን ለመተግበር የቀረበው ይዘት አንድ (5%) ሲሆን ነፃ ፅህፈትን ለማስተማር ደግሞ ሁለት (10%) መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

የቀረበው ይዘት አንድ (5%) ሲሆን ነፃ ፅህፈትን ለማስተማር ደግሞ ሁለት (10%) መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

በአጠቃላይ በአርከኑ የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው በውስንና መር (Controlled and Guided Writing) ፅህፈትን መሰረት አድርገው የሚከናወኑ መሆናቸውን ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል:: በአንፃሩ ደግሞ ለነፃ ፅህፈት (Free writing) እና ለሂደታዊ ፅህፈት (Process Writing) የማስተማር ዘዴዎች የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ሆኖ ታይቷል:: ይህም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉት የፅህፈት ትምህርት የማስተማር ዘዴዎች በአብዛኛው በክለሳ ድርሳኑ ላይ በቁጥር 2.5.1 የቀረበውን በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብን (Product Focused Approach) መሰረት ያደረጉ ናቸው ማለት ይቻላል::

በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በሚገኙት የመማሪያ መፃህፍት ውስጥም የፅህፈት ትምህርትን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች መርሀ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ ናቸው:: ለምሳሌ ያህልም በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የሚገኙትን የአንቀጽ አፃፃፍ የመማር ማስተማር ክንውኖች በሰንጠረዥ ሁለት ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል::

ሰንጠረዥ 2. በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የአንቀጽ አፃፃፍን የሚያሳዩ መግለጫዎች

| ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን |
| --- | --- |
| አንቀጽ መፃፍ | 1. በአንድ አንቀጽ ውስጥ ያሉ አረፍተ ነገሮች ስለ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ የሚናገሩ መሆን እንዳለባቸው ማስገንዘብ<br>2. አንድ አንቀጽ የሚያብራራው ዋና ሀሳብ ብዙ ጊዜ በአንቀጽ መጀመሪያ ላይ እንደሚገኝ ማስገንዘብና የተለያዩ አንቀጾችን እያቀረቡ ማወያየት<br>3. እንደ ሁኔታው ሁለትም ሶስትም አረፍተ ነገር ያለው ጅምር አንቀጽ ሰጥቶ የጎደለውን ሀሳብ የያዙ አረፍተ ነገሮች እንዲያሟሉ ማለማመድ<br>4. የተለያዩ መንደርደሪያና ዝርዝር ሀሳቦችን አንድ ላይ አቅርቦ ከየመንደርደሪያ ሀሳቡ ጋር አብረው የሚሄዱ ዝርዝሮችን እንዲመርጡና አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ<br>5. ልዩ ልዩ መንደርደሪያ አረፍተ ነገሮችን በማቅረብ በሚመርጡት አንቀጽ እንዲጽፉ በማድረግ ማለማመድ |

ከላይ በሰንጠረዥ 2 የተገለፀው የአንቀጽ አፃፃፍን አስመልክቶ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረበው የመማር ማስተማር ክንውን በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በተመሳሳይ ሁኔታ የቀረበ ነው:: /አባሪ ሶስትን ይመለከቷል/:: ይሁን እንጂ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ያላቸው አቀራረብና አተገባበር የተማሪዎቹን ደረጃ ያገናዘበ ነው:: በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ተማሪዎቹ አንቀጽን የሚለማመዱባቸው ርዕስ ጉዳዮችና የሚቀርብላቸው የአቀጽ ይዘቶች ይለያያሉ::

በደረጃው የቀረቡ የማስተማሪያ መፃህፍትም ሙሉ በሙሉ እገዛ ያደርጋሉ ባይባልም መማሪያ መጻህፍቱ ላይ የተቀመጡትን ትዕዛዞች መሰረት በማድረግ፣ መምህራኑ ተግባራቱን እንዲያከናውኑ ፍንጭ የሚሰጡ ናቸው:: ለምሳሌ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የቀረቡ የመፃፍ ክሂል ስነ ዘዴን የሚመለከቱ መረጃዎች የሚከተለውን አካሄድ የሚከተሉ ናቸው::

- መምህሩ ለዕህፈት ትምህርት የቀረቡትን ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ ላይ የተቀመጠውን ትዕዛዝ መሰረት አድርገው ተማሪዎች እንዲመልሱ ማድረግ እንዳለባቸው፣
- የፅህፈት ተግባራቱ ሲከናወኑ ማበረታታት እንደሚያስፈልግ፣
- አስፈላጊ ሲሆን ፍንጭ ሰጪ ሀሳቦችን ማብራራት እንደሚገባ፣
- ተማሪዎች ስራቸውን ተለዋውጠው እንዲገማገሙ ማድረግ እንዳለባቸው እና

ሌሎች አመች ዘዴዎችን ሁሉ (በግልጽ ማወቅ አይቻልም) በመጠቀም ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማበረታታት፣ የሚሉት ጥቅል የሆኑ ሀሳቦችን የያዘ እንጂ ተግባራቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉት ስነ ዘዴዎች በተገቢው መንገድ የቀረቡና ለመምህሩ ሙሉ በሙሉ እገዛ ያደርጋሉ ብሎ ለመናገር አያስችሉም::

### 4.1.2. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የክፍል ውስጥ ምልከታ በተካሄደባቸው ጊዜያት ተጠኚ መምህራኑ በሙሉ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችን ያቀረቡት በትምህርት ዓመቱ በደረጃዎቻቸው ተዘጋጅተው በሚገኙት መማሪያ መፃህፍት በመጠቀም ነው:: የቀረቡት ይዘቶችም ስለመልመጃዎች አሰራር፣ አቀራረብ ወይም የመማር ማስተማር ክንውኖችና በሂደቱ የመምህራኑንና የተማሪዎችን ሚና ያሳዩ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ::

ምልከታዎች በተካሄዱባቸው ጊዜያት ለትምህርት የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት መልመጃዎች ዘጠኝ ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ በአምስተኛ ክፍል በተደረገው ምልከታ የታዩት ሁለቱ ነገሮችን በማወዳደር አንድነትና ልዩነታቸውን እንዲፅፉ የሚጠይቁና የመንስኤና ውጤት ግንኙነትና ልዩነትን ለይተው እንዲፅፉና እንዲናገሩ የሚያዙ ሲሆኑ መልመጃዎቹም በገጽ 67፣ 68 እና 72 ላይ ይገኛሉ:: በስድስተኛ ክፍል ደግሞ ግጥም መፃፍ፣ ነባራዊ ሀቅና የግል አስተያየቶችን ለይቶ በጽሁፍ መግለፅን የተመለከቱና በገፅ 69 እና 70 ላይ የሚገኙ ናቸው:: በሰባተኛ ክፍልም የድርጊቶችን ቅደም ተከተል አስተካክሎ መጻፍና የህይወት ታሪክ መፃፍ በገፅ 70 እና 71 ላይ የቀረቡ ናቸው:: በ8ኛ ክፍል የታዩት ደግሞ ደብዳቤ መፃፍ፣ ጽሁፍን አሳጥሮ መጻፍና ድርሰት መጻፍ በቅደም ተከተል በገፅ 62፣ 63፣ 64፣ 69 እና 70 ላይ ቀርበዋል::

የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን የማስተማር ዘዴ አተገባበር ትንተና በሚመለከት ከምልከታ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በሰንጠረዥ ሶስት ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል::

ሰንጠረዥ 3. የጽህፈት ትምህርት የማስተማር ዘዴ ትግበራ የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጽህፈትን የማስተማር ዘዴ ትግበራ | የተከናወኑ | | | | | | | | ያልተከናወኑ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ትምህርቱን በመግቢያ በመጀመር ተማሪዎችን ማነቃቃት | 2 | 25 | 1 | 12.5 | 3 | 37.5 | 2 | 25 | 6 | 75 | 7 | 87.5 | 5 | 62.5 | 6 | 75 |
| 2 | በተግባር መጻፍን ማለማመድ፣ መከለስና መገምገም | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 3 | የመማር ማስተማር ተራክቦ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ሀ. በግል መስራት | 7 | 87.5 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 1 | 12.5 | | | | | | |
| | ለ. በጥንድ መስራት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ሐ. በቡድን መስራት | 1 | 12.5 | | | | | | | 7 | 87.5 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| | መ. በህብረት መስራት | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 4 | በትክክለኛነት ላይ ማተኮር | 3 | 37.5 | 2 | 25 | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 | 6 | 75 | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 |
| 5 | ለዕለቱ ትምህርት አስረጅ /ሞዴል/ ማቅረብ | | | | | 1 | 12.5 | 1 | 12.5 | 8 | 100 | 8 | 100 | 7 | 87.5 | 7 | 87.5 |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በሰንጠረዥ ሶስት እንደተገለፀው በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ (ከ5ኛ -8ኛ) ከተደረጉት ስምንት ስምንት ምልከታዎች መረዳት እንደተቻለው መምህራኑ ትምህርቱን በመግቢያ በመጀመር ስለሚያስተምሩት ትምህርት ተማሪዎችን ባማነቃቃት ወደ ዕለቱ ትምህርት እንዲገቡ የማድረግ ጥረታቸው በሁሉም መምህራን ዘንድ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በአምስተኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ከተደረጉ ምልከታዎች ሁለቱ (25%)፣ ከስድስተኛ ክፍል አንዱ (12.5%)፣ ከሰባተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%) እና ከስምንተኛ ክፍል ሁለቱ (25%) ብቻ ያከናወኑ ሲሆን እነዚህም ቢሆኑ ከአለፈው ትምህርት በመነሳት የተከናወኑ ተግባራትን ከማስታወስ የዘለለ አይደለም። ቀሪዎቹ በቀጥታ ተማሪዎች ደብተሮቻቸውንና መፅሀፋቸውን አውጥተው እንዲከታተሉ ከመጠየቅ ባሻገር መግቢያ የሚሆን ገለጻ አላደረጉም። የቀረበውን የዕህፌት ትምህርት ይዘት ለምን ዓላማና እንዴት አድርገው ማከናወን እንዳለባቸው የተባለ ነገር የለም።

ተጠኝ መምህራኑ ተማሪዎች ዕህፌትን በተግባር እንዲዕፉና እንዲለማመዱ የመከለስና የመገምገም ተግባራትንም እንዲያከናውኑ የማድረግ ጥረት ሲያደርጉ አልታዩም። በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ሲከናወን የታየው ነገር፣ መምህራኑ በመማሪያ መፅሀፉ ላይ የቀረበውን ይዘት ተማሪዎች በጽሁፍ እንዲመልሱ ከአዘዟቸው በኂላ ተግባሩ የሚወስደውን ጊዜ ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የፃፉትን እንዲያነቡ ይጠይቋቸዋል። በዚህ ጊዜ ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፋቸውን በማንበብ ለጥያቄው መልስ ነው ያሉትን በቃላቸው በመግለፅ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ይገባደዳል። አንዳንድ ፈጣን ተማሪዎች የመልመጃ ደብተሮቻቸውን ይዘው የፃፉትን ሲያነቡ ሌሎቹ እያዳመጡ እንደሚዕፉም በምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የመማር ማስተማር ተራክቦን በተመለከተ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ተማሪዎች በግል የመስራት እድላቸው ከፍተኛ ሆኖ ታይቷል። በአምስተኛ ክፍል ከታዩት ምልከታዎች ሰባቱ (87.5%) በግል የተከናወኑ ሲሆኑ አንዱ (12.5%) በቡድን የተከናወነ መሆኑ ተረጋግጧል። ሌሎች የክፍል ደረጃዎች ስድስተኛ፣ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ (100%) ተማሪዎች በግል የመስራት አጋጣሚዎች ታይተውባቸዋል። በአጠቃላይ የጥንድ፣ የቡድንና የህብረት የመማር ማስተማር ሂደቶች በአምስተኛ ክፍል ከታየው ውጭ ተግባራዊ ሲደረጉ በምልከታው አልታዩም። በምልከታ ወቅት የታየው ተጠኝ መምህራኑ ተማሪዎች በፅሁፍ እንዲመልሱ ሲጠይቁ ተማሪዎች በግል የመሰላቸውን ሲናገሩ አንዳንዶቹም የፃፉትን ሲያነቡ ነው።

ተማሪዎች በክፍልም ሆነ በቤት በሚያከናውኗቸው የዕህፈት ትምህርት ተግባራት ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ በመጨረሻ ስራዎቻቸው ላይ የተካሄዱ ስህተቶችን ለይቶ የማውጣት፣ የሰዋስዋዊም ሆነ የዕሁፍ አወቃቀር እንዲሁም የስርዓተ ነጥብ አፃፃፍ ግድፈቶች እንዲታረሙ የማድረግና ተማሪዎች ከስህተታቸው ተምረው ዕሁፋቸውን የማስተካከል የመምህርና ተማሪ ተራክቦ ከሰባተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎቹ ክፍሎች ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል:: በትክክለኛነት ላይ በማተኮር ከተከናወኑት ተግባራትም በምልከታው የታዩት በአምስተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%)፣ በስድስተኛ ሁለቱ (25%)፣ በሰባተኛ ክፍል አምስቱ (62.5%) እና በስምንተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%) ብቻ ናቸው:: ይሁን እንጅ የቀረቡት የውስንና መር የዕህፈት ተግባራት በመሆናቸው ለትክክለኛነትም መስጠት የነበረበት ትኩረት ከፍተኛ ሆኖ ሳለ ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱን ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ::

ተጠኚ መምህራኑ ለሚያቀርቧቸው የዕህፈት ትምህርት ተግባራት አስረጅ የሚሆኑ ሞዴሎችን የማቅረብ ሁኔታ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው:: በምልከታው እንደታየው በአምስተኛና ስድስተኛ ክፍሎች መምህራኑ በክፍልም ይሁን በቤት ስራ ላቀረቧቸው ተግባራት ሙሉ በሙሉ ሞዴሎችን አላሳዩም:: በአንፃሩ በሰባተኛ ክፍል በአንድ የምልከታ ጊዜ ብቻ ስለነባራዊ ሀቅና የግል አስተያየትን በተመለከተ አስረጅ የሚሆኑ ሞዴሎች የቀረቡ ሲሆን በስምንተኛ ክፍልም እንዲሁ በአንድ የምልከታ ጊዜ ብቻ ለተለያዩ ደብዳቤዎች ሞዴል ያሉትን ማቅረባቸውን ከምልከቱ የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ::

የመማር ማስተማር ክንውኖችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ትንተና በተመለከተ ደግሞ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በሰንጠረዥ አራት ውስጥ ተጠቃለው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

## ሰንጠረዥ 4. የመማር ማስተማር ክንውኖች መግለጫ

| ተ.ቁ | ጽህፈትን የመማር ማስተማር ክንውኖች | የተከናወኑ | | | | | | | | ያልተከናወኑ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ስለዕለቱ ትምህርት ግልፅ መመሪያ መስጠት | 3 | 37.5 | 4 | 50 | 2 | 25 | 5 | 62.5 | 5 | 62.5 | 4 | 50 | 6 | 75 | 3 | 37.5 |
| 2 | ጊዜን በአግባቡ መጠቀም | 4 | 50 | 3 | 37.5 | 6 | 75 | 3 | 37.5 | 4 | 50 | 5 | 62.5 | 2 | 25 | 5 | 62.5 |
| 3 | ስህተትን ማረም | 2 | 25 | 1 | 12.5 | 3 | 37.5 | 4 | 50 | 6 | 75 | 7 | 87.5 | 5 | 62.5 | 4 | 50 |
| 4 | ምገበ መረጃ መስጠት<br>ሀ. የመምህር ምገበ ምላሽ | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | 6 | 75 | 4 | 50 | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 | 2 | 25 | 4 | 50 |
| | ለ. የቢጤ ምገበ ምላሽ | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 5 | አስፈላጊ ሲሆን ገለፃ መስጠት | 6 | 75 | 7 | 87.5 | 5 | 62.5 | 8 | 100 | 2 | 25 | 1 | 12.5 | 3 | 37.5 | | |
| 6 | የቤት ስራ መስጠት | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | | | | | | | | |
| 7 | የክፍል ስራ መስጠት | 2 | 25 | 1 | 12.5 | | | | | 6 | 75 | 7 | 87.5 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 8 | ለመፃፍ ሂደት ተግባሮች ትኩረት መስጠት | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 9 | አስመስሎ መፃፍን (imitation) መጠቀም | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 10 | ፅህፈትን መማር<br>ሀ. በተግባራዊ ልምምድ | 3 | 37.5 | 4 | 50 | 2 | 25 | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 | 4 | 50 | 6 | 75 | 5 | 62.5 |
| | ለ. በመማሪያ መሳሪያነት | 6 | 75 | 7 | 87.5 | 6 | 75 | 5 | 62.5 | 2 | 25 | 1 | 12.5 | 2 | 25 | 3 | 37.5 |
| 11 | ተማሪዎች የግል ገጠመኞቻቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ሀሳባቸውንና ቋንቋቸውን መጠቀማቸው | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |

በሰንጠረዥ አራት እንደተገለፀው ተጠኝ መምህራት ስለዕለቱ ትምህርት ግልፅ መመሪያ መስጠትን በተመለከተ ከስድስተኛና ስምንተኛ ክፍሎች በስተቀር በሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች ዝቅተኛ ሆኖ ተስተውሏል:: ከምልከታ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአምስተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%)፣ በስድስተኛ ክፍል አራቱ (50%)፣ በሰባተኛ ክፍል ሁለቱ (25%) እና በስምንተኛ ክፍል አምስቱ (62.5%) ምልከታዎች ከመማሪያ መፅሀፉ ለተሰጡት የቤት ስራ መልመጃዎች መመሪያዎችንና ምሳሌዎችን ተከትለው መስራት እንዳለባቸው ለተማሪዎች በግልፅ መመሪያ ሲሰጡ የታዩ መሆናቸው በምልከታው የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ:: ቀሪዎቹ መምህራን ግን መማሪያ መፅሀፉን አውጥተው መልመጃዎቹ የሚገኙበትን ገፅና ቁጥር በመንገር እንዲሰሩ ትዕዛዝ ሲያስተላልፉ ታይተዋል::

ለዕህራት ትምህርት ተግባራት የተመደበውን የጊዜ አጠቃቀም በተመለከተ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተጠኝ መምህራን በዕለት ትምህርት ዝግጅት ዕቅዳቸው ላይ ለመግቢያ፣ ለማቅረቢያ፣ ለማጠናከሪያና ለመገምገሚያ ከፋፍለው ያሰፈሩ ቢሆንም፣ ከተደረገው ምልከታ መረዳት እንደተቻለው ከአምስተኛና ከሰባተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች አተገባበሩ ዝቅተኛ ነው:: መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአምስተኛ ክፍል አራቱ (50%)፣ በስድስተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%)፣ በሰባተኛ ክፍል ስድስቱ (75%) እና በስምንተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%)፣ ምልከታዎች መምህራኑ ጊዜያቸውን በአግባቡ የተጠቀሙ መሆናቸውን አመልክተዋል:: ቀሪዎቹ ግን የጊዜ አጠቃቀም ችግሮች እንዳሉባቸው ከምልከታው የተገኙት መረጃዎች ይገልፃሉ::

ተማሪዎች የሰሯቸውን የዕህራት ትምህርት ተግባራት በቃል ወይም በንባብ ሲመልሱ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በማረም ረገድ የመምህራኑ ሚና ከስምንተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል:: ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በአምስተኛ ክፍል ሁለቱ (25%)፣ በስድስተኛ ክፍል አንዱ (12.5%)፣ በሰባተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%) እና በስምንተኛ ክፍል አራቱ (50%) ምልከታዎች ተጠኝ መምህራኑ የተማሪዎችን ስህተት በማረም ሚናቸውን የተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል:: በቀሪዎቹ ግን ይህ ተግባር በምልከታ ሲከናወን አልታየም:: የመምህራኑን ምግበ ምላሽ በተመለከተ ደግሞ ከስድስተኛ ክፍል በስተቀር አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎቹ ለሰሯቸው የዕህራት ትምህርት መልመጃዎች መልስ ሲሆን የሚችል መረጃ ያቀረቡ

መሆናቸውን በምልከታው ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል:: በአምስተኛ ክፍል አምስቱ (62.5%) በስድስተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%) በሰባተኛ ክፍል ስድስቱ (75%) እና በስምንተኛ ክፍል አራቱ (50%) ምልከታዎች በመምህራት የተሰጡትን ምላሾች ያመላከቱ ናቸው:: በቀሪዎቹ ምልከታዎች ግን ተማሪዎች የሰሯቸው ተግባራት ትክክል ይሁኑም አይሁኑ ከግምት ውስጥ ሳይገቡ መምህራኑ ጥያቄውን በማንበብ እጅ ላወጣው ተማሪ እድል በመስጠት እንዲመልስ ያደርጋሉ፤ ከዚያም በመምህራኑ አጭር መልስ ወይም ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው የሚታለፍባቸው ጊዜያቶች መሆናቸውን በምልከታው የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ተማሪዎች ዕህሪትን በመማር ሂደት የመልመጃ ደብተሮቻቸውን ተለዋውጠው ከጓደኞቻቸው ምግበ ምላሽ ያገኙበት ጊዜ በምልከታው አልታየም:: ይህ ተግባር በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን አለመታየቱን ከምልከታው የተገኙ መረጃዎች አመልክተዋል::

ተጠኝ መምህራኑ በአብዛኛው የዕህሪት ትምህርት ይዘቶችን የሚያስተምሩት በገለፃ መሆኑን በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ይገልፃሉ:: ከተካሄዱት ምልከታዎች ውስጥም በአምስተኛ ክፍል ስድስቱ (75%)፣ በስድስተኛ ክፍል ሰባቱ (87.5%)፣ በሰባተኛ ክፍል አምስቱ (62.5%) እና በስምንተኛ ክፍል ስምንቱ (100%) ገለፃዊ (Lecture Method) በሆነ መንገድ የተጠቀሙ ናቸው:: በመማር ማስተማሩ ሂደትም የተማሪዎች ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበር መረጃዎች ጠቁመዋል:: ቀሪዎቹ መምህራን ደግሞ ተማሪዎች በግል የሚሰጣቸውን መልመጃ ሰርተው ሲጠየቁ በሚያቀርቡት መልስ ላይ የተመሰረተ እንደነበር በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል::

ከምልከታ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያስገነዝቡት በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የሚገኙት ተጠኝ መምህራን የቤት ስራ በመስጠት በኩል ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው:: ምልከታዎች በተካሄዱባቸው ጊዜያቶች ሁሉም መምህራን ሙሉ በሙሉ (100%) የቤት ስራዎችን ሰጥተዋል:: በቤት የሚሰሩት መልመጃዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው አተገባበር ግን መጠነኛ ሆኖ ታይቷል:: መምህራኑ በተማሪዎች ለቀረቡት ምላሾች የሚሰጡት አስተያየትም ይሁን ምግበ ምላሽ ከተሰጠው የቤት ስራ ጋር ሲወዳደር አነስተኛ መሆኑን ከምልከታው የተገኙት መረጃዎች ያስረዳሉ:: ተማሪዎች በክፍል እንዲያከናውኗቸው የሚደረጉ የዕህሪት ትምህርት ተግባራትም በሁሉም የክፍል ደረጃዎች እጅግ በጣም ዝቅተኛ ናቸው:: ከተደረጉት ምልከታዎች በአምስተኛ ክፍል ሁለቱ (25%) እና በስድስተኛ ክፍል አንዱ (12.5%) ከታዩት በስተቀር በሌሎቹ ክፍሎች የክፍል ስራ ተሰጥቶ ሲከናወን የሚያሳይ መረጃ የለም::

ተማሪዎች ሂደታዊ ጽህፈትን (Process Writing) ተግባራዊ እንዲያደርጉ የተደረጉ ጥረቶች በመምህራኑ በኩል አልታዩም:: ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት አርቅቀው፣ እየደጋገሙ አርመውና ከልሰው ዕህፈትን እንዲማሩ የማድረግ ሁኔታዎች በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ (100%) አልተከናወነም:: አንድን ሞዴል መነሻ አድርገው ዕህፈትን ሲለማመዱ የሚያሳዩ መረጃዎችም በምልከታው ጊዜ አልታዩም:: በመምህራኑም በኩል አስመስሎ መፃፍን ለማበረታታት የተደረገ ጥረት፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች አልነበረም::

ዕህፈትን በተግባር የማለማመድ ሁኔታ ከስድስተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎቹ የክፍል ደረጃዎች ዝቅተኛ መሆኑን ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ይገልፃሉ:: በክፍል ውስጥ ከተካሄዱ ምልከታዎች በአምስተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%)፣ በስድስተኛ ክፈል አራቱ (50%)፣ በሰባተኛ ክፍል ሁለቱ (25%) እና በስምንተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%) ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረዋል:: ይሁን እንጂ በእነዚህ ምልከታዎች የተከናወኑት ተግባራት ዕህፈትን በተግባር በማለማመድና ክሂሉን በማዳበር በኩል ያላቸው አስተዋፅኦ በቂ እንዳልሆነ ከምልከታው የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ክሂሉን በተግባር ከማለማመድ ይልቅ በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረበውን የዕህፈት ትምህርት ይዘት መሰረት በማድረግ ይዘቱን መግለፅ (በመማሪያ ማስተማሪያነት) እንጂ ዕህፈትን በልምምድ እንዲማሩ የማድረግ ጥረታቸው በጣም ዝቅተኛ ነው:: ምልከታዎች እንደሚገልፁት በአምስተኛ ክፍል ስድስቱ (75%)፣ በስድስተኛ ክፍል ሰባቱ (87.5%)፣ በሰባተኛ ክፍል ስድስቱ (75%) እና በስምንተኛ ክፍል አምስቱ (62.5%)፣ ያከናወኗቸው ተግባራት በገለፃ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ተማሪዎች የግል ገጠመኞቻቸውንና እውቀታቸውን መሰረት አድርገው ሀሳባቸውን በራሳቸው ቋንቋ እንዲገልፁ የተደረገበት ጊዜ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በምልከታ ጊዜ የታየ ነገር የለም:: በውስንና መር ዕህፈት ያዳበሩትን የጽህፈት ችሎታ በነፃ ጽህፈት ሲያጠናክሩትም አልታዩም::

የመምህራንንና የተማሪዎችን ሚና የሚያመለክቱ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ደግሞ በሰንጠረዥ አምስት ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል::

ሰንጠረዥ 5. በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህራንንና የተማሪዎችን ሚና የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ጽህፈትን የመማር ማስተማር ክንውኖች | የተከናወኑ | | | | | | | | ያልተከናወኑ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | | 5ኛ | | 6ኛ | | 7ኛ | | 8ኛ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | የተወሰነና ግልጽ አላማ ይዞ መግባት | 3 | 37.5 | 4 | 50 | 2 | 25 | 4 | 50 | 5 | 62.5 | 4 | 50 | 6 | 75 | 4 | 50 |
| 2 | ተማሪዎች ፅህፈትን በመፃፍ /በተግባር/ የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ መከታተል | 1 | 12.5 | | | 1 | 12.5 | | | 7 | 87.5 | 8 | 100 | 7 | 87.5 | 8 | 100 |
| 3 | የተማሪዎችን ጽሁፍ አንባቢና ገምጋሚ መሆን | | | 1 | 12.5 | 2 | 25 | 3 | 37.5 | 8 | 100 | 7 | 87.5 | 6 | 75 | 5 | 62.5 |
| 4 | ተማሪዎች በራሳቸው እንዲሰሩ ማድረግ | | | | | | | | | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 |
| 5 | ሁሉም ነገር በራሱ በመምህሩ ብቻ እንዲከናወን ማድረግ | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | 8 | 100 | | | | | | | | |

በሰንጠረዥ አምስት እንደተገለፀው ተጠኝ መምህራኑ የተወሰነና ግልፅ ዓላማ ይዞ የመግባትና ተግባራዊ የማድረግ ሁኔታ በስድስተኛና ስምንተኛ ክፍሎች ከታየው በስተቀር፣ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍሎች ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል:: በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት እንደታየው ሁሉም መምህራን በዕለት ትምህርት ዝግጅት እቅዳቸው ላይ የሰፈረ ዓላማ ይዘው መግባታቸው በምልከታው ታይቷል:: ይሁን እንጅ ሁሉም የቀረቡትን የፅህፈት ትምህርት ተግባራት የተወሰነ ዓላማን በግልጽ የሚያመለክቱ አይደሉም:: ከተካሄዱት ምልከታዎች

በአምስተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%)፣ በስድስተኛ ክፍል አራቱ (50%)፣ በሰባተኛ ክፍል ሁለቱ (25%) እና በስምንተኛ ክፍል አራቱ (50%)፣ ስለ ፅህፈት በማስተማር ላይ በማተኮር የቀረቡ እንደነበሩ በምልከታው የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ይሁን እንጂ ስለምንና እንዴት ፃፉ ለሚሉት ጥያቄዎች በቂ ምላሽ የሚሰጡ ሆነው አልታዩም::

ተማሪዎች ፅህፈትን በተግባር የሚማሩበትን ሁኔታ የማመቻቸትና የመከታተል የመምህራኑ ጥረት በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል:: ከተካሄዱት ምልከታዎች በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍሎች አንድ አንድ ጊዜ መምህራኑ በተማሪዎች መካከል እየተመላለሱ በግልና በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ሲያበረታቱ መታየታቸውን ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሳይተዋል:: በአንፃሩ ከመምህራኑ አቅም በላይ የሆኑ ችግሮችም ተስተውለዋል:: ተማሪዎቹ የተቀመጡባቸው ወንበሮች ተንቀሳቃሽ አለመሆን በትምህርቱ አተገባበር ላይ ጫና የሚያሳድሩ እንደነበሩ መረጃዎች ይገልፃሉ:: በምልከታው ተማሪዎች በመልመጃ ደብተሮቻቸው ላይ የፃፉትን አንብበው የማሻሻያ ሀሳብ የሰጡ ወይም የግምገማ ውጤት ያስቀመጡ መምህራን እጅግ በጣም ውስን ናቸው:: በምልከታው በስድስተኛ ክፍል አንዱ (12.5%)፣ በሰባተኛ ክፍል ሁለቱ (25%) እና በስምንተኛ ክፍል ሶስቱ (37.5%) የተማሪዎቻቸውን ደብተር ተመልክተው ፊርማዎቻቸውን ያስቀመጡ ቢሆንም ምን እንደተፃፈ ያረጋገጡት ነገር የለም:: በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በምልከታው እንደታየው ተማሪዎች በራሳቸው የሚያከናውኗቸው የጽህፈት ትምህርት ተግባራት አልታዩም:: ከመምህራኑ ጫና ነፃ ሆኖ የቀረበ ነገር የለም:: ሁሉም የጽህፈትን ትምህርት እውቀት በማስተማር በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡትን መልመጃዎች በመስራት ላይ ያተኩራሉ::

4.1.3. **ከመምህራን በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ትንተና**

ለመምህራን በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ የመጀመሪያው ክፍል ጥያቄዎች ስለመምህራን ሁኔታ /ዳራ/ ለማወቅ የቀረቡ ነበሩ:: መጠይቁን በትክክል ሞልተው ከመለሱት አስራ ሁለት መምህራን የተገኙት ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ሰንጠረዥ 6. የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ መግለጫ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | ፆታ | | ዕድሜ | | | | | | የአገልግሎት ዘመን | | | | የትምህርት ደረጃ | | የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ | | የሚያስተምሩት የክፍል ጊዜ ብዛት | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | 20-25 | 26-30 | 31-35 | 36-40 | 41-45 | 46-50 | 1-5 | 6-10 | 11-15 | 16-20 | ዲፕሎማ | ዲግሪ | አማርኛ | ሌላ | 20-25 | 26-30 | እንግሊዘኛ | ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ (CPD) | የማታ | ወርክሾፕ | የክረምት |
| 1 | ደምበጫ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | - | 2 | 1 | 1 | - | - | - | - | 2 | - | - | - | 2 | - | 2 | - | 1 | 1 | - | 2 | - | - | - |
| 2 | አርበኞች አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 1 | 1 | - | 2 | - | - | - | - | 1 | 1 | - | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | - | 2 | 1 | - | - |
| 3 | ዋድ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 3 | 2 | 2 | 3 | - | - | - | - | 5 | - | - | - | 5 | - | 2 | - | - | 5 | - | 5 | - | - | 1 |
| 4 | አዲስ አምባ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | - | 3 | - | - | 1 | 2 | - | - | - | 1 | - | 2 | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 1 | 3 | - | - | - |
| | ድምር | 4 | 8 | 3 | 6 | 1 | 2 | - | - | 8 | 2 | - | 2 | 12 | - | 12 | - | 1 | 11 | 1 | 12 | 1 | - | 1 |

በሰንጠረዥ ስድስት እንደተገለፀው የወንዶችና የሴቶች መምህራን ቁጥር ከፍተኛ ልዩነት አሳይቷል:: የወንዶች ብዛት አራት (33.33%) ሲሆን የሴቶች ደግሞ ስምንት (66.66%) ነው:: ተጠኝ መምህራኑ በሙሉ አማርኛን አብይ የትምህርት ዘርፍ አድርገው የሰለጠኑና በትምህርት ደረጃቸውም ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ሁሉም የዲፕሎማ ምሩቃን ናቸው:: አብዛኞቹ መምህራን ከስድስት አመት በታች በቋንቋ ማስተማር ላይ ያሉ ናቸው:: በአላቸው የአገልግሎት ዘመን ሙያቸውን ለማሻሻል የወሰዷቸው የተለያዩ የስልጠና አይነቶች መኖር አለመኖራቸውን ተጠይቀው አብዛኞቹ ተከታታይ የሙያ ላይ ስልጠና (CPD) እንደወሰዱ ገልፀዋል:: ይሁን እንጅ ይህ ስልጠና በቀጥታ ከሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት ጋር የሚገናኝ ሳይሆን አጠቃላይ ስለመማር ማስተማሩ የሚቀርብ ተከታታይ ስልጠና ነው::

መምህራኑ በአብዛኛው በሳምንት የሚያስተምሩት ክፍለ ጊዜ ብዛት ከሃያ ስድስት ክፍለ ጊዜ በላይ በመሆኑ የተወሰነ ጫና እንዳለባቸው መገንዘብ ተችሏል:: በማስተማር ሙያ ላይ ያላቸው ቆይታም አብዛኞቹ አጭር ጊዜ የሚባል ይሁን እንጂ ወቅታዊ ከሆነ የጽህፈት ትምህርት የማስተማር ስነ-ዘዴ ጋር ያላቸው ትውውቅ እጅግ በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል::

መምህራኑ በስልጠና ቆይታቸው ቋንቋውንና ታላሚውን የፅህፈት ትምህርት የማስተማር ስነ ዘዴ መተግበር የሚያስችል እውቀትና ክህሎት ማግኘት አለማግኘታቸውን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተናን በተመለከተ ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ ሰንጠረዦች እንዲቀርቡ ተደርጓል::

ሰንጠረዥ 7. የመምህራን የዕውቀትና ክህሎት ሁኔታ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች በቁጥርና በፐርሰንት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችል ምን ያህል ስልጠና በተማሩበት ማሰልጠኛ ወስደዋል? | 11 | 91.66 | | | 1 | 8.33 | | | | |
| 2 | አማርኛን ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና ከወሰዱ የዕህፌት ትምህርቶችን ለማስተማር ቴክኒካዊ ክህሎትንና እውቀትን አዳብሮልዎታል? | | | 9 | 75 | 3 | 25 | | | | |

በሰንጠረዥ ሰባት በተራ ቁጥር አንድ ላይ እንደተገለፀው አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና በተማሩበት ማሰልጠኛ መውሰድ አለመውሰዳቸውን ለማረጋገጥ መጠይቁን ከሞሉት አስራ ሁለት መምህራን መካከል አስራ አንዱ (91.66%) በቂ ስልጠና መውሰዳቸውን ሲመልሱ፣ አንዱ (8.33%) በቂ ስልጠና ወስጃለሁ ለማለት አልደፍርም ሲል መልስ ሰጥቷል:: በተራ ቁጥር ሁለት ደግሞ አማርኛን ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና ከወሰዱ የዕህፌት ትምህርትን ለማስተማር ቴክኒካዊ ክህሎትንና እውቀትን ያዳበረላቸው ወይም ያላዳበረላቸው መሆኑን እንዲመልሱ ከተጠየቁትም ዘጠኙ (75%) በመጠኑ አዳብሮልኛል ብለው የመለሱ ሲሆን፣ ሌሎቹ ሶስቱ (25%) በቂ ስልጠና ወስጃለሁ ለማለት አልደፍርም በማለት መልስ የሰጡ ናቸው::

መምህራን የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል ምን አይነት የዕህፌት ትምህርት ቴክኒኮችን ተጠቅመው እንደሚያስተምሩ ለማረጋገጥ ደግሞ በሰንጠረዥ ስምንት እንደሚከተለው ቀርቧል::

ሰንጠረዥ 8. የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል የመምህራንን የዕህፌት ትምህርት አተገባበር የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች በቁጥርና በፐርሰንት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3 | የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በጥንድ መድበው ዕህፌትን በመወያየትና በመተራረም እንዲማሩ ያደርጋሉ? | 2 | 16.66 | 4 | 33.33 | 4 | 33.33 | 2 | 16.66 | | |
| 4 | በተራ ቁጥር ሶስት ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አሉታዊ ከሆነ አማራጭ ነው የሚሉት የትኛው ነው? | 3 | 25 | 3 | 25 | 5 | 41.66 | | | 1 | 8.33 |

መምህራኑ በሰንጠረዥ ስምንት በተራ ቁጥር ሶስት የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ወይም በጥንድ በጥንድ መድበው ዕህፌትን በመወያየትና በመተራረም እንዲማሩ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ሁለቱ (16.66%) ሁልጊዜ አደርጋለሁ ሲሉ፣ አራቱ (33.33%) ደግሞ በአብዛኛው አደርጋሁ ያሉ ናቸው፤ ሌሎቹ አራቱ (33.33%) በመጠኑ አደርጋለሁ ብለው የመለሱ ሲሆን፣ ሁለቱ (16.66%) ደግሞ በአብዛኛው አላደርግም በማለት የመለሱ መሆናቸውን መረጃዎቹ ያመለክታሉ:: በተጨማሪም በተራ ቁጥር አራት ላይ፣ በተራ ቁጥር ሶስት ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አሉታዊ ከሆነ አማራጭ ነው የሚሉት የትኛው ነው ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት አማራጭ መልስ፣ ሶስቱ (25%) ለደረጃው የቀረበውን ትምህርት በገለፃ ማስተማር ሲሉ፣ ሌሎች ሶስቱ (25%) ደግሞ ተጨማሪ መማሪያ ክፍል በመክፈትና ቁጥራቸውን በመቀነስ ብለዋል፤ አምስቱ (41.66%) ለተማሪዎች የቤት ስራ በመስጠት የሰሩትን መልመጃ

በማረም ያሉ ሲሆን፣ አንዱ (8.33%) ደግሞ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መልስ በመፃፍ እንዲያስተካክሉ በማድረግ ማስተማር በአማራጭነት የሚወስዱ መሆናቸውን ገልፀዋል::

መምህራን በመማሪያ መፅሀፉና በማስተማሪያ መፅሀፉ የቀረቡትን የፅህፈት ትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች ከስነ ዘዴ አኳያ ያላቸውን የአተገባበር ሁኔታ እንዲሁም ለተማሪዎች የሚያቀርቧቸው የክፍልም ሆነ የቤት ስራ ተግባራትን በተመለከተ ያላቸውን ድርሻ ለመቃኘት ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኙት መረጃዎች በሰንጠረዥ ዘጠኝ እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ሰንጠረዥ 9. የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች በመምህራን ያላቸውን የመማር ማስተማር ክንውን አተገባበር የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች በቁጥርና በፐርሰንት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | ፅህፈትን ለመማሪያና ክሂሉን ለማዳበሪያ በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎችና ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑት እንዴት ነው? | | | 2 | 16.66 | 5 | 41.66 | 4 | 33.33 | 1 | 8.33 |
| 6 | ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡትን ይዘቶችና መልመጃዎች በሚመለከት በመምህሩ መምሪያ የተጠቀሰውን የአቀራረብ ስልት/የማስተማሪያ ዘዴ ይተገብሩታል? | 2 | 16.66 | 9 | 75 | 1 | 8.33 | | | | |
| 7 | ለተማሪዎች በፅሁፍ የሚመለስ የቤት ስራ ይሰጣሉ? | 2 | 16.66 | 8 | 66.66 | 2 | 16.66 | | | | |
| 8 | ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመጻፍ ልምምድ የሚያደርጉበት የክፍል ስራ ይሰጣሉ? | 2 | 16.66 | 5 | 41.66 | 5 | 41.66 | | | | |
| 9 | በፅሁፍ እንዲመልሱ የተሰጣቸውን መልመጃ ተማሪዎች ይሰራሉ? | 4 | 33.33 | 7 | 58.33 | 1 | 8.33 | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ ዘጠኝ በተራ ቁጥር አምስት እንደሚታየው ዕህሬትን ለመማሪያና ክሂሉን ለማዳበሪያ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎችንና ይዘቶችን በክፍል ውስጥ መምህሩን እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጓቸው ለማረጋገጥ በጽሁፍ መጠይቁ ከቀረበው ጥያቄ የተገኙት ምላሾች ሁለቱ (16.66%) በክፍልና በቤት ስራ የሄፋትን እንዲያነቡ በማድረግ እንደሆነ፣ አምስቱ (41.66%) ደግሞ በዕሁፍ ሰርተው እርስ በርስ እንዲተራረሙ በማድረግ መሆኑን፣ አራቱ (33.33%) በክፍል ውስጥ በቡድን ተወያይተው በየግላቸው እንዲፅፉ በማድረግና በማረም እንደሆነ ሲገልፁ አንዱ (8.33%) አንድን የጽሁፍ ሞዴል ተከትለው እንዲፅፉ በማድረግና በማረም መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል:: እንዲሁም በተራ ቁጥር ስድስት ዕህሬትን ለማስተማር የቀረቡትን ይዘቶችና መልመጃዎች በሚመለከት በመምህሩ መምሪያ የተጠቀሰውን የአቀራረብ ስልት ወይም የማስተማር ዘዴ ምን ያህል እንደሚተገብሩት ከተገኙት መረጃዎች ሁለቱ (16.66%) ሙሉ በሙሉ እተገብረዋለሁ፣ ዘጠኙ (75%) በአብዛኛው እተገብረዋለሁ ሲሉ፣ አንዱ (8.33%) ደግሞ አልፎ አልፎ እተገብረዋለሁ በማለት ምላሽ የሰጡ መሆናቸው ተመልክቷል::

መምህራኑ ለተማሪዎች በዕሁፍ የሚመለስ የቤት ስራ መስጠት አለመስጠታቸውን ለማወቅ በተራ ቁጥር ሰባት ከቀረበላቸው ጥያቄ ከተገኙት ምላሾች ውስጥ ሁለቱ (16.66%) ሁል ጊዜ እሰጣለሁ በማለት ሲመልሱ፣ ስምንቱ (66.66%) ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ ብለዋል፣ ሁለቱ (16.66%) ግን አልፎ አልፎ እሰጣለሁ በማለት መልስ የሰጡ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ:: በሌላ በኩል በተራ ቁጥር ስምንት መምህራን ለተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ የመፃፍ ልምምድ የሚያደርጉበት የክፍል ስራ ማቅረብ አለማቅረባቸውን ከመለሱት ሁለቱ (16.66%) ሁል ጊዜ እንደሚያቀርቡ የገለፁ ሲሆን፣ አምስቱ (41.66%) ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሰጡ ገልፀዋል:: ሌሎቹ አምስቱ (41.66%) ግን አልፎ አልፎ እንደሚያቀርቡ ምላሽ የሰጡ መሆናቸው ታውቋል:: በተራ ቁጥር ዘጠኝ ደግሞ ተማሪዎች በዕሁፍ እንዲመልሱ የሚሰጣቸውን ተግባር መስራት አለመስራታቸውን መምህራኑ እንዲገልፁ ከቀረበላቸው ጥያቄ አራቱ (33.33%) ሁልጊዜ ይሰራሉ፣ ሰባቱ (58.33%) አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ ብለው የመለሱ ሲሆን፣ አንዱ (8.33%) አልፎ አልፎ እንደሚሰሩ መልሳቸውን ሰጥተዋል::

ተማሪዎች የዕህሬት ትምህርት ተግባራትን ሲያከናውኑ የመምህራን ምግበ ምላሽ (Feedback) ምን እንደሚመስል ለመመልከት ደግሞ በሰንጠረዥ አስር እንደሚከተለው ቀርቧል::

ሰንጠረዥ 10. የመምህራን ምግበ ምላሽ ሁኔታ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች በቁጥርና በፐርሰንት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 10 | ተማሪዎች የሚሰሩት የዕህፈት መልመጃ ይታረምላቸዋል? | 1 | 8.33 | 3 | 25 | 8 | 66.66 | | | | |
| 11 | በሚያስተምሩበት ክፍል የተማሪዎችን ስራ አርመው ምግበ ምላሽ (Feedback) ወይም የማሻሻያ ሀሳብ ሰጥተው ያውቃሉ? | 9 | 75 | 3 | 25 | | | | | | |
| 14 | አርመው ምግበ ምላሽ (Feedback) የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ምላሽ መሰረት ስህተታቸውን አስተካክለው እንደገና እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | 9 | 75 | | | 3 | 25 | | | | |

በሰንጠረዥ አስር በተራ ቁጥር አስር የመምህራንን ምግበ-ምላሽ (Feedback) ለመቃኘት ተማሪዎች የሚሰሩት የዕህፈት መልመጃ ምን ያህል በመምህራን እንደሚታረም ለማወቅ ከቀረበው ጥያቄ አንዱ (8.33%) ሁልጊዜ ይታረምላቸዋል ያለ ሲሆን፣ ሶስቱ (25%) ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ይታረምላቸዋል በማለት መልስ ሰጥተዋል፤ ሌሎች ስምንቱ (66.66%) ግን አልፎ አልፎ እንደሚታረምላቸው የገለፁ ናቸው:: ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተየያዘ መልኩ በተራ ቁጥር አስራ አንድ መምህራኑ በሚያስተምሩበት ክፍል የተማሪዎችን ስራ አርመው ምግበ ምላሽ ወይም የማሻሻያ ሀሳብ ምን ያህል ጊዜ ሰጥተው እንደሚያውቁ ለቀረበላቸው ጥያቄ ዘጠኙ (75%) ሁልጊዜ እሰጣለሁ ሲሉ፣ ሶስቱ (25%) ደግሞ በአብዛኛው እሰጣለሁ በማለት ምላሽ መስጠታቸው ታውቋል:: እንዲሁም በተራ ቁጥር አስራ አራት መምህራኑ አርመው ምግበ-ምላሽ የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ምላሽ መሰረት ስህተታቸውን አስተካክለው እንደገና እንዲፅፉ ማድረግ አለማድረጋቸውን ከመለሱት ዘጠኙ (75%) ሁልጊዜ አደርጋለሁ ያሉ ሲሆን፣ ሶስቱ (25%) ደግሞ አልፎ አልፎ አደርጋለሁ በማለት መልስ የሰጡ ናቸው::

መምህራኑ የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን እንዴት እንደሚያከናውኑ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ በሰንጠረዥ አስራ አንድ እንደሚከተለው ቀርቧል::

ሰንጠረዥ 11. የመምህራንን አተገባበር ስልት የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች በቁጥርና በፐርሰንት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 12 | ተማሪዎች በመረጡት፣ እርስዎ በሚሰጧቸው ወይም በመፅሀፉ ውስጥ በሚቀርብ ርዕስ፣ አንቀፅ ወይም ድርሰት እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | | | 6 | 50 | 6 | 50 | | | | |
| 13 | ተማሪዎች የዕህፈት መልመጃ ሲሰሩ በአብዛኛው እንዲያተኩሩበት የሚያበረታቷቸው በምን ላይ ነው? | 4 | 33.33 | 2 | 16.66 | 2 | 16.66 | | | 4 | 33.33 |
| 15 | በክፍል የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የእርስዎ ተግባር የትኛው ነው? | 9 | 75 | 3 | 25 | | | | | | |
| 16 | ለዕህፈት ክሂል መልመጃ በክፍል ውስጥ ለሚቀርበው ክንውን በምንጭነት የሚጠቀሙት የትኛውን ነው? | 5 | 41.66 | 1 | 8.33 | 5 | 41.33 | | | 1 | 8.33 |
| 17 | ተማሪዎች በማስመሰል ለመፃፍ የሚጠቀሙበትን የታላሚ ፅሁፍ ሞዴል አቅርበው በመተንተን ያሳያሉ? | 2 | 16.66 | 3 | 25 | 7 | 58.33 | | | - | - |

በሰንጠረዥ አስራ አንድ የመምህራኑን የዕህፈት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው በተራ ቁጥር አስራ ሁለት ላይ መምህራኑ ተማሪዎች በመረጡት፣ እርስዎ በሚሰጧቸው ወይም በመፅሀፉ በሚቀርብ ርዕስ፣ አንቀፅ ወይም ድርሰት እንዲፅፉ ያደርጋሉ ተብለው ከተጠየቁት መካከል ስድስቱ (50%) አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለሁ ያሉ ሲሆን፣ ስድስቱ (50%) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩት ምላሽ ሰጥተዋል:: በተራ ቁጥር አስራ ሶስት ተማሪዎች የዕህፈት መልመጃ ሲሰሩ በአብዛኛው እንዲያተኩሩበት የሚያበረታቷቸው በምን ላይ ነው በሚል ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ የሰጡት መልስ፣ አራቱ

(33.33%) በፅሁፋቸው ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ ሁለቱ (16.66%) በሚገልፁት ሀሳብ ተከታታይነትና ግጥምጥምነት ላይ በማለት አመልክተዋል፤ ሌሎቹ ሁለቱ (16.66%) በመፃፍ ሂደቱ በሚያከናውኗቸው የማቀድ፣ የማርቀቅና የመከለስ ተግባራት ላይ ያሉ ናቸው፤ በመጨረሻ አራቱ (33.33%) ደግሞ ሀሳባቸውን በመግለፅና በፅሁፍ መግባባት መቻላቸው ላይ እንደሆነ አመልክተዋል።

በተራ ቁጥር አስራ አምስት በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የእርስዎ ተግባር የትኛው ነው በሚል ለቀረበው ጥያቄ፣ ዘጠኙ (75%) በጥንድ፣ በቡድንና በህብረት የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሆነ ሲገልፁ፣ ሶስቱ (25%) ደግሞ የተማሪዎችን ስራ መከታተልና መቆጣጠር በማለት መልስ የሰጡ ናቸው። በተራ ቁጥር አስራ ስድስት ለፅህፈት ትምህርት መልመጃ በክፍል ውስጥ ለሚቀርበው ክንውን በምንጭነት የሚጠቀሙት የትኛውን ነው ለሚለው ጥያቄ፣ አምስቱ (41.66%) ሙሉ በሙሉ መርሀ ትምህርቱን እንደሆነ ሲገልፁ፣ አንዱ (8.33%) ደግሞ ሙሉ በሙሉ የመምህሩን መምሪያ በማለት የመለሱ ናቸው፤ አምስቱ (41.66%) ግን ሙሉ በሙሉ የመማሪያ መፅሀፉን ያሉ ሲሆን፣ አንዱ (8.33%) ደግሞ ሙሉ በሙሉ ሌሎች ማጣቀሻ ማቴሪያሎችን እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል። በመጨረሻም በተራ ቁጥር አስራ ሰባት ተማሪዎች በማስመሰል ለመፃፍ የሚጠቀሙበትን የታላሚ ፅሁፍ ሞዴል አቅርበው በመተንተን ማሳየት አለማሳየታቸውን ለሚያረጋግጠው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣ ሁለቱ (16.66%) ሁልጊዜ እንደሚያሳዩ፣ ሶስቱ (25%) ደግሞ በአብዛኛው እንደሚያሳዩና ሰባቱ (58.33%) በመጠኑ እንደሚያሳዩ የገለፁ ናቸው።

በክፍል ሶስት መምህራኑ በፅህፈት ትምህርት አተገባበር ወቅት የሚያቀርቧቸውንና በተደጋጋሚ ተማሪዎች የሚለማመዱባቸውን መልመጃዎች በቅደም ተከተል እንዲገልፁ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ በሰንጠረዥ አስራ ሁለት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 12. በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የዕህሬት ትምህርት ተግባራት የድግግሞሽ መጠንን የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | መልመጃዎች | የመልመጃዎች ተደጋጋሚነት ደረጃ በቁጥርና በፐርሰንት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 1 | | ደረጃ 2 | | ደረጃ 3 | | ደረጃ 4 | | ደረጃ 5 | | ደረጃ 6 | | ደረጃ 7 | | ደረጃ 8 | | ደረጃ 9 | | ደረጃ 10 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ለቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች መስጠት | 3 | 25 | 3 | 25 | 4 | 33.33 | | | 1 | 8.33 | | | 1 | 8.33 | | | | | | |
| 2 | በቀረቡት የቃላት ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን መመስረት | 2 | 16.66 | 3 | 25 | 1 | 8.33 | 3 | 25 | 2 | 16.66 | 1 | 8.33 | | | | | | | | |
| 3 | በጅምር የቀሩትን አረፍተ ነገሮች ማሟላት | | | | | 3 | 25 | 3 | 25 | 3 | 25 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | | | | |
| 4 | እስተዋፅኦ ማዘጋጀትና አንቀፅ መፃፍ | | | | | | | | | 1 | 8.33 | 5 | 41.66 | 3 | 25 | 1 | 8.33 | 2 | 16.66 | | |
| 5 | የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለምሳሌ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን፣ ምሳሌያዊ አባባሎችን፣ ትኒያዎችን፣ መፍታት | | | | | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | | | 2 | 16.66 | 3 | 25 | 1 | 8.33 | 2 | 16.66 | 2 | 16.66 |
| 6 | ድርሰት፣ ደብዳቤ፣ ሪፖርት መጻፍ | | | 1 | 8.33 | | | 1 | 8.33 | 2 | 16.66 | | | | | 4 | 33.33 | 2 | 16.66 | 2 | 16.66 |
| 7 | ዕሁፍን ማሳጠርና ግጥምን ወደ ስድ ዕሁፍ መቀየር | | | | | | | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | 2 | 16.66 | | | 5 | 41.66 | 2 | 16.66 |
| 8 | የፈጠራ ስራዎችን ለምሳሌ ግጥም፣ አጭር ታሪክ፣ ጭውውት መፃፍ | | | | | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | | | 2 | 16.66 | 1 | 8.33 | 2 | 16.66 | 1 | 8.33 | 4 | 33.33 |
| 9 | ክስሌዳ ላይ በመገልበጥ ማስታወሻ መያዝ | 3 | 25 | 2 | 16.66 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | | | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | | | 2 | 16.66 |
| 10 | የቃል ጽህፈት መፃፍ | 4 | 33.33 | 3 | 25 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | 1 | 8.33 | | | | | 2 | 16.66 | | | | |

በሰንጠረዥ አስራ ሁለት እንደተገለጸው በክፍል ውስጥ የቀረቡት የዕህፈት ትምህርት ተግባራት ምን ያህል በተጠኝ መምህራት ተደጋግመው እንደቀረቡ የሚጠቁሙ ናቸው:: በይበልጥ ከሚደጋገመው በመጀመር በተራ ቁጥር አንድ ለቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ የሚፈለግላቸው መልመጃዎች ያላቸውን የተደጋጋሚነት ደረጃ የገለጹት፣ ሶስቱ (25%) በአንደኛ ደረጃ፣ ሌሎቹ ሶስቱ (25%) በሁለተኛ ደረጃ፣ አራቱ (33.33%) በሶስተኛ ደረጃ፣ አንዱ (8.33%) በአምስተኛ ደረጃ እና ሌላው አንዱ (8.33%) በሰባተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጠውታል:: በተራ ቁጥር ሁለት፣ በቀረቡት የቃላት ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በመመስረት ለሚከናወነው መልመጃ፣ ሁለቱ (16.6%) አንደኛ ደረጃ፣ ሶስቱ (25%) ሁለተኛ ደረጃ፣ አንዱ (8.33%) ሶስተኛ ደረጃ፣ ሶስቱ (25%) አራተኛ ደረጃ፣ ሁለቱ (16.6%) አምስተኛ ደረጃ እና አንዱ (8.33%) ስድስተኛ ደረጃ ሰጥተውታል:: በተራ ቁጥር ሶስት በጅምር የቀሩትን አረፍተ ነገሮች ማሟላትን በተመለከተ፣ ሶስቱ (25%) ሶስተኛ ደረጃ፣ በድጋሚ ሶስቱ (25%) አራተኛ ደረጃ፣ ሌሎቹ ሶስቱ (25%) አምስተኛ ደረጃ፣ አንዱ (8.33%) ስድስተኛ ደረጃ፣ እንዲሁም አንዱ (8.33%) ሰባተኛ ደረጃና የመጨረሻው አንዱ (8.33%) ስምንተኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጡ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ::

አስተዋፅኦ በማዘጋጀት አንቀፅ መፃፍን ለሚመለከቱ መልመጃዎች ደግሞ፣ አንዱ (8.33%) በአምስተኛ ደረጃ፣ አምስቱ (41.66%) በስድስተኛ ደረጃ፣ ሶስቱ (25%) በሰባተኛ ደረጃ፣ አንዱ (8.33%) በስምንተኛ ደረጃና ሁለቱ (16.66%) በዘጠነኛ ደረጃ ላይ በማመልከት ድግግሞሻቸውን ገልፀዋል:: የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለምሳሌ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን፣ ምሳሌያዊ አባባሎችንና ቅኔዎችን በመፍታት ላይ የሚያተኩረውና በቁጥር አምስት ላይ ለቀረበው መልመጃ፣ አንዱ (8.33%) በሶስተኛ ደረጃ በድጋሚ አንዱ (8.33%) በአራተኛ ደረጃ፣ ሁለቱ (16.66%) በስድስተኛ ደረጃ፣ ሶስቱ (25%) በሰባተኛ ደረጃ፣ አንዱ (8.33%) በስምንተኛ ደረጃ፣ ሁለቱ (16.66%) በስምንተኛ ደረጃ እና ሌሎች ሁለቱ (16.66%) በዘጠነኛ ደረጃ ላይ ያመለከቱ መሆናቸው ታውቋል:: በተራ ቁጥር ስድስት ድርሰት፣ ደብዳቤና ሪፖርትን በመጻፍ ለሚከናወኑ መልመጃዎች ደግሞ፣ አንዱ (8.33%) ሁለተኛ ደረጃ፣ ሌላው አንዱ (8.33%) አራተኛ ደረጃ፣ ሁለቱ (16.66%) አምስተኛ ደረጃ፣ አራቱ (33.33%) ስምንተኛ ደረጃ፣ ሁለቱ (16.66%) ዘጠነኛ ደረጃ እና ቀሪዎቹ ሁለቱ (16.66%) አስረኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጡ ናቸው:: በተራ ቁጥር ሰባት ጽሁፍን በማሳጠርና ግጥምን ወደ ስድ ጽሁፍ በመቀየር ለሚካሄዱ የጽህፈት መልመጃዎች፣ አንዱ (8.33%) አራተኛ ደረጃን፣ ሌላው አንዱ (8.33%) አምስተኛ ደረጃን፣

በተጨማሪ አንዱ (8.33%) ስድስተኛ ደረጃን፣ ሁለቱ (16.66%) ሰባተኛ ደረጃን፣ አምስቱ (41.66%) ዘጠነኛ ደረጃን እና ሁለቱ (16.66%) አስረኛ ደረጃን በመምረጥ ያመለከቱ ሆነው ተገኝተዋል።

በተራ ቁጥር ስምንት የፈጠራ ስራዎችን ለምሳሌ ግጥም፣ አጭር ታሪክና ጭውውትን በመፃፍ ለሚከናወኑ መልመጃዎች መምህራኑ የሰጧቸው ደረጃዎች ደግሞ፣ አንዱ (8.33%) ሶስተኛ ደረጃን፣ ሌላው አንዱ (8.33%) አራተኛ ደረጃን፣ ሁለቱ (16.66%) ስድስተኛ ደረጃን፣ አንዱ (8.33%) ሰባተኛ ደረጃን፣ ሁለቱ (16.66%) ስምንተኛ ደረጃን፣ አንዱ (8.33%) ዘጠነኛ ደረጃንና አራቱ (33.33%) አስረኛ ደረጃን የመረጡ መሆናቸውን መረጃዎች አሳይተዋል። ተማሪዎች ከሰሌዳ ላይ በመገልበጥ ማስታወሻ የሚይዙበትን ደረጃ የሚለካ በተራ ቁጥር ዘጠኝ ለቀረበው ተግባር ሶስቱ (25%) አንደኛ ደረጃን፣ ሁለቱ (16.66%) ሁለተኛ ደረጃን፣ አንዱ (8.33%) ሶስተኛ ደረጃን፣ ሌላው አንዱ (8.33%) አራተኛ ደረጃን፣ በተጨማሪ ሌላው አንዱ (8.33%) አምስተኛ ደረጃን፣ እንዲሁም አንዱ (8.33%) ሰባተኛ ደረጃን፣ በመጨረሻ አንዱ (8.33%) ስምንተኛ ደረጃን እና ሁለቱ (16.66%) አስረኛ ደረጃን ያመለከቱ ናቸው። በመጨረሻ በተራ ቁጥር አስር ለሚካሄደው የቃል ጽህፈት መልመጃ የተሰጠው ደረጃ አራቱ (33.33%) በአንደኛ ደረጃ፣ ሶስቱ (25%) በሁለተኛ ደረጃ፣ አንዱ (8.33%) በሶስተኛ ደረጃ፣ ሌላው አንዱ (8.33%) በአራተኛ ደረጃ፣ በተጨማሪ አንዱ (8.33%) በአምስተኛ ደረጃኛ ሁለቱ (16.66%) በስምንተኛ ደረጃ ላይ በቅደም ተከተል ማስቀመጣቸውን የተገኙት መረጃዎች አመልክተዋል።

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ያተኮረው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የጽህፈት ትምህርትን ለማስተማር በቀረቡት ስነ ዘዴዎች አተገባበር ላይ ነው። ጥናቱ በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የክሂል ትምህርቱ እየተሰጠ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ሞክሯል። ከማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ ከምልከታና ከመምህራን የዕሁፍ መጠይቆች የተገኙት መረጃዎችም ተተንትነዋል። ከዚህ ትንተና በመነሳት ጥናቱ የደረሰበት ውጤት በሚከተለው አኳኋን ተብራርቶ ቀርቧል።

በመጀመሪያ ደረጃ የታዩት በመርሀ ትምህርቱ ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ናቸው። የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በመማር ማስተማር ሂደቱ የቀረቡትና የተከናወኑት ተግባራት በአብዛኛው መርሀ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ ናቸው። በመርሀ ትምህርቱ፣

በመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ለመፃፍ ክሂል የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል:: ክሂሉን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶችም በአብዛኛው የውስንና መር (Controlled and Guided writing) የዕህፈት ተግባራትን የተከተሉ ሲሆኑ ለነፃ ዕህፈት (Free Writing) እና ለሂደታዊ ዕህፈት (Process Writing) ተግባራት የተሰጠው ትኩረት ግን አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል:: አብዛኞቹ ተግባራትም በክለሳ ድርሳኑ በቁጥር 2.5.1. እንደተገለጸው ተማሪዎች በፃፉት የመጨረሻ ስራ ላይ የሚያተኩሩና ስህተት የመፍጠር አጋጣሚ እንዳያገኙ የሚያደርጉ ናቸው::

ይሁን እንጂ በመማር ማስተማር ሂደቱ የሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች ብቻቸውን የተማሪዎችን በዕሁፍ ሀሳብን የመግለዕና የዕሁፍ ተግባቦት የመፍጠር ችሎታቸውን ሊያዳብሩ የማይችሉ የውስንና የመር የዕህፈት ተግባራት ናቸው:: ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲያከናውኗቸው የቀረቡት ተግባራትም በአብዛኛው ብዙ ማሰብንና ማፍለቅን የማይጠይቁ ሰፋ ያለ የቃላት ቅንጅትን የማይጠይቁ ቋንቋውን ለመማርና ስህተትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መሆናቸውን ከምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: ከመምህራን በፅሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰበው መረጃም በተደጋጋሚ የሚቀርቡት የዕህፈት ትምህርት ተግባራት የቃላትን፣ የሀረጋትን፣ የአባባሎችንና የአረፍተ ነገሮችን ፍች የመፃፍ፣ አረፍተ ነገሮችን የመስራት፣ ቃላትንና ሀረጋትን በቅደም ተከተል የመፃፍ መልመጃዎች መሆናቸውን አመላካቾች ናቸው::

የመምህራን የዕህፈት ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ትምህርቱን በመግቢያ በመጀመር ተማሪዎችን በተገቢው ሁኔታ ሲያነቃቁ የታዩት መምህራን አነስተኛ ናቸው:: የክሂል ትምህርቱንም በተግባር መፃፍን ማለማመድ መከለስና መገምገምን ተጠኝ መምህራኑ ሲተገበሩ የሚያሳዩ መረጃዎች የሉም:: በመማር ማስተማር ሂደቱም የታየው ተማሪዎች በግል የመስራት እድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው:: ይህም ተማሪዎች ሀሳብ ለሀሳብ ተደጋግፈው ክሂሉን እንዳያዳብሩ ክፍተት የሚፈጥር ነው:: ይህ ውጤትም ተማሪዎች የዕህፈት ችሎታቸውን ማዳበር እንዲችሉ እርስ በራሳቸው እንዲፃፉ ማድረግ፣ የጻፉትን ጽሁፍ ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት እንዲሰጡ መደረግ አለበት በሚል በክለሳ ድርሳኑ በቁጥር 2.4. ላይ ከሰፈረው ከእነ Attkins (1996) ሀሳብ ጋር አይስማማም::

በትክክለኛነት ላይ ማተኮርን በተመለከተ ምንም እንኳ በአብዛኛው የሚቀርቡት የውስንና መር የፅህፈት ትምህርት ተግባራት ቢሆኑም መምህራኑ፣ ተማሪዎቹ የሰሯቸውን የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ከስርዓተ-ነጥብ፣ ከሰዋስው፣ ወዘተ አንፃር ተከታትለው የማስተካከል የመምህርና ተማሪ ተራክቦ ከሰባተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎቹ ክፍሎች ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል:: ተጠኝ መምህራኑ ለሚያቀርቧቸው የጽህፈት ትምህርት ተግባራት አስረጅ የሚሆኑ ሞዴሎች የመጠቀም ሁኔታ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች እጅግ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል::

ፅህፈትን የመማር ማስተማር ቴክኒኮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተመለከተ በምልከታ ከተገኙት ውጤቶች መረዳት የሚቻለው ተጠኝ መምህራኑ ስለፅሁፉ ትምህርት ግልፅ መመሪያ ለተማሪዎች በመስጠት በኩል ያሳዩት እንቅስቃሴ መጠነኛ ሆኖ መገኘቱን ነው:: የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ሲጠቀሙበት የታዩት የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተጠኝ መምህራን ሲሆኑ በስድስተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ያለው አተገባበር ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል:: ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትኩረት ተደርጎባቸው፣ እርማት ተሰጥቶባቸው እንዲስተካከሉ የተደረገበት ሁኔታ ከስምንተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎቹ በጣም አነስተኛ ነው:: ከመምህራን የሚሰጡ ምግበ ምላሾች በአብዛኛው ቃላዊ ቢሆኑም ከስድስተኛ ክፍል በስተቀር በሌሎች ክፍሎች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል:: ይሁን እንጂ ከተሰጣቸው ምግበ ምላሽ ተነስተው ሲያስተካክሉ ወይም ስህታቶቻቸውን ሲያርሙ የታዩት ተማሪዎች ውስን ናቸው:: በተጨማሪም ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ደብተራቸውን ተለዋውጠው ሲተራረሙ የታዩበት የምልከታ ጊዜ የለም:: ይህ ውጤት በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራን ለተማሪዎች ጠቃሚና ገንቢ ምግበ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል በሚል በ2.4. ከቀረበው መርህ ጋር ይቃረናል::

ተማሪዎች በቤት ሰርተውት እንዲመጡ የሚታዘዙበት ጊዜ ከፍተኛ ነው:: ሁሉም ተጠኝ መምህራን በአብዛኛው ይህን ይፈፅማሉ:: ይሁን እንጅ የእያንዳንዱን ተማሪ የመልመጃ ደብተር ማረምም ይሁን ለሰሩት የጽህፈት ስራ አስረጅ ሊሆን የሚችል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስተካከያ በትክክል የመፃፍ ጉዳይ አነስተኛ ነው:: የክፍል ስራን በተመለከተ ተማሪዎች በክፍል እንዲያከናውኗቸው የተደረጉ የጽህፈት ትምህርት ተግባራት በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ዝቅተኛ ናቸው:: የተወሰኑት የአምስተኛና የስድስተኛ ክፍል መምህራን ብቻ የሰጡ ሲሆን ሌሎቹ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መምህራን ሲሰጡ አልታዩም:: ይህም ተማሪዎች የፅህፈት ክሂላቸውን በመምህራቸው ታግዘው እንዳያዳብሩ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ክፍለ ጊዜው

የተመደበው፣ ተማሪዎች ቃላትንና ሰዋስውን ብቻ እንዲማሩበት ሳይሆን ዕህፈትንም በክፍል እንዲለማመድ ጭምር ነው በሚል በክለሳ ድርሳኑ ከቀረበው ሀሳብ ጋር አይስማማም።

በሂደት የዕህፈት ትምህርትን ለመማር፣ ለመፃፍ ሂደት ተግባሮች የተሰጡ ትኩረቶች በምልከታ ወቅት አልታዩም። ተማሪዎች በመምህራቸው ታዘው የሚፈፅሙት እንጅ በራሳቸው ሀሳባቸውን አፍልቀው፣ አርቅቀውና ከልሰው የሰሩት የዕህፈት ትምህርት ተግባራት አልነበረም። አስመስሎ መፃፍን በተመለከተም የቀረበላቸው ሞዴል በጣም ውስን ነው።

መምህራኑ የዕህፈት ትምህርትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ወደ ትክክለኛው የዕህፈት ክሂል ተግባራት እንዲገቡና እንዲለማመዱ የሚያደርጉት ጥረት ቢኖርም እጅግ በጣም አነስተኛ ሆኖ ታይቷል። በአንፃሩ የዕህፈት ትምህርቱ የተማሪዎችን የዕህፈት ችሎታ እያደገ እንዲሄድ የሚያደርግ ሳይሆን በመማሪያ መሳሪያነት የቀረበ ነው። ተማሪዎች የግል ገጠመኞቻቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ሀሳባቸውንና ቋንቋቸውን ተጠቅመው የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን ሲያከናውኑ አለመታየታቸውን ከተደረገው ምልከታ መገንዘብ ተችሏል። ይህ በተለይ ተማሪዎች የነፃ ዕህፈት ተግባራትን ለማከናወን የሚጠቀሙበት ሆኖ ሳለ በራሳቸው መንገድ የሚለማመዱበትና ክሂሉን የሚያዳብሩበት ስልት ተግባራዊ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል። ይህም ጽህፈት ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት በተከታታይ መለማመድን የሚጠይቅ የክሂል አይነት ነው በሚል በክለሳ ድርሳኑ በ2.3. ከተገለፀው ሀሳብ ጋር ይቃረናል።

በመማር ማስተማር ሂደቱ የመምህራንን ሚና ለመፈተሽ ከቀረቡት ጥያቄዎች ከተካሄደው ትንተና በመነሳት የተገኘው ውጤት መምህራን የተወሰነና ግልፅ ዓላማ ይዞ ወደ ክፍል በመግባት የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን ለማከናወን ያደረጉት ጥረት መጠነኛ ሆኖ ታይቷል። ምንም እንኳ ሁሉም ተጠኚ መምህራን የእለት ትምህርት ዝግጅት እቅድ አዘጋጅተው የተገኙ ቢሆንም ከሚያስተምሩት ተግባር ጋር ሙሉ በሙሉ ግልፅ በሆነ መንገድ አለመቅረቡን መረጃዎች ያሳያሉ። ተማሪዎች ዕህፈትን በተግባር የሚማሩበትን ሁኔታ የሚመቻቸትና የመከታተል ተግባራት ሲያከናውኑ የታዩት መምህራን ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ተማሪዎች የሰሯቸውን የዕህፈት ትምህርት መልመጃዎች አንብበው የማሻሻያ ሀሳብ የሰጡ መምህራን ቁጥርም አጅግ በጣም አነስተኛ ነው። መምህራኑ የተማሪዎችን የመልመጃ

ደብተሮች ተመልክተው ፊርማቸውን ያስቀመጡ ቢኖሩም እንኳ ምን እንደተገፈ በውል ያረጋገጡት ነገር የለም።

ተማሪዎች የተሰጣቸውን የጽህፈት ትምህርት ተግባራት በራሳቸው እንዲከናወን የማድረግ ሁኔታ አልታየም። መምህራን ከመማሪያ መፅሃፋ ላይ የሚሰጡት መልመጃ ሙሉ በሙሉ በተማሪው የሚከናወን ሳይሆን በራሳቸው በመምህራን ገለፃ የሚቋጭበት ሁኔታ ነው ያለው። ሁሉም ነገር በመምህሩ አማካኝነት የሚፈፀምበት ሁኔታ ጎልቶ መታየቱን መረጃዎች አመልክተዋል።

ለመምህራን ከቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ ከተካሄደው ትንተና የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው መምህራኑ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችል ምን ያህል ስልጠና በተማሩት ማሰልጠኛ ወስደዋል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአንዱ መምህር በስተቀር ሁሉም በቂ ስልጠና መውሰዳቸውን ገልፀዋል። አማርኛን ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና ከወሰዱ የፅህፈት ትምህርትን ለማስተማር ቴክኒካዊ ክህሎትንና እውቀትን አዳብሮልዎታል ተብለው ከተጠየቁትም ዘጠኙ በመጠኑ አዳብሮልኛል ብለው ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ በቂ ስልጠና ወስጃለሁ ለማለት አልደፍርም ብለው የመለሱ ናቸው። ይሁን እንጂ በክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራኑ በቂ ስልጠና ወስጃለሁ ብለው ከመለሱት አኳያ በክፍል ውስጥ የክሂል ትምህርቱን በተገቢ ሁኔታ ሲተገብሩት አልታዩም።

መምህራን የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል ምን አይነት የፅህፈት ትምህርት ቴክኒኮችን ተጠቅመው እንደሚያስተምሩ ተጠይቀው ከተካሄደው ትንተና የተገኘው ውጤት መምህራኑ ተማሪዎችን በቡደን ወይም በጥንድ በጥንድ መድበው ፅህፈትን በመወያየትና በመተራረም እንዲማሩ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አብዛኞቹ በአብዛኛው እንደሚያደርጉትና በመጠኑ እንደሚያደርጉ የገለፁ ናቸው። ይሁን እንጂ በምልከታ በተካሄደው ፍተሻ፣ መምህራኑ ይህን ሲያደርጉ አልታዩም። በተራ ቁጥር ሶስት ለቀረበው ጥያቄ መልሰዎ አሉታዊ ከሆነ አማራጭ ነው የሚሉት የትኛው ነው ተብለው ከተጠየቁት አብዛኞቹ የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎች የሰሩትን መልመጃ በማረም የክሂል ትምህርቱን ማስተማር እንደማራጭ አቅርበዋል። ሆኖም ግን መምህራኑ፣ ተማሪዎቹ በቤት ስራ የሰሯቸውን መልመጃዎች በማረም፣ የማስተካከልና የመገምገም ተግባራትን በአግባቡ ሲያከናወኑ በምልከታ

ጊዜ አልታዩም:: ይህም ተማሪዎች ክሂሉን እንዲያዳብሩ የሚያደርጋቸው አይሆንም:: ይህም በ2.4. ከቀረበውና ተማሪዎች ከመምህራቸውም ሆነ ከጓደኞቻቸው ተገቢ ምግበ ምላሽ ማግኘት አለባቸው ከሚለው ሀሳብ ጋር የማይስማማ ነው::

ተጠኝ መምህራት በመማሪያ መፅሀፋና በማስተማሪያ መፅሀፉ የቀረቡትን የፅሀፈት ትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች ከስነ ዘዴ አኳያ ያላቸውን የአተገባበር ሁኔታ በተመለከተ ከተካሄደው ትንተና የተገኘው ውጤት አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች የሰሯቸውን የፅሀፈት ትምህርት ተግባራት እርስ በርስ እንዲተራረሙ በማድረግ እንደሆነ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ አራቱ ደግሞ በክፍል ውስጥ በቡደን ተወያይተው በየግላቸው እንዲፅፉ በማድረግና በማረም እንደሆነ የገለፁ ናቸው:: በክፍል ውስጥ የተካሄደው ምልከታ ግን መምህራኑ እነዚህን ተግባራት ሲያከናውኑ አያሳይም:: ይህም በ2.4. በክለሳ ድርሳኑ ተማሪዎች እንዲያቅዱ፣ እንዲያረቁና እንዲከልሱ ማበረታታት ያስፈልጋል ከሚለው ሀሳብ ጋር ይቃረናል:: በመምህሩ መምሪያ የቀረቡትን የፅሀፈት ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ተከትለው በአብዛኛው ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ዘጠኙ መምህራን ገልፀዋል:: ይሁን እንጅ በመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረቡት የመማር ማስተማር ክንውኖች በበቂ ሁኔታ ተብራርተው የቀረቡ አለመሆናቸውን ከተደረገው የሰነድ ምርመራ መመልከት ተችሏል::

መምህራኑ ለተማሪዎች በፅሁፍ የሚመለሱ የቤት ስራዎች እንደሚሰጧቸው አብዛኞቹ መምህራን አረጋግጠዋል:: በምልከታ የተገኘው መረጃም ከመምህራኑ ምላሽ ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል:: ተማሪዎች የመፃፍ ልምምድ የሚያደርጉበት የክፍል ስራ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሰጡ አምስቱ መምህራን የገለፁ ሲሆን በተመሳሳይ መንገድም ሌሎቹ አምስቱ አልፎ አልፎ መስጠታቸውን ገልፀዋል:: በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ግን እንደሚያስረዱት መምህራኑ ተማሪዎች በክፍል ፅሀፈትን እንዲለማመዱ የሚያደርጉበት ጊዜ እጅግ በጣም የተወሰነና አተገባበሩም የክሂል ትምህርቱን ሊያዳብር የሚችል ሆኖ ያለመገኘቱን ነው:: ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸውን ለማዳበር የሚሰጧቸውን መልመጃዎች በአብዛኛው እንደሚያከናውኑ አብዛኞቹ መምህራን አመልክተዋል:: ይህም በምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር በትንሹ የሚስማማ ነው::

ተማሪዎች የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን ሲያከናውኑ የመምህራን ምግብ-ምላሽ ምን እንደሚመስል ከተካሄደው ትንተና የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች የሚሰሯቸውን የዕህፈት ትምህርት ተግባራት አልፎ አልፎ እንደሚያርሙላቸው የገለፁ ናቸው:: ይሁን እንጅ በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው መምህራኑ የተማሪዎችን ደብተር ሲያርሙ የታዩበት ጊዜ እጅግ በጣም ውስን ነው:: የተማሪዎችን ስራ አርመው ምግበ ምላሽ ወይም የማሻሻያ ሀሳብ ሰጥተው ያውቃሉ ተብለው በፅሁፍ መጠይቁ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞቹ መምህራን ሁልጊዜ እንደሚያደርጉ የገለፁ ቢሆንም በምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር በአብዛኛው የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል:: ተማሪዎች በተሰጣቸው ምላሽ መሰረት ስህተታቸውን አስተካክለው እንደገና እንዲፅፉ ማድረጋቸውን አብዛኞቹ መምህራን አመልክተዋል:: ከተሰጣቸው ምላሽ ተነስተው ሲያስተካክሉ የታዩት ተማሪዎች ግን ጥቂት እንደነበሩ የተደረገው ምልከታ ያሳያል::

መምህራኑ የዕህፈት ትምህርትን የሚተገብሩበትን መንገድ ለመፈተሽ በፅሁፍ መጠይቁ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች ከተደረገው ትንተና በመነሳት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው፣ ተማሪዎች በመረጡት፣ እርስዎ በሚሰጧቸው ወይም በመፅሀፉ ውስጥ በሚቀርብ ርዕስ፣ አንቀፅ ወይም ድርሰት እንዲፅፉ ያደርጋሉ ተብለው ከተጠየቁት ስድስቱ፣ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያደርጉ የገለፁ ሲሆን፣ ሌሎቹ ስድስቱ ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩት ገልፀዋል:: ይሁን እንጅ በምልከታ ወቅት ተማሪዎቹ ይህን ተግባር ሲያከናውኑ አልታዩም:: የክሂል ትምህርቱ በሚሰጥበት ወቅት በአብዛኛው ተማሪዎች ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው የሚያበረታቷቸውን መምህራኑ ተጠይቀው፣ አብዛኞቹ በፅሁፋቸው ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይና ሀሳባቸውን መግለፅና በፅሁፍ መግባባት መቻላቸው ላይ መሆኑን ገልፀዋል:: በምልከታ የተገኘው መረጃ ግን እንደሚያመለክተው መምህራኑ የቀረበውን መልመጃ እንዲሰሩ ከማዘዝ ውጭ ተማሪዎች ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በግልፅ ያሉት ነገር አልታየም::

በክፍል ውስጥ ፅህፈትን የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የእርስዎ ተግባር ምንድን ነው ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎች በጥንድ፣ በቡድንና በህብረት የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሆነ ሲገልፁ፣ ሶስቱ ደግሞ የተማሪዎችን ስራ መከታተልና መቆጣጠር ሲሉ የገለፁ ናቸው:: ሆኖም ግን በምልከታ ከተገኘው መረጃ በመነሳት የመምህራኑ ተግባር እጅግ በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል:: መምህራኑ ለፅህፈት ትምህርት

መልመጃዎች ወይም በክፍል ውስጥ ለሚቀርበው ክንውን በምንጭነት የሚጠቀሙት የትኛውን የማስተማሪያ መሳሪያ እንደሆነ ከተጠየቁት አብዛኞቹ መምህራን፣ አምስቱ መርሀ ትምህርቱን የሚጠቀሙ እንደሆነ፣ በተጨማሪ ሌሎቹ አምስቱ መማሪያ መፅሀፉን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልፁ ሁለቱ የመምህሩን መምሪያና ሌሎች ማጣቀሻ ማቴሪያሎችን ሙሉ በሙሉ እንደሚተገብሯቸው ገልፀዋል:: በምልከታ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ተጠኝ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ይዘውት የገቡትና ሲተገብሩት የታየው የማስተማሪያ መሳሪያ ግን መማሪያ መፃህፉን ብቻ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል:: ተማሪዎች በማስመሰል ለመፃፍ የሚጠቀሙበትን የታላሚ ፅሁፍ ሞዴል አቅርበው በመተንተን የማቅረብ ሁኔታ አብዛኞቹ መምህራን በመጠኑ እንደሚያሳዩ የገለጹ ሲሆን፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ሁልጊዜና በአብዛኛው እንደሚያቀርቡ ጠቁመዋል:: ይሁን እንጂ ምልከታ በተካሄደባቸው በሁሉም ክፍለ ጊዜዎች መምህራኑ ይህን የፅህፈት ትምህርት ሂደት ሲያከናውኑ የሚያሳዩ መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም::

ተጠኝ መምህራኑ በፅህፈት ትምህርት አተገባበር ወቅት የሚያቀርቧቸውንና በተደጋጋሚ ተማሪዎች የሚለማመዱባቸውን መልመጃዎች በቅደም ተከተል እንዲገልፁ ከተጠየቁት ጥያቄዎች በመነሳት ከተደረገው ትንተና የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው መምህራኑ በይበልጥ በተደጋጋሚ ሁኔታ የሚተገብሯቸው የፅህፈት ትምህርት ተግባራት ለቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች መስጠት፣ በቀረቡት የቃላት ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ ከሰሌዳ ላይ በመገልበጥ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግና በቃል መፃፍ መሆናቸውን አመልክተዋል:: ምንም እንኳን ሁሉንም ተግባራት በምልከታ ወቅት ማግኘት ባይቻልም ከተገኙት ሌሎች መረጃዎች በመነሳት የውስንና መር የፅህፈት ተግባራት በአብዛኛው መቅረባቸውን የሚያመላክት ነው::

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራ ክልል ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የዕህፌትን ክሂል ለማስተማር የቀረቡትን ስነ ዘዴዎች አተገባበር መፈተሽ ሲሆን፣ ስነ ዘዴዎቹ ከመማሪያና ማስተማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸውን ትስስር፣ በመምህራን ያላቸውን አተገባበር፣ የተማሪዎችን ሚናና በትግበራ ሂደቱም የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን የቃኘ ነው።

በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በሰነድ ምርመራ በክፍል ውስጥ ምልከታና በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት ከተሰበሰቡ በኋላ አስፈላጊው ቁጠራ ተደርጎባቸው በመቶኛ (%) ተሰልተው ተተንትነዋል። መረጃዎቹን መሰረት በማድረግም ጥናቱ የደረሰበት ውጤት ተብራርቶ ቀርቧል።

በደረጃው በስራ ላይ የሚገኘው መርሀ ትምህርት ውስጥ የዕህፌት ትምህርት የማስተማር ዘዴዎች (የመማር ማስተማር ክንውኖች) በመማሪያና ማስተማሪያ መፅሀፎች ውስጥ ያላቸው አቀራረብና በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደቱ ያላቸው አተገባበር ምን እንደሚመስል በተደረገው የሰነድ ምርመራ በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ለዕህፌት ትምህርት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ክሂሉን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶችም በአብዛኛው የውስንና መር የዕህፌት ተግባራት ናቸው። ይሁን እንጅ ለሂደታዊና ለነፃ ዕህፌት ተግባራት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ ታውቋል።

የመምህራን የዕህፌት ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ ከተካሄደው የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ እንደሚያመለክቱት መምህራኑ የክሂል ትምህርቱን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ በተግባር እንዲለማመዱ፣ የፃፉትን እንዲከልሱና እንዲገመግሙ በማድረግ ሲያስተምሩ የታዩበት ጊዜ አለመኖሩ ተረጋግጧል። በተጨማሪም ተማሪዎች ከመነሻው ትምህርቱን ተግባራዊ እንዲያደርጉ በመምህራኑ የተሰጣቸው ግፊት (ማነቃቃት) እጅግ በጣም አነስተኛ መሆኑ ታውቋል። ተማሪዎች በፅሁፍ ሀሳባቸውን እንዲገልፁና ከጓደኞቻቸው ምላሽ

እንዲያገኙ አልተደረገም:: የቀረቡት የውስንና የመር የዕህፈት ተግባራት (Controlled and Guided writing) በትክክለኛነት ላይ ያተኩሩ ቢሆኑም መምህራኑ ተማሪዎች ለሰሯቸው የዕህፈት ትምህርት መልመጃዎች ከስርዓተ-ነጥብ፣ ከሰዋስው፣ ከቅርፅ፣ ወዘተ. አካያ ተከታትለው የሰጡት ማስተካከያ አነስተኛ ነው:: ለቀረቡት ተግባራት ለአስረጅነት ያቀረቧቸው ሞዴሎችም ዕጅግ በጣም የተወሰኑ ናቸው::

መምህራኑ በእለቱ ለሚቀርበው የዕህፈት ትምህርት የሚሰጡት መመሪያ የተብራራና በአብዛኛው ግልፅ አለመሆኑ ታውቋል:: በዕለት ትምህርት ዝግጅታቸው ከፋፍለው ያስቀመጡትን ጊዜ በአግባቡ የሚፈፅሙት እጅግ በጣም ውስን የሆኑ መምህራን መሆናቸው የተደረገው ምልከታ ያሳያል:: በመማር ማስተማር ሂደቱም ተማሪዎች የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ተከታትሎ በማረምና በማስተካከል በኩል የተደረገው የመምህራን ምግበ ምላሽ (Feedback) መጠነኛና ቃላዊ መሆኑ ተረጋግጧል:: ተማሪዎችም ከተሰጣቸው ምላሽ ተነስተው ሲያስተካክሉ የታዩበት ጊዜ በጣም ውስን መሆኑ ታውቋል::

ተማሪዎች በቤታቸው ሰርተውት እንዲመጡ የሚሰጣቸው የቤት ስራ ከፍተኛ መሆኑ ታውቋል:: ይሁን እንጂ የመልመጃ ደብተሮቻቸውን የማረምም ሆነ የማስተካከያ ሀሳብ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በትክክል የመፃፍ ሁኔታ አነስተኛ ነው:: በክፍል የሚሰጡት የዕህፈት መልመጃዎችም ቢሆኑ እጅግ በጣም ውስን ናቸው:: ይህ በመሆኑ ተማሪዎች ከመምህራቸው የሚያገኙት እገዛ አነስተኛ ሆኗል:: ተማሪዎች በመምህራን ታዘው የሚፈፅሟቸው እንጅ በራሳቸው ተነሳስተው ሀሳብ አፍልቀው፣ አርቅቀውና ከልሰው ያከናወኑት የዕህፈት ትምህርት ተግባራት አልነበሩም::

መምህራን፣ ተማሪዎች ወደ ትክክለኛው የዕህፈት ትምህርት ተግባራት እንዲገቡና እንዲለማመዱ የሚያደርጉት ጥረት ቢኖርም እንኳ እጅግ በጣም አነስተኛ መሆኑን የተደረገው ምልከታ ያስረዳል:: ተማሪዎቹ ነፃ ሆነው ገጠመኞቻቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ሀሳባቸውንና ቋንቋቸውን ተጠቅመው የዕህፈት ትምህርት ተግባራትን ሲያከናውኑ አለመታየታቸው ታውቋል:: የክሂል ትምህርቱን ተግባራት የሚማሩበትን ሁኔታ የማመቻቸትና የመከታተል ጉዳይም በመምህራኑ ዘንድ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ ታውቋል:: ተማሪዎቹ የሚፅፏቸው መልመጃዎች በመምህራኑ ሲነበቡም ሆነ ሲገመገሙ የታዩባቸው ጊዜያቶች ውስን

ናቸው:: ጥቂት መምህራን ተማሪዎች የሰሯቸውን መልመጃዎች ቢያርሙም እንኳ የተሻሉውን ነገር በሚገባ ተመልክተው እንዳልሆነ የተካሄደው የክፍል ውስጥ ምልከታ ያረጋግጣል::

ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን የጽህፈት ትምህርት ተግባራት በራሳቸው እንዲከናወን የማድረግ ሁኔታ በመምህራኑ ዘንድ አልተደረገም:: መምህራኑ ከመማሪያ መጻህፍቱ ላይ የሚሰጧቸው መልመጃዎች ሙሉ በሙሉ በተማሪው የሚከናወኑ ሳይሆን በራሳቸው በመምህራን ገለፃ የሚቋጭበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል:: ይህም ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያደርጉትን ጥረት የሚቀንስ ነው::

ምንም እንኳ መምህራን አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በቂ ስልጠና ወስጃለሁ በማለት በፅሁፍ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ የሰጡ ቢሆንም፣ በተግባር የፅህፈት ትምህርትን ለማስተማር የቀረቡትን የመማር ማስተማር ክንውኖች (ስነ-ዘዴዎች) በአግባቡ ሲያከናውኑ አልታዩም::

በአጠቃላይ በአንደኛ ደረጃ ለሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ውስጥ የፅህፈትን ትምህርት ለማስተማር የቀረቡት ስነ ዘዴዎች በደረጃው በሚገኙት ክፍሎች (ከ5ኛ-8ኛ) ያላቸው አተገባበር እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነና ተማሪዎች በደረጃቸው ሊያዳብሩት የሚገባውን የመፃፍ ክሂል ከግብ የማያደርስ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል::

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ወደፊት ምንና እንዴት ባለ ሁኔታ መሰራት አለበት በሚል መነሻ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት መፍትሄዎች በአጥኚው ቀርበዋል::

- መምህራን በክሂሉ ዙሪያ የሚቀርቡትን ተግባራት በአግባቡ ለማከናወን እንዲችሉ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ፅህፈትን ለማስተማር የቀረቡት የመማር ማስተማር ክንውኖች በመምህሩ መምሪያ ላይ ሰፋ ባለ ሁኔታ ተብራርተው ቢቀርቡ፣
- የመምህራን የፅህፈት ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት መምህር ተኮር ከመሆን አልፎ ሙሉ በሙሉ ተማሪ ተኮር የሚሆንበት መንገድ ቢፈጠር፣

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የዕህፊት ትምህርት ተግባራትን ማከናወን መቻላቸው የመምህሮቻቸውን እገዛ ሊያተርፍላቸው ስለሚችል ለቋንቋ ትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ የሚራዘምበት ሁኔታ በሚመለከተው አካል ቢመቻች፣
- የመምህራን ምግብ ምላሽ (Feedback) የክሂል ትምህርቱን ለማዳበር ወሳኝ በመሆኑ ተማሪዎች በቤታቸውም ይሁን በክፍል ለሚያከናውኗቸው የዕህፊት ትምህርት ተግባራት ተገቢ እርማትና ማስተካከያ የሚሰጡበት ሁኔታ ቢኖር፣
- መምህራን የዕህፊት ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ የሚመለከታቸው አካላት ለመምህራን ሙያቸውን መሰረት ባደረገ መልኩ ስልጠናዎች ቢሰጡና የመማማር መድረኮች ቢፈጠሩና
- በመማር ማስተማር ሂደቱ ተማሪዎች የዕህፊት ትምህርት ተግባራትን ሲሰሩ የመምህራን ክትትልና ግፊት አስፈላጊ በመሆኑ ለክሂል ትምህርቱ አተገባበር ያመች ዘንድ ተማሪዎች የሚቀመጡባቸው ወንበሮች ተንቀሳቃሽ እንዲሆኑ ቢደረግ መልካም ነው።

## ዋቢ. መፃህፍት


ባዬ ይማም (1987) የአማርኛ ሰዋስው:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

ማረው ዓለሙ (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል ለሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ ጥናት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

ሰሎሞን ተሰማ (1987) "የበ.ጤ እርማ ተግባራዊነትና ውጤታማነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

ሰሎሞን ዮሐንስ (1991) "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

ሰይድ ይመር (1993) "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ የቀረቡትን የፅሁፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ (የመማር ማስተማር ሂደት) ግምገማ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

ስዩም ከበደ (1988) "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

ትምህርት ሚኒስቴር (1997) የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ከ5ኛ-8ኛ ክፍል:: (ተሻሽሎ የተዘጋጀ):: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

አለም እሸቱ (1995) "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር" ከጥቅምት 25-29/1995 ዓ.ም ለአማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደጥናት የቀረበ:: አዲስ አበባ፣ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት:: (ያልታተመ)::

አለም እሸቱ (1997) መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አፃፃፍ:: (ሶስተኛ እትም):: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ (1997) አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አምስተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

________ (1997) አማርኛ የመምህሩ መምሪያ አምስተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.::

________ (1996) አማርኛ መማሪያ መጻህፍ ስድስተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

________ (1996) አማርኛ የመምህሩ መምሪያ ስድስተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

________ (1997) አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ሰባተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

________ (1997) አማርኛ የመምህሩ መምሪያ ሰባተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ በት.መ.ማ.ማ.ድ ታተመ::

________ (1997) አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ስምንተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.::

________ (1997) አማርኛ የመምህሩ መምሪያ ስምንተኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.::

ዕጌ ታደሰ (1992) "ለዕህፌት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መፃህፍት ላይ የተካሄደ የይዘት ትንተና ግምገማ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

Attkins, J. and et al. (1996) Skills Development Methodology. (Part II). Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Badger, R. and W. Goodith (2000) A Process Genre Approach to Teaching Writing. ELT Journal 54/2. pp153-160

Barr, R. and J. Barbara (1997) Teaching Reading and Writing in Elementary Classroom. New York: Longman.

Breen, M.P. (1987) "Contemporary Paradigms in Syllabus Design." (Part one). Language Teaching: The International Language Abstract Journal for Language Teachers and Applied Linguistics. Vol. 20, No.2, pp.81-91.

Brown, H.D. (1994) Principles of Language Learning and Teaching. (3rd ed.). New Jersey: Prentice Hall Regents.

Byrne, D. (1988) Teaching Writing Skills. Singapore: Language Group Ltd.

Doll, R. C. (1977) Curriculum Improvement: Decision Making and Process. (3rd ed.). Boston: Allyn and Bacon, Inc.

Dubin, F. and E. Olshtain (1986) Course Design: Development Program and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Duke, H. (1983) Writing Through Sequence: A Process Approach. Oxford: Oxford University Press.

Dyer, B. (1996) L1 and L2 Composition Theories: Hillocks Environmental Mode Task-based Language Teaching. ELT Journal 50/41, pp. 312-317.

Fullan, M. G (1992) The New Meaning of Educational Change. (2nd ed.). London: Cassell Educational Ltd.

Harmer, J. (1991) The Practice of English Language Teaching. London: Longman Press.

Hutchinson, T and A. Waters (1987) English for Specific Purposes: A Learning-Centred Approach. Cambridge: Cambridge University Press.

Hedge, T. (1988) Writing. Oxford: Oxford University Press.

Horowitz, D. M. (1986) "What Professors Actually Require: Academic Tasks of the ELS Classroom" TESOL Quarterly. 20/3. 445-464.

Kroll, B. (1990) Second Language Writing. Cambridge: Cambridge University Press.

Lewy, A. (1977) Planning the School Curriculum. Paris: UNESCO Press.

McDonough, J. and G. Shaw (1993) Materials and Methods in ELT. Oxford: Blakwell.

Moore, C. (1995) Reading and Writing in Elementary Classrooms. London: Longman.

Murray, D. (1982) Learning by Teaching: Selected Articles on Writing and Teaching. New York: Heinemann.

Nunan, D. (1988) Syllabus Design. Oxford: Oxford University Press.

________ (1989) Designing Tasks for the Communicative Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Oliva, P.F. (1988) Developing the Curriculum. (2nd ed.). London: Scott, Foresman and Company.

Ornstein, A.C. and F.P. Hunkins (1988) Curriculum: Foundations, Principles and Issues. New Jersey: Prentice Hall Inc.

Pasner, G. J. (1992) Analysing the Curriculum. New York: McGraw Hill, Inc.

Pincas, A. (1982) Teaching English Writing. London: Macmillan Publisher Ltd.

Pratt, E. (1980) Curriculum: Design and Development. New York: Harconrt Brace Jovanovich Pubs.

Raimes, A. (1983) Techniques in Teaching Writing. Oxford: Oxford University Press.

Reid, J. M. (1993) Teaching ESL Writing. New Jersey: Prentice Hall Regents.

Richards, J. C. (1990) The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J. C. (2001) Curriculum Development in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J. C. and J. Rodgers (1985) Methods: Approach Design and Procedure. TESOL Quarterly Vol. 16, No. 2, pp.237.

Sommer, R. and B. Sommer (1980) A Practical Guide to Behavioral Research: Tools and Techniques. Oxford: Oxford University Press.

Ur, P. (1996) A Course in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Yalden, J. (1987) Principles of Course Design for Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

## ዕህፈትን የመማር ማስተማር ክንውን ምልከታ መከታተያ ዝርዝር (Checklist)

የት/ቤቱ ስም ____________

ምልከታ የሚካሄድበት ምድብ ______ ፈረቃ _______ ክ.ጊዜ _______ ሰዓት____

ምልክታውን ያካሄደው መምህር ኮድ ________

የትምህርቱ ርዕስ________________

መመሪያ:- ከዚህ በታች ሶስት የዕህፈት ትምህርት መከታታያ ሊስቶች ቀረበዋል:: በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን በጥሞና በማንበብ ተስማሚ ነው ለምትሉት አማራጭ መልስ የ "X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ

**ሀ**

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴ ትግበራ | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1 | ትምህርቱን በመግቢያ በመጀመር ተማሪዎችን ማነቃቃት | | |
| 2 | በተግባር መፃፍን ማለማመድ መከለስና መገምገም | | |
| 3 | የመማር ማስተማር ተራክቦ<br>ሀ. በግል መስራት | | |
| | ለ. በጥንድ መስራት | | |
| | ሐ. በቡድን መስራት | | |
| | መ. በህብረት መስራት | | |
| 4 | በትክክለኛነት ላይ ማተኮር | | |
| 5 | ዕለቱ ትምህርት ሞዴል ማቅረብ | | |

ለ

| ተ.ቁ | የመማር ማስተማር ክንውን | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ዕለቱ ትምህርት /ክንውን/ ግልፅ መመሪያ መስጠት | | |
| 2 | ጊዜን በአግባቡ መጠቀም | | |
| 3 | ስህተትን ማረም | | |
| 4 | ምግበ መረጃ መስጠት | | |
| | ሀ. የመምህር ምግበ መረጃ | | |
| | ለ. የቢ.ጤ ምግበ መረጃ | | |
| 5 | አስፈላጊ ሲሆን ገለፃ መስጠት | | |
| 6 | የቤት ስራ መስጠት | | |
| 7 | የክፍል ስራ መስጠት | | |
| 8 | ለመጻፍ ሂደት ተግባሮች ትኩረት መስጠት | | |
| 9 | አስመስሎ መጻፍን (imitation) መጠቀም | | |
| 10 | ዕህፈትን መማር | | |
| | ሀ. በተግባራዊ ልምምድ | | |
| | ለ. በመማሪያ መሳሪያነት | | |
| 11 | ተማሪዎች የግል ገጠመኞቻቸውን፣ ዕውቀታቸውን፣ ሀሳባቸውንና ቋንቋቸውን መጠቀማቸው | | |

ሐ

| ተ.ቁ | የመምህሩ ተግባራት | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1 | የተወሰነና ግልፅ አላማ ይዞ መግባት | | |
| 2 | ተማሪዎች ዕህፈትን በመፃፍ የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ መከታተል | | |
| 3 | የተማሪዎችን ዕሁፍ አንባቢና ገምጋሚ መሆን | | |
| 4 | ተማሪዎቹ በራሳቸው እንዲሰሩ ማድረግ | | |
| 5 | ሁሉም ነገር በራሱ በመምህሩ ብቻ እንዲከናወን ማድረግ | | |

## አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

### በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ አላማ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ያለው መርሀ ትምህርት ውስጥ የዕህፈት ትምህርትን ለማስተማር የቀረቡትን የመማር ማስተማር ክንውኖች (ስነ-ዘዴዎች) አተገባበር በመፈተሽ ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ነው::

በጥናቱ የሚደረስበት ውጤት በደረጃው ዕህፈትን ለማስተማር የሚቀርቡት ስነዘዴዎች ውጤታማ መሆንና ለተማሪዎች የዕህፈት ክሂል መዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታመናል:: ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽም ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል:: ስለዚህ የምትሰጡት ትክክለኛ ምላሽ ለጥናቱ ግብ መምታት ወሳኝ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክል ናቸው የምትሏቸውን መልሶች እንድትሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ::

ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ

ማሳሰቢያ:- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም::

## ክፍል አንድ:- አጠቃላይ መረጃ

ክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃ

1. ፆታ ________________
2. ዕድሜ ________________

ከተራ ቁጥር ሶስት ስር ለሚገኙት ከ3.1-3.3 ጥያቄዎች በክፍት ቦታዎች ላይ የ"√" ምልክትን ተጠቅመው ይመልሱ::

3. የትምህርት ደረጃ
   3.1. የመጀመሪያ ዲግሪ ________________
   3.2. ዲፕሎማ________________
   3.3. ከመምህራን ማሰልጠኛ ሁለገብ መምህር________________
   3.4. ሌላ ከሆነ ይግለፁ________________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ
   4.1. ዓብይ________________
   4.2. ንዑስ________________
5. በመምህርነት ያገለገሉባቸው ዓመታት________________
6. በ ደረጃው አማርኛን ምን ያህል ዓመታት አስተምረዋል________________
7. በሳምንት የሚያስተምሩት የክ/ጊዜ ብዛት________________
8. ሙያዎን ለማሻሻል ከአዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ለመተዋወቅ ሙከራና ጥረት ያደረጉባቸው (ለምሳሌ ተከታታይ ኮርስ፣ ሴሚናር፣ ወርክሾፕ፣ ወዘተ.) መንገዶች ካሉ መጠሪያውንና ዓመተምህረቱን ይፃፉ

| ዓይነቱ | ዓመተ ምህረቱ |
|---|---|
| ሀ. ________________ | ________________ |
| ለ. ________________ | ________________ |
| ሐ. ________________ | ________________ |

## ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል። ትክክለኛ ነው ብለው ያመኑበትን መርጠው ፊደሉን በማክበብ ይመልሱ።

1. አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችል በቂ ስልጠና በተማሩበት ማሰልጠኛ ወስደዋል?
   ሀ. በከፍተኛ ደረጃ ወስጃለሁ
   ለ. በአብዛኛው ወስጃለሁ
   ሐ. በመካከለኛ ደረጃ ወስጃለሁ
   መ. በአብዛኛው አልወሰድሁም
   ሠ. በፍፁም አልወሰድሁም
2. አማርኛን ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና ከወሰዱ የዕህሌት ክሂልን ለማስተማር ቴክኒካዊ ክህሎትንና ዕውቀትን አዳብሮልዎታል?
   ሀ. በከፍተኛ ደረጃ አዳብሮልኛል
   ለ. በአብዛኛው አዳብሮልኛል
   ሐ. በመጠኑ አዳብሮልኛል
   መ. በአብዛኛው አላዳበረልኝም
   ሠ. በፍፁም አላዳበረልኝም
3. የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ወይም በጥንድ በጥንድ መድበው ዕህሌትን በመወያየትና በመተራረም እንዲማሩ ያደርጋሉ?
   ሀ. ሁልጊዜ አደርጋለሁ
   ለ. በአብዛኛው አደርጋለሁ
   ሐ. በመጠኑ አደርጋለሁ
   መ. በአብዛኛው አላደርግም
   ሠ. በፍፁም አላደርግም
4. በተራ ቁጥር ሶስት ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አሉታዊ ከሆነ አማራጭ ነው የሚሉት የትኛው ነው?
   ሀ. ለደረጃው የቀረበውን ትምህርት በገለፃ ማስተማር
   ለ. ተጨማሪ መማሪያ ክፍል በመክፈት ቁጥራቸውን መቀነስ
   ሐ. የቤት ስራ እንዲሰሩ በመስጠት የሰሩትን ማረም
   መ. በቀረቡት መልመጃዎች በውይይት በቃል መልስ ሰጥቶ ማለፍ
   ሠ. በጥቁር ሰሌዳ ላይ መልስ በመፃፍ እንዲያስተካክሉ በማድረግ ማለፍ
5. ዕህሌትን ለመማሪያና ክሂሉን ለማዳበሪያ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎችና ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑት እንዴት ነው?
   ሀ. ተማሪዎቹ የጥያቄዎቹን መልሶች በየተራ በቃል እንዲናገሩ በማድረግ ነው
   ለ. በክፍልና በቤት ስራ የፃፉትን እንዲያነቡ በማድረግ ነው
   ሐ. በዕሁፍ ሰርተው እርስ በእርስ እንዲተራረሙ በማድረግ ነው

መ. በክፍል ወስጥ በቡድን ተወያይተው በየግላቸው እንዲፅፉ በማድረግና በማረም ነው

ሠ. አንድን የፅሁፍ ሞዴል ተከትለው እንዲፅፉ በማድረግና በማረም ነው

6. ጽህፈትን ለማስተማር የቀረቡትን ይዘቶችና መልመጃዎች በሚመለከት በመምህሩ መምሪያ የተጠቀሰውን የአቀራረብ ስልት/የማስተማሪያ ዘዴ ይሰሩበታል?

ሀ. ሙሉ በሙሉ እሰራበታለሁ　　መ. በአብዛኛው አልሰራበትም

ለ. በአብዛኛው እሰራበታለሁ　　ሠ. በፍፁም አልሰራበትም

ሐ. አልፎ አልፎ እሰራበታለሁ

7. ለተማሪዎች በፅሁፍ የሚመለስ የቤት ስራ ይሰጣሉ?

ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ　　መ. አብዛኛውን ጊዜ አልሰጥም

ለ. አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ　　ሠ. በፍፁም አልሰጥም

ሐ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ

8. ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመፃፍ ልምምድ የሚያደርጉበት የክፍል ስራ ይሰጣሉ?

ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ　　መ. አብዛኛውን ጊዜ አልሰጥም

ለ. አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ　　ሠ. በፍፁም አልሰጥም

ሐ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ

9. በፅሁፍ እንዲመልሱ የተሰጣቸውን መልመጃ ተማሪዎች ይሰራሉ?

ሀ. ሁልጊዜ ይሰራሉ　　መ. አብዛኛውን ጊዜ አይሰሩም

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ　　ሠ. በፍፁም አይሰሩም

ሐ. አልፎ አልፎ ይሰራሉ

10. ተማሪዎች የሚሰሩት የፅህፈት መልመጃ ይታረምላቸዋል?

ሀ. ሁልጊዜ ይታረምላቸዋል　　መ. አብዛኛውን ጊዜ አይታረምላቸውም

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ይታረምላቸዋል　　ሠ. በፍፁም አይታረምላቸውም

ሐ. አልፎ አልፎ ይታረምላቸዋል

11. በሚያስተምሩበት ክፍል የተማሪዎችን ስራ አርመው ግብረ ምላሽ (Feedback) / ወይም የማሻሻያ ሀሳብ ሰጥተው ያውቃሉ?

ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ　　መ. በአብዛኛው አልሰጥም

ለ. በአብዛኛ እሰጣለሀ　　ሠ. በፍፁም አልሰጥም

ሐ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ

12.ተማሪዎች በመረጡት፣ እርስዎ በሚሰጧቸው ወይም በመፅሀፉ ውስጥ በሚቀርብ ርዕስ አንቀፅ ወይም ድርሰት እንዲፅፉ ያደርጋሉ?

ሀ. ሁል ጊዜ አደርጋሁ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለሁ

ሐ. አልፎ አልፎ አደርጋለሁ

መ. አብዛኛውን ጊዜ አላደርግም

ሠ. በፍፁም አላደርግም

13.ተማሪዎች የጽህፈት መልመጃ ሲሰሩ በአብዛኛው እንዲያተኩሩበት የሚያበረታቷቸው በምን ላይ ነው?

ሀ. በፅሁፋቸው ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይ

ለ. በሚገልፁት ሀሳብ ተከታታይነትና ግጥምጥምነት ላይ

ሐ. በመፃፍ ሂደት በሚያከናውኗቸው የማቀድ፣ የማርቀቅና የመከለስ ተግባራት ላይ

መ. በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና በስርዓተ አፃፃፍ ላይ

ሠ. ሀሳባቸውን መግለፅና በፅሁፍ መግባባት በመቻላቸው ላይ

14.እርመው ምግበ ምላሽ (Feedback) የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ምላሽ መሰረት ስህተታቸውን አስተካክለው እንደገና እንዲፅፉ ያደርጋሉ?

ሀ. ሁልጊዜ አደርጋለሁ

ለ. በአብዛኛው አደርጋሁ

ሐ. አልፎ አልፎ አደርጋሁ

መ. በአብዛኛው አላደርግም

ሠ. በፍፁም አላደርግም

15.በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የእርስዎ ሚና የትኛው ነው?

ሀ. በጥንድ፣ በቡድንና በህብረት የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ለ. የተማሪዎቹን ስራ መከታተልና መቆጣጠር

ሐ. በግል የሰሩትን መልመጃ ማረም

መ. ስነ-ልሳናዊ ግንዛቤን ለማስጨበጥ በገለፃ ማስተማር

ሠ. ተማሪዎች አንድን ሞዴል ተከትለው እንዲፅፉ ትዕዛዝ መስጠት

16. ለፅህፈት ክሂል መልመጃ በክፍል ውስጥ ለሚቀርበው ክንውን በምንጭነት የሚጠቀሙት የትኛውን ነው?

ሀ. ሙሉ በሙሉ መርሀ ትምህርቱን ነው

ለ. ሙሉ በሙሉ የመምህሩን መምሪያ ነው

ሐ. ሙሉ በሙሉ የመማሪያ መፅሀፉን ነው

መ. ሙሉ በሙሉ በግል የሚያዘጋጁትን ነው

ሠ. ሙሉ በሙሉ ሌሎች ማጣቀሻ ማቴሪያሎችን ነው

17.ተማሪዎች በማስመሰል ለመፃፍ የሚጠቀሙበትን የታላሚ ዕሁፍ ሞዴል አቅርበው በመተንተን ያሳያሉ?

ሀ. ሁልጊዜ አሳያለሁ

ለ. በአብዛኛው አሳያለሁ

ሐ. በመጠኑ አሳያለሁ

መ. በአብዛኛው አላሳይም

ሠ. በፍፁም አላሳይም

## ክፍል ሶስት

ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ክንውኖች ዕህፈትን ለመማር በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ያከናውኗቸዋል ተብሎ ይታሰባል:: ክንውኖችን ለተማሪዎች አቅርበው የሚያለማምዱ ከሆነ በተዳጋጋሚ ተግባራዊ ከሚሆነው በመጀመር በደረጃ ያስቀምጧቸው:: ደረጃቸውን ለማመልከትም ይበልጥ ከሚደጋገመው በመጀመርና 1 2 3... በማለት በሰንጠረዡ ውስጥ ፊት ለፊታቸው ቁጥሩን ይፃፉ::

| ተ.ቁ | ክንውኖች | |
|---|---|---|
| 1 | ለቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍች መስጠት | |
| 2 | በቀረቡት የቃላት ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን መመስረት | |
| 3 | በጅምር የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ማሟላት | |
| 4 | አስተዋፅኦ ማዘጋጀትና አንቀፅ መፃፍ | |
| 5 | የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለምሳሌ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን፣ ምሳሌያዊ አባባሎችን፣ ቅኔዎችን መፍታት | |
| 6 | ድርሰት፣ ደብዳቤ፣ ሪፖርት፣ ወዘተ. መፃፍ | |
| 7 | ዕሁፍን ማሳጠር፣ ግጥምን ወደ ስድ ዕሁፍ መቀየር | |
| 8 | የፈጠራ ስራዎችን ለምሳሌ ግጥም፣ አጭር ታሪክ፣ ጭውውት መፃፍ | |
| 9 | ከሰሌዳ ላይ በመገልበጥ ማስታወሻ መያዝ | |
| 10 | የቃል ዕህፈት መፃፍ | |

መጠይቁን ሞልተው በመመለስ ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው::

አጥኚው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የመማር ማስተማር ክንውን | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለሥዕሎች ፎቶግራፎችና ሠንጠረዦች የሚሆኑ የግርጌ መግለጫዎችን ይፅፋሉ:: | 23.6 የግርጌ መግለጫ /ካፕሽን/ | | 1. ተዘበራርቀው ከሚሰሟቸው በርካታ የግርጌ መግለጫዎች ውስጥ በክፍሉ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለተለጠፉ ስዕሎች በተለይ የሚሆኑትን እንዲመርጡ በማድረግ ማለማመድ፤<br>2. ሠንጠረዥ ሠርተውና የተለያዩ ሥዕሎችንና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የግርጌ መግለጫ እንዲያዘጋጁ ማለማመድ፤ | • የግርጌ መግለጫ ያላቸው የተለያዩ ከጋዜጦችና መጽሔቶች ሥዕሎችና ፎቶዎች | 1. ከተለያዩ የግርጌ መግለጫዎች ውስጥ በተለይ የሚቀርቡላቸውን ስዕል ሊገልፁ የሚችሉ መግለጫዎችን መምረጣቸውን በክፍል ሥራ ማረጋገጥ፤<br>2. ለልዩ ልዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች ተስማሚ የሆኑ የግርጌ መግለጫዎችን መፃፍ መቻላቸውን በቤት ሥራ |



# የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት

## 5ኛ ክፍል

## ሁለተኛው የትምህርት ክፍለ ዓመት

| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የመማር ማስተማር ክንውን | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሁለት | ስለአንድ ሀሳብ የሚያወሳ አንቀፅ ይፅፋሉ:: | 20. አንቀፅ መፃፍ፡ | 3 | 1. በአንድ አንቀፅ ውስጥ ያለ አረፍተ-ነገሮች ስለ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ የሚናገሩ መሆን እንዳለባቸው ማስገንዘብ፤<br>2. አንድ አንቀፅ የሚያብራራው ዋና ሀሳብ ብዙ ጊዜ በአንቀፅ መጀመሪያ ላይ እንደሚገኝ ማስገንዘብና የተለያዩ አንቀፆችን እያቀረቡ ማሳየት፤<br>3. እንደሁኔታው ሁለትም ሦስትም አረፍተ-ነገር ያለው ጅምር አንቀፅ ሰጥቶ የጎደለውን ሀሳብ የያዙ አረፍተ-ነገሮች በመጨመር እንዲያሟሉ ማለማመድ፤<br>4. የተለያዩ መንደርደሪያና ዝርዝር ሀሳቦችን አንድ ላይ አቅርቦ ከየመንደርደሪያ ሀሳቡ ጋር አብረው የሚሄዱ ዝርዝሮችን እንዲመርጡና አንቀፅ እንዲፅፉ ማድረግ፤<br>5. ልዩ ልዩ መንደርደሪያ አረፍተ-ነገሮችን በማቅረብ በሚመርጡት አንቀፅ እንዲፅፉ በማድረግ ማለማመድ፤ | • ሞዴል አንቀፆች | 1. የአንድ አንቀፅ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ መረዳታቸውን የተለያዩ የቃል ጥያቄዎች አቅርቦ ማረጋገጥ፤<br>2. ስለአንድ አንቀፅ ዋና ሀሳብ ተግባርና በአንቀፁም ስለሚገኝበት ሥፍራ መገንዘባቸውን የተለያዩ አንቀፆችን መንደርደሪያ አረፍተነገሮች እንዲጠቁሙ በማድረግ ማረጋገጥ፤<br>3. ጅምር አንቀፅ ሰጥቶ የተጓላ ሀሳብ በሚሰጥበት ሁኔታ ሊጨርሱ መቻላቸውን የተለያዩ ጅምር አንቀፆችን በክፍል ሥራ በማቅረብ ማረጋገጥ፤<br>4. በሚሰሟቸው መንደርደሪያ አረፍተ-ነገር አንቀፅ መፃፋቸውን የቤት ሥራ መገምገም:: |

# 6ኛ ክፍል

## ሁለኛው የትምህርት ክፍል ዓመት

| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የመማር ማስተማር ክንውን | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ለዋሰው | ስለአንድ ሀሳብ የሚገልፅ አን ቀፅ ይፅፋሉ:: | 18. አንቀፅ መፃፍ፡ | 4 | 1. ትደምተከተላቸው ያልተስተካከለ አረፍተነገሮችን ትደምተከተላቸውን ጠብቀው የተሟሉ አንቀፆች እንዲያደርጓቸው በማድረግ ማለማመድ፣<br>2. አንድን አንቀፅ ሰጥቶ ዋናውን ሀሳብ እንዲገልፁ በማድረግ የአንቀፅን አመሠራረት ማሳወቅ፣<br>3. አንድ አንቀፅ አንድ መንደርደሪያ አረፍተነገርና ዝርዝር አረፍተነገሮች ያሉት ሲሆን ዝርዝር አረ ፍተነገሮቹ መንደርደሪያውን አረፍተነገር የሚያጎሉ መሆናቸውን በተለያዩ ምሳሌዎች ማሳወቅ፣<br>4. አንቀፅ ስለአንድ ሀሳብ ብቻ የሚገልፅ መሆኑን መገንዘባቸውን ከተለያዩ ጋዜጦችና መፅሄቶች አንቀፅችን አምጥተው የአንቀፃቸውን ዋና ሀሳብ እንዲገልፁ በማድረግ ማጠናከር፣<br>5. የተለያዩ መንደርደሪያ ሀሳቦችንና ዝርዝር ሀሳቦችን በማቅረብ ለየመንደርደሪያው ተገቢ የሚሆኑ ዝር ዝር ሀሳቦችን እንዲመርጡ ማድረግና አንቀፆችን እንዲፅፉ ማድረግ፣<br>6. መንደርደሪያ አረፍተነገር ሰጥቶ በቡድን ውይይት ዝርዝር ሀሳቦችን እንዲሰጡ ማድረግና በተናጠልም አንቀፅ እንዲፅፉ በማድረግ ማለማመድ፡ | - ሞዴል አን ቀፆች የተፃፉ በት ቻርት | 1. አንቀፅ ምን ማለ ትም እንደሆነ ማወ ቃ ቸውን በተለያዩ ጥያቄ ዎች መገምገም፣<br>2. በአንድ አንቀፅ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የሚይዝ አረፍተነገር የሚዘረዝሩ አረፍተ ነገሮች እንዳሉ ማወ ቃ ቸውን መንደርደሪያና ዝርዝር አፍተነገሮችን አንድ ላይ አቅርቦ በመለየታቸው መከታ ተል፤<br>3. በተለያየ መልኩ ስለ አንቀፅ የተማሩትን መሠረት አድርገው አንቀፅ መፃፍ መቻላ ቸውን ማረጋገጥ፣ |



| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የመማር ማስተማር ክንውን | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰዋስው | • በአያያዦች ይጠቀማሉ::<br>• ትጥያዎች አያያዦች ሆነው የትር ጉም ለውጥ እንደሚያመጡ ይገለፃሉ:: | 19. የአያያ ዦች አጠ ቃቀም፣ | 2 | 1. የአያያዦች ትጥያዎች መለዋወጥ /ፍች/ ለውጥ ሊያስከትል እንደሚችል በደረጃው በሚመጥኑ ልዩ ልዩ መልመጃዎች አማካይነት ማለማመድ፣<br>ምሳሌ:- አለማዝ ስለነገረችው ቀረ:: /ምክንያት/<br>አለማዝ እንደነገረችው ቀረ:: /ወዲያው-ጊዜ/<br>2. ተስማሚ አያያዥ ሐረጎች ያሏቸው ለደረጃው የሚመጥኑ አረፍተ-ነገሮችን በማቅረብ የትርጉም ለውጥ ሳያመጡ ያሉትን ሊተኩ የሚችሉ ሌሎች አያያዥ ሐረጎችን እንዲያስገቡ በማድረግ ማለማ መድ፣<br>3. ለደረጃው ተመጣጣኝ በሆኑ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ አያያዥ ትጥያዎችንና ሐረጎችን በማስገባት አገል ግሎታቸውን ማሳወቅ፣<br>ምሳሌ:- ሀ/ ምንም እንኳ፣<br>ለ/ የሆነ ሆኖ፣<br>ሐ/ እንዲሁም፣<br>መ/ ታዲያ፣<br>ሠ/ ከ የተነሣ፣<br>4. በአያያዦች ሊገናኙ የሚችሉ አጠር አጠር ያሉና ለደረጃው የሚመጥኑ የአንቀፅ ፅሁፎችን ሳያገናኙ ሰጥቶ ተገቢዎቹን አያያዦች ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በመወያየት እንዲጨም ሩ በማድረግ ሰፋ ያለ ልምምድ መስጠት፣ | - የተለያዩ አያያዦችንና አጠ ቃቀማቸ ውን የሚያሳዩ አረፍተ-ነገሮ ችን የያዘ ቻርት | 1. የአያያዥ ትጥያዎች መለዋወጥ የትርጉም ለውጥ እንደሚያስከትል ማወ ቃቸውን የቤት ስራ በመስጠት መገምገም፣<br>2. በአረፍተነገር ውስጥ ያሉ አያያዥ ሐረጎችን የትርጉም ለውጥ ሳያ መጡ በሌሎች አያያ ዦች መተካት መቻላ ቸውን በክፍል ውስጥ ስራ መከታተል፤<br>3. በተለያዩ አንቀፆች ውስጥ ለሚገኙ አረ ፍተ-ነገሮች ተስማሚ አያያዥ ትጥያዎችና ሀረጎች በመጨመር የተሟላ ትርጉም ሊሰ ጡ በሚችሉበት ሁኔታ ለማገናኘት መቻላቸውን የቡድን ስራ በመስጠት ውጤቱን መፈተሽ፣ |

| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 3. የተለያዩ ካርታዎችን አቅርቦ በካርታዎቹ እየተመሩ ልዩ ልዩ መግለጫዎች እንዲሰጡ ባቸው እያረጉ ማለማመድ።<br>4. ስለተወሰነ አካባቢ የቀረበን ጽሁፋዊ ማብራሪያ በካርታ አማካይነት ሠርቶ በአጭሩ ማቅረብ እንደሚቻል በማሳየት ማለማመድ። | | | 2. ስለፁሁፍ ማብራሪያ የቀረበን ካርታ ከጽሁፉ ጋር እያነበቡ የተሟላ ሃሳብ ማግኘት መቻላቸ ውን የተለያዩ ጥያቄዎችን እያቀረቡ መመልከት።<br>3. አንዳንድ የፅሁፍ ሃሳቦችን በካርታ አማካይ ነት መግለጽ መቻላቸውን አቅማቸውን አካባቢን የሚገ ልፁ ፅሁፎችን አቅርቦ መከታተል። |
| | ከግራፍ ያገኙትን የመረጃ ሃሣብ ያቀርባሉ። | 16.2 ከግራፍ | 1. ግራፍ አንድ ነገር ከወቅቶች አንፃር የሚያሳየውን ተከታታይ ልድገት/መቀነስ ያመጣውን ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን በተለያዩ ግራፎች፣<br>2. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በማወዳደር ሊያሳይ የሚችል መግለጫ መሆኑን የተለያዩ ምሳሌዎችን አቅርበው እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>3. ለግራፍ መሠረቱ የሚሆነውን ነገር ልኩን ከሚያሳየው ማነፃፀሪያ አኳያ ማንበብና ማገናዘብ መሆኑን ማሳወቅ።<br>4. ለደረጃው በሚመጥኑ ግራፎች የተለያዩ ሃሳቦችን እንዲያስረዱና እንዲገልጹ በማድረግ ማለማመድ። | | • ግራፎች<br>• ከግራፎች የተገኙና የመረጃ ሃሣብ ሞዴል መግለጫዎች | 1. የግራፍን ምንነትና አገልግሎቱን ማወቃቸ ውን መከታተል።<br>2. ከግራፍ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ተረድተው መግለጽ መቻላቸውን የተለያዩ ግራፎችን መሠረት አድርገው በሚሰጡት ገለፃ መገምገም። |
| | የኢንዴክስን አጠቃቀም ተረድተው ይገለገላሉ። | 16.3 ከኢንዴክስ | 1. ኢንዴክስ በፊደል ተራ የተዘረዘሩ ስሞችና ርዕሶች ከሚገኙበት ገጽ ጋር በመጣሕፍት በጽሁፎች መጨረሻ ገጽ የሚገኝ መሆኑን ማሣወቅና የተለያዩ መፃፍትን በምሳሌነት ማሳየት።<br>2. በኢንዴክስ ውስጥ በሚገኙት ዋና ዋና ሃሣቦች ጥቆማ እየተመሩ ገጾቹን በማውጣት ስለ ሃሣቡ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል በማስረዳት በሚዘጋጅ እንዴክስ መረጃዎችን ማግኘት እንዲችሉ ማለማመድ። | | • ኢንዴክስ ያላቸው ሞዴል መፃሕፍት | 1. የኢንዴክስን ምንነት መገንዘባቸውን ጥያቄዎችን አቅርቦ መገምገም።<br>2. በኢንዴክስ ተጠቅመው የመረጃ ሀሳብ ማግኘት መቻላቸውን እንዴክሶችን አዘጋጅቶ መመዘን። |



| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፅሕፈት | አረፍተ ነገሮችን አገጣጥመው አንቀፅ ይፅፋሉ። | 17. አንቀፅ መፃፍ | 1. በተለያየ አንቀፅ ሊከፋፈሉ የሚችሉ ፅሁፍን ሳይከፋፍሉ አቅርቦ በጋራ ውይይት ምክንያት እየሰጡ እንዲከፋፍሉ ማድረግ፣<br>2. በአንድ/በሁለት አረፍተ ነገሮች የቀረበን ሃሳብ በሌሎች አረፍተ ነገሮች በመደገፍ አሟልተው እንዲፅፉ በማድረግ የተማሩትን ማጠናከር።<br>3. በአንቀፅ አፃፃፍ መሠረት ችግር ያለበትን አንቀፅ ሰጥቶ ከዝርዝሩ ውስጥ ዋናውን ሃሳብ የማይደግፉትንና በሌላ አንቀፅ ሊቀርቡ የሚገባቸውን እንዲለዩና አንቀፆችን እንደገና እንዲፅፏቸው ማድረግ።<br>4. አንድ አንቀፅ አንድ መንደርደሪያ አረፍተ ነገርና ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ያሉት ሲሆን ዝርዝሮቹ መንደርደሪያውን በተጨባጭ መረጃ ዎችና ምሳሌዎች እያዳበሩ የሚያጎሉ መሆናቸ ውን እያሳዩ ማለማመድና እነሱም እንዲፅፉ ማድረግ። | 4 | • ናሙና አንቀጾች<br>• በተማሪዎች የተፃፈ የተመረጡ አንቀጾች | 1. ያልተከፋፈሉ አንቀጾች ምክንያት እየሰጡ እንዲከፋፈሉ በማድረግ መገምገም።<br>2. ጅምር አረፍተ ነገር አሟልተው አንቀፅ መፃፍ መቻላቸውን መመዘን።<br>3. የተለያዩ አንቀ ፆችን መንደርደሪያና ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ። |
| ሰዋስው | • በአያያዦች ይገለገላሉ<br>• የአያያዦችን አገልግሎት ያስረዳሉ። | 18. አያያዦች | 1. ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን በመስጠት በአያያዥ ቃላት እንዲገለገሉ ማድረግ።<br>2. ቀደም ሲል የተባለውን ሃሳብ በማፍረስ ከቀጣዩ ጋር የሚያያዙ ቅጥያዎችንና ሐረጎችን ማለማመድ።<br>ምሳሌ፦ ተከፍቷል ግን ደስተኛ ይመስላል። የምንዋደድ እንመስላለን ዳሩ ግን እንጣጣምም። | 2 | • የአያያዦች ዝርዝር<br>• በአያያዦች የተጣመሩ አረፍተ ነገሮች | 1. የአያያዥ ቅጥያ ዎችንና ሐረጎችን አገልግሎት መረዳትና መገልገላቸውን መከታተል። |

| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከካርታ የሚያገኙትን መረጃ ይገልጻሉ። | 16. ከመገለጫዎች የመረጃ ሀሳቦችን ማግኘት<br>16.1 ካርታ | 1. በካርታ አማካይነት ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ማለማመድ።<br>2. ስለሀገራችን ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ መስህቦችና የተፈጥሮ ሀብቶች መረጃ ሰጪ ካርታዎችን ተመልክተው ልዩ ልዩ መረጃዎችን እንዲተረጉሙ በማድረግ ማለማመድ። | 4 | • ካርታ | ካርታዎችን ተመልክተው የተለያዩ መረጃዎች መስጠት መቻላቸውን በክፍል ተያቄ መገምገም። |
| | በግራፍ የቀረበን መረጃ ተረድተው ያስረዳሉ። | 16.2. ግራፍ | 1. በጽሁፍ ቢገለጽ ብዙ ጊዜና ወረቀት የሚፈጁ ሃሳቦችን በአነስተኛ ወረቀት ላይ ቦታና ጊዜን በመሰፈሪያ /በስኬል/ ቆጥቦ ለማስተላለፍ ግራፍ ጠቃሚ መሆኑን በምሳሌ ማስረዳት፤<br>2. አንድን ሁኔታ፤ (ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት፤ የሕዝብ ብዛት ዕድገት...) የሚያሳይ ግራፍ ሠርቶ በማቅረብ በግራፉ የተላለፈውን መረጃ በተገቢ ማብራሪያ እንዲያስረዱ በማድረግ ማለማመድ። | | • ግራፍ | 1. ከሂሳብ መምህር ጋር በመወያየት ስለግራፍ አዘገጃጀት የተረዱትን መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።<br>2. ከግራፍ ያገኙትን መረጃ ተንትነው በጽሁፍ ማቅረብ መቻላቸውን መገምገም። |



| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | የክፍል ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተጨማሪ ማብራሪያን ምንነት ተገንዝበው ይገልጻሉ። | 16.3. ተጨማሪ ማብራሪያ /አፔንዲክስ/ | 1. አፔንዲክስ በአንድ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙ ሃሳቦችን በተሟላና በተጨማሪ መልኩቸው መረጃ ለማቅረብ/ለማግኘት እንደሚያገለግል ባለፈው የክፍል ደረጃ የተማሩትን መነሻ በማድረግ ማለማመድ።<br>2. ተጨማሪ ማብራሪያ ያላቸውን መፃህፍት ወይም ጽሁፎችን እያቀረቡ በዋና ይዘቱና በተጨማሪ ማብራሪያው መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ተገንዝበው እንዲናገሩና እንዲጽፉ በማድረግ ማለማመድ፤<br>3. ተጨማሪ ማብራሪያ ለዋነኛው ይዘት የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ተመራምረው በማግኘት እንዲናገሩ/እንዲጽፉ ማለማመድ። | | • አፔንዲክስ ያለው ናሙና መጽሀፍ | 1. ከተጨማሪ ማብራሪያ ወይም ከአፔንዲክስ የሚገኙ መረጃዎችን አገልግሎት ማወቃቸውን ለጥያቄዎች መልስ በሚሰጡት ማረጋገጥ።<br>2. የመጽሀፉ ዋና ይዘትና ተጨማሪ ማብራሪያው የሚኖራቸው መደጋገፍ በምን ደረጃ እንደሆን መገንዘባቸውን ተጨማሪ ማብራሪያ ያለውን መፅሐፍ አቅርቦና ማብራሪያ እንዲሰጡ በማድረግ መመዘን፤ |
| ቃሀፈት | በምሣሌና በመረጃዎች የዳበረ አንቀፅ ይፅፋሉ። | 17. አንቀፅ መፃፍ | 1. የሀሳብ ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተ ነገሮችን በማቅረብ በአንድ አንቀፅ አስተካክለው እንዲፅፉ በማድረግ ባለፈው የተማሩትን በልምምድ ማጠናከር። | 3 | • የአንቀጽ ምንነት የሚገልፅ ማብራሪያ<br>• ሞዴል አንቀፆች | 1. ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተ ነገሮችን ለዋቀ ቅንብሩ በተስተካከለ አንቀፅ እያሳኩ መፃፍ መቻላቸውን በክፍል ሥራ ማረጋገጥ። |

| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2. የተለያዩ መንደርደሪያና ዝርዝር ሐሳቦችን አደበላልቆ በመስጠት እያንዳንዱን መንደርደሪያ ከነዝርዝሮቹ እንዲለዩና የተለያዩ አንቀፆችን እንዲፅፉ ማድረግ። <br> 3. መንደርደሪያ አረፍተ ነገር እያቀረቡና እነሱም እንዲያቀርቡ በማድረግ አንቀፅ እንዲፅፉ ሀሳቦችን እንዲሰጡ በማድረግ ማለማመድ። <br> 4. አንድ አንቀጽ መንደርደሪያ አረፍተ ነገር እንዳለው ሁሉ መደምደሚያ አረፍተ-ነገር የሚኖረው መሆኑን ገልፆ ለተለያዩ አንቀፆች መደምደሚያ እንዲሰጡ በማድረግ ማለማመድ፣ <br> 5. አንድን ጉዳይ የሚመለከቱ ሁለት ተቃራኒ መንደርደሪያ አ.ነገሮችን በመስጠት ሃሳቡን የሚያጎሉ በምሳሌና በመረጃ የተደገፉ ዝርዝር አ.ነገሮችን እየጨመሩ የተሟላ አንቀፅ እንዲፅፉ ማለማመድ። | | | 2. ራሳቸው በሚያቀርቧቸው መንደርደሪያ አ.ነገሮች መነሻነት አንቀፅ መፃፍ መቻላቸውን መገምገም። |



| የትምህርት ክፍል | ዝርዝር ዓላማ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | የክፍለ ጊዜ ብዛት | የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች | ክትትልና ግምገማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ምሳሌ፡ ኢድስ እንዳይስፋፋ ማድረግ ይቻላል/ ኢድስ እንዳይስፋፋ ማድረግ አይቻልም፣ <br> • ግብር መክፈል ያለበት ነጋዴ ብቻ ነው/ ግብር መክፈል ያለበት ነጋዴ ብቻ አይደለም፣ <br> • የቤት ሥራ መስጠት አለበት/ የቤት ሥራ መስጠት የለበትም። | | | |
| ዕሀፈት | ስዕላዊና (መስታወታዊ) አመዛዛኝ ድርሰቶችን ይፅፋሉ። | 18. ድርሰት <br> • ስዕላዊ <br> • አመዛዛኝ | 1. ስለድርሰት ዓይነቶች የተማሩትን መከለስና በቡድን ሆነው ለተራኪና ለገላጭ ድርሰቶች አብነት የሚሆኑ ድርሰቶችን አሰባስበው ክፍል ውስጥ እንዲያነቡ በማድረግ ማጠናከር፣ <br> 2. የስዕላዊና የአመዛዛኝ ድርሰቶችን ባህርያት ማብራራትና የተለያዩ ምሳሌዎችን አቅርቦ ምሳሌዎቹ ስዕላዊና አመዛዛኝ ስለመሆናቸው ምክንያት እየሰጡ እንዲያብራሩ ማድረግ፣ | 6 | ሞጁል ሥዕላዊና አመዛዛኝ ድርሰቶች | 1. የስዕላዊና አመዛዛኝ ድርሰቶችን ባህርያት በደረጃቸው መግለፅ እንዲችሉ ማድረግና ምሳሌ የሚሆኑ ድርሰቶችንም አምጥተው እንዲያነቡ በማድረግ መገምገም፣ <br> 2. ሰውንና አካባቢን የሚገልፁ ስዕላዊ ድርሰቶችን ከተለያዩ ልቦለድ መፃህፍት ፈልገው እንዲያወጡ በማድረግ መገምገም፣ |

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸውና የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራ መሆኑን፣ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎችና ምንጮችም በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

ስም: አንለይ አዳነ

ፊርማ:

አድራሻ: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል አዲስ አበባ::

ቀን: 16/10/2000 ዓ.ም